1. መግቢያ

የዐቃቤ ህግ ክህሎት ስንል ምን ማለት ነዉ?
ወደተራቀቀ ትንተና መግባት ሳያስፈልግ የዚህ አባባል ሃሳብ በጠቅላላዉ የዐቃቤህግ ተቋም በሚያከናዉናቸዉ ተግባራት ላይ የአንድ ዐቃቤህግ ብቃትን የሚመለከት ነዉ በማለት እንነሳለን:: ይህ ብቃት በመደበኛ ትምህርት ፣ በሥራ ልምድ ፣ በሥልጠና በሚገኝ ችሎታ ላይ የተመሰረተ ነዉ::

የህግ ዕዉቀት - ይህ ዕዉቀት በመደበኛ ትምህርት፣ በልምድ ወይም በሥልጠና ሊዳብር ይችላል:: በተለይ ዋና ወይም መሰረታዊ ህግጋትን በተመለከተ በመደበኛ ትምህርት በቂ ዕዉቀት ሊገኝ ይችላል::

*በልምድ የተገኘ ችሎታ*ዉ ከላይ እንደተመለከተዉ የህግ ዕዉቀት በመደበኛ ትምህርት ሊገኝ ይችላል:: ሆኖም ይህ ዕዉቀት ብቻ በዐቃቤህግ ተግባራት ላይ ብቃትን አያጎናጽፍም:: ለዚህ ብቃት በልምድ የሚከማቸዉ ዕዉቀት ወይም ችሎታ ቀላል የማይባል አስተዋጽዖ ይኖረዋል::
ሆኖም ነባሮች ከሃላፊነት ብዛት ወይም ከስራ ዉጥረት የተነሳ አዲሶችን በወግ የማሰልጠን አቅም ያንሳቸዋል:: የሚሰጧቸዉም የተለመደዉን ነዉ:: አዳዲስ አማራጮችን አብረዉ አይመረምሩም:: ስለዚህ አዲሶች ሁልጊዜም እንደየጉዳዩ እና እንደየጊዜዉ የሚስተካከል አሰራር ወይም አቀራረብ ማዳበር ያስፈልጋቸዋል::
*በስልጠና የሚገኝ ችሎታ*ዉ የህግ ዕዉቀትም ሆነ በልምድ የሚገኝ ችሎታ እንደማንኛዉም ዕዉቀት በጊዜ ርዝማኔ በአዳዲስ ዕዉቀት እየተተካ እና እያረጀ ስለሚሄድ በየጊዜዉ መታደስ ይኖርበታል:: ይህን እድሳት ባለሙያዉ ራሱ በግል ጥረቱ (በማንበብ፣ በተጨማሪ መደበኛ ትምህርት ወዘተ) ሊያከናዉነዉ ይችላል:: ከዚህ በበለጠ ግን በየጊዜዉ በሚሰጡ ስልጠናዎች አማካኝነት የባለሙያዉ ችሎታ ከጊዜዉ ጋር እንዲሄድ ማድረግ ይቻላል::

ለምሳሌ የፌዴራል ዐቃብያነ ህግ በሚተዳደሩበት ደንብ (ቁ. 44/1991 ከቁ. 52 ጀምሮ) እንደተደነገገዉ በተቋሙ ከላይ ለተመለከተዉ ዓላማ ስልጠና ይዘጋጃል:: ዐቃብያነ ህግም በዚህ ስለጠና የመሳተፍ ግዴታ አለባቸዉ::

በስልጠና የሚገኝ ችሎታ በህግ ላይ መሰለጠንን ያስቀራልን? ለብቃት መሻሻል የሚሰጡ ስልጠናዎች በህግ ዕዉት ላይ ሊሆኑ ይችላሉ:: አዳዲስ ህግጋት ይወጣሉ፣ አዳዲስ ጽንሰሃሳቦች ይፈጠራሉ፣ አዳዲስ አተረጓጎሞች ሊነሱ ይችላሉ ወዘተ. ስለዚህ በነዚህ አይነት ጉዳዮች ላይ መሰልጠን አይቀሬ ነዉ::

ክህሎት ከዕዉቀትና ችሎታ ጋር ብቻ የተያያዘ ነዉን? ብቃት የጊዜ አጠቃቀምን፣ የሃብት አጠቃቀምን ወዘተ ያካትታል::
ጊዜ ደግሞ የስራ ሰዓትን ብቻ የሚመለከት አይደለም:: በአፋጣኝ ፍርድ ከማግኘት መብት ጋር ይያያዛል:: ዐቃቤህግ ይህን መብት የሚጎዳ ተግባር መፈጸም አይኖርበትም:: ይህ ነገር ከዐቃቤህግ አጠቃላይ ሚና ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነዉ:: ይህ አጠቃላይ ሚና የህግ ጠባቂነት ሚና ነዉ::

የዐቃቤህግ የህግ ጠባቂነት ሚና እና የሰዎችን መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታ:- ዐቃቤህግ ከስሙ እንደሚታየዉ የህግ ጠባቂ፣ ባለአደራ ወዘተ ማለት ነዉ:: ስለዚህ በማንምና በየትም ቦታ የሃገሪቱ ህግጋት መከበራቸዉን ማረጋገጥ የዐቃቤህግ ተግባር ነዉ:: የሃገሪቱ ህግጋት ከሚደነግጓቸዉ ነገሮች ከፊሉ የሰዎች መብቶችን ይመለከታሉ:: ስለዚህ ከዐቃቤ ህግ ግዴታዎች አንዱ የሰዎችን መብቶች መከበር ማረጋገጥ ይሆናል:: ይህን ለመተግበር ደግሞ ለዚሁ የተደነገጉ ህግጋትን አፈጻጸም ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል::
ስለዚህ የዐቃቤህግ ክህሎት ከዚህ ሚናዉ አኳያ የተቃኘ መሆን አለበት:: ክህሎቱ የራሱን ክስ ለማስረዳት ብቻ ሳይሆን በጠቅላላዉ የህግ መከበርን (የሰዎችን መብት መከበርን) የሚያራምድ መሆን ይኖርበታል::
በዐቃቤህግ ተግባራት ሊጎዱ ከሚችሉት መብቶች ዉስጥ በአፋጣኝ ፍርድ ከማግኘት መብት በተጨማሪ የመከላከል መብትን እና ንጹህ ሆኖ የመገመት መብትን እናገኛለን:: እነዚህን መብቶች ለመተግበር በርከት ያሉ የሥነሥርዓት ህግጋት ወጥተዉ እናገኛለን:: የነዚህን ህግጋት መከበር ዐቃቤህግ ሊያረጋግጥ ይገባል::

ከዚህ በተጓዳኝ እና ከዚህ ዕኩል ዐቃብያነ ህግ ለህግ ማስፈጸም ብቃትም ሊጨነቁ ይገባል:: ስለዚህ የሰዎችን መብትም ሆነ የህብረተሰብን ጥቅም የሚያስጠብቁ ህግጋትን በሚተገብሩበት ጊዜ ሁለቱን ጥቅሞች አቻችሎ የመተግበር ክህሎት ሊኖራቸዉ ይገባል:: የእነዚህ ጥቅሞች ፉክክር በዐቃብያነ ህግ የዕለትተዕለት ተግባራት ዉስጥ የሚንጸባረቅ ነዉ:: ስለዚህ ይህ ስልጠና ተገቢነት ይኖረዋል::

ለዚህም በዚህ ስልጠና የተለያዩ የዐቃብያነ ህግ ተግባራት በህግ እና በተግባር ያላቸዉን ቦታ እንዳስሳለን:: በዚህ ረገድ በህግ እና በተግባር መካከል ያለዉን ልዩነት እንመረምራለን:: እንዲሁም ይህን ክህሎት በማዳበርም ሆነ በመተግበር ጊዜ ከፍርድቤት ጋር ባለ ግንኙነት ምክንያት የሚደርሱ ተጽዕኖዎችን እንተነትናለን::

ዐቃብያነ ህግ የተለያዩ ተግባራት አሏቸዉ:: እነዚህ ተግባራት በጠቅላላዉ ከወንጀል ምርመራ እና የወንጀል ክስ አቅርቦ ከመከራከር ጋር የተያያዙ ናቸዉ:: ይህን ለምሳሌ ከአዋጅ ቁ 4/1987 ቁ 23(2) እና (4) ማየት ይቻላል::

> 23. የፍትህ ሚኒስቴር
>
> የፍትህ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፦
>
> ...
>
> 2. በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ስር በሚወድቁ ወንጀሎች ፌዴራል መንግሥቱን በመወከል ይከራከራል
>
> ...
>
> 4. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል ፦ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል ፦ በህግ መሰረት የወንጀል ክስ ያነሳል

ስለዚህ ፍትህ ሚኒስቴር (ዐቃቤህግ) ከወንጀል ምርመራና ከወንጀል ክስ መሰማት ጋር የተቆራኙ ታላላቅ ተግባራት አሉት ማለት ነዉ።

2. ከወንጀል ምርመራ ጋር የተያያዙ የዐቃብያነህግ ተግባራት

የዐቃቤህግ ተቋም የተቋቋመባቸዉ የተለያዩ ህግጋት ከላይ ከተመለከተዉ ባለፈ ይህ ተቋም የወንጀል ምርመራ ሊያከናዉን እንደሚችል ሲደነግጉ ቆይተዋል (አዋጅ ቁ. 11/1980):: እንዲሁም እንዲህ አይነቱ አቀራረብ በአሁኑ ጊዜ እንዲቀጥል ፍላጎት እንዳለ የሚያዚያ 2001 ዓም. የኢፌዴሪ ረቂቅ የወንጀል ፖሊሲ ይጠቁማል (የረቂቁ 3.4 ሐ):: ከዚህ በተረፈ ግን ከላይ እንደተመለከተዉ ዐቃቤህግ በአሁኑ ጊዜ የወንጀል ምርመራን የመምራትና የመቆጣጠር ሥልጣን እንዳለዉ ይስተዋላል::

ዐቃቤህግ ከወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ ስላለዉ ሚና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ ተደንግጎ ይገኛል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 8(2)፣ 16፣ 17፣ 38-48፣ 66፣ 80ና ተከታዮቹ፣ 109(1)):: በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለዉጥ አማካኝነት ዐቃቤህግና ፖሊስ የወንጀል ምርመራን

ሥራ በጋራ የሚያካሂዱበትን አሰራር ለመዘርጋት እይተሞከረ ይገኛል:: ይህን ሁሉ ስንመለከት ዐቃቤህግ በወንጀል ምርመራ ሥራ ዉስጥ የሚኖረዉ ሚና ሰፊ እንደሆነ እንገነዘባለን::

የምርመራ መመሪያ ስለመስጠት

በተለመደዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ አሰራር ዐቃቤህግ በምርመራ ተግባር ዉስጥ ተሳትፎ የሚያደርገዉ ፖ/ሊስ ባከናወነዉ ምርመራ ላይ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ:: ይህ ዉሳኔ ተጨማሪ ምርመራ የሚደረግበት መመሪያ ለምርመራ ክፍሎች የሚሰጥበትን የሚያጠቃልል ነዉ:: ይህ መመሪያ ከተጠርጣሪ መብትም ሆነ ከህግ ማስፈጸም ጥቅም አኳያ ፖ/ሊስ በመሰለዉ መንገድ ምርመራዉን በእጁ ካቆየ በኋላ ከሚሆን ከመጀመሪያዉኑ ለምርመራ ክፍሉ ቢሰጥ የተሻለ እንደሚሆን አያጠያይቅም:: ይህን ለማድረግ የሥ/ሥ/ ህጉ በግልጽ የደነገገዉ ነገር የለም:: ሆኖም አዋጅ ቁ. 4/1987 ለፍትህ ሚኒስቴር በሰጠዉ ሥልጣን መሰረት እንዲሁም የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 16(2) እንደሚደነግገዉ ዐቃቤህግ የወንጀል ምርመራ እንዲደረግ ማዘዝ ስለሚችል በዚህ አጋጣሚ የምርመራ መመሪያዉ ከመነሻዉ ሊሰጥ ይችላል:: እንዲያዉም አሁን ባለዉ አዝማሚያ ዐቃቤህግና ፖ/ሊስ የወንጀል ምርመራን በጋራ ሊያካሂዱ የሚችሉበት አጋጣሚ የበዛ ስለሚሆን ይህ መመሪያ አስቀድሞ ከዐቃቤህግ ሊገኝ ይችላል ማለት ነዉ:: ሆኖም ችግሩን ለማስወገድ ይህ ብቻዉን በቂ ነዉ ለማለት አያስደፍርም:: ክስ አቅርቦ ለሚከራከረዉ ዐቃቤህግ ነገሩ ከቀረበ በኋላ መመሪያ የመስጠት አጋጣሚን ማስቀረት አይቻልም::

የምርመራ መመሪያ ምንምን ሊይዝ ይገባል? እንደየጉዳዩ አይነት ይህ መመሪያ ሊይዛቸዉ የሚገቡ ነገሮች አስቀድሞ ሊለዩ መቻላቸዉ ያጠራጥራል:: ሆኖም እነዚህ ነገሮች ሊኖራቸዉ ስለሚገባዉ አጠቃላይ ባህሪ አንዳንደድ ነገሮች ማንሳት ይቻላል:: ይህ መመሪያ በዐቃቤህግ የሚሰጥ እንደመሆኑ በምርመራዉ የህግ ብቃት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል:: የምርመራዉም ሆነ ከዚህ ቀጥሎ የሚሰሩ ከወንጀል ጉዳይ ጋር የተያያዙ ሥራዎች አንድ ትልቅ ግብ አላቸዉ - ወንጀል የፈጸመ ሰዉ ለፍርድ ቀርቦ ተገቢዉን ምላሽ እንዲያገኝ ማድረግ:: ስለዚህ የሚሰጠዉ የተጨማሪ ምርመራ መመሪያ ክሱን ለማስረዳት አስፈላጊ ስለሆኑ ጉዳዮች መሆን ይገባዋል:: ይህም በህግ የተፈቀደ ሊሆን ይገባዋል፣ የሚከናወነዉ የምርመራ ተግባር በህግ የተፈቀደና የሰዉን መብት ያላግባብ የማይጎዳ ሊሆን ይገባል::

ማሳያ-1

የቀረበልዎ የወንጀል ምርመራ ሪፖርት ወይም መዝገብ በርከት ያሉ ሰዎች የተመረመሩበት ሲሆን ከነዚህ ዉስጥ አንዱ ተጠርጣሪ ቃሉን ያልሰጠበት ነዉ እንበል:: ተጠርጣሪ ቃሉን ያልሰጠዉ ፈቃደኛ ስላልሆነ ነዉ ተብሎ በምርመራ መዝገቡ ተጠቅሷል:: ሌላዉ ተጠርጣሪ የሰጠዉ ቃል የወንጀሉ ዋና አቀናባሪ የሆነዉ ሰዉ ላይ በቂ መረጃ የሚሰጥ ነዉ:: በዚህ ሪፖርት

ላይ ምን አይነት ዉሳኔ ይሰጣሉ፣ ይህን ዉሳኔ ይጻፉትና ከባልደረባዎ ዉሳኔ እያስተያዩ በልዩነቶቹ ላይ ከባልደረባዎ ጋር ይከራከሩበት።

የምርመራ መመሪያ ያላግባብ ስለሚሰጥባቸዉ ሁኔታዎች

እነዚህ አጋጣሚዎች ሥራን ገሸሽ ለማድረግ ማለትም ክስን የመዝጋት ዉሳኔ ላለመስጠት (አድካሚ ስለሆነ)፣ የስታቲስቲክስ ግብ ለማሟላት፣ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ የሚሰጡ መመሪያዎች ለጉዳዩ ምንም የማይፈይዱ ተግባራት እንዲከናወኑ ሊሆን ይችላል። ከዚህም በቀር ነገሩ ቶሎ እንዳይቋጭ ለማድረግ በሚደረግ ሴራ መመሪያዉ ሊሰጥ ይችላል። ይህ ነገር ሊረጋገጥ ባይችል እንኳ በተገልጋዩ ዘንድ ይህ ጥርጣሬ ከተፈጠረ የተቋሙን ዉጤታማነት ለመጉዳት በቂ ነዉ።

መያዝና ብርበራ

ዐቃቤህግ በምርመራ ሥራ የሚሳተፍ እንደመሆኑ በምርመራ ጊዜ የሚነሱ የህግ ጥያቄዎች ላይ የምርመራ ክፍሉን ያግዛል - ምክር በመስጠት። የህግ ጥያቄ ከሚያስነሱት አጋጣሚዎች ዋናዎቹ ተጠርጣሪን የመያዝና ብርበራ አድርጎ ማስረጃ መያዝ ይገኙበታል። ዐቃቤህግና የምርመራ ክፍሎች በተናጠል በሚሰሩበት ጊዜ በርካታ ክርክር የሚያስነሱ ተግባራት የሚፈጸሙት እነዚህን የምርመራ ሥራዎች በማከናወን ወቅት ነዉ። በዚህ ደረጃ የሚፈጸሙ ተግባራት የወንጀል ፍትህ ሥርዓቱን ሂደት ይወስናሉ - መያዝ የማይገባዉ ሰዉ ሲያዝ ዐቃቤህግ ክስ አልመሰርትም ብሎ እስኪወስን ወይም ፍርድቤት በነጻ እስኪያሰናብተዉ ተጠረጣሪዉ ተይዞ ይቆያል። መያዝ የሚገባዉ ሰዉ ሳይያዝ ቢቀር የህግ ማስፈጸም ጥቅም ይጎዳል። ሊያዝ ስለሚገባዉ ሰዉ አያያዝ በህግ የተመለከተዉ ባግባቡ ካልተፈጸመም እንዲሁ ተመሳሳይ ችግር ይከሰታል። በብርበራ ጊዜም ቢሆን ይኸዉ ነዉ።

ዐቃቤህግ የምርመራ ክፍሎችን ስለመያዝ፣ ስለብርበራ እና ማስረጃ ስለመያዝ ህግጋት ሊያማክራቸዉ ይገባል። እነዚህ ህግጋት ምን ይላሉ?

ስለመያዝ

በተለምዶ ተጠርጣሪን መያዝ በፍርድቤት ትዕዛዝ ብቻ ሊፈጸም እንደሚገባ ይታመናል። በርግጥም እንደመርህ ይህ ዕዉነት ነዉ። ሆኖም ያለፍርድ ቤት ፈቃድ መያዝ የሚቻልባቸዉ አጋጣሚዎች እንዳሉ በህግ ተደንግጎ ይገኛል፣ ስለብርብራና መያዝም እንዲሁ። በነዚህ ህግጋት መሰረት የሚፈጸሙ የምርመራ ተግባራትን በተመለከተ የሚፈጠሩ የተዛቡ አስተሳሰቦችን ዐቃብያነህግ ግልጽ በማድረግ መርማሪዎችን መርዳት ይኖርባቸዋል።

ህጎቹ የወ/መ/ሥ/ሥ/ ህጎች ናቸዉ። መርማሪዎች ያለፍርድቤት ፈቃድ ሰዉ መያዝ የሚችሉባቸዉ ህግጋት እንደተለዩ ሁኔታዎች የተደነገጉ ቢሆኑም እጅግ የበዙ ወንጀሎች ተጠርጣሪዎችን ያለፍርድቤት ፈቃድ መያዝ የሚያስችሉ ናቸዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 50፣ 51)። ከሚቀርቡ የወንጀል አቤቱታዎች በመነሳት በምን ሊያስከስሱ እንደሚችሉ በመለየት ከሚያስቀጡት ቅጣት አኳያ ያለፍርድቤት ትዕዛዝ መያዝ በሚቻልባቸዉ አጋጣሚዎች በትዕዛዝ አለመኖር ሰበብ ሊያዝ የሚገባዉ ሰዉ ሳይያዝ እንዳይቀር ዐቃብያነ ህግ መርማሪዎችን ይህን ህጋዊ ተግባራቸዉን ሊያስታዉሷቸዉ እና የህግ ማስፈጸመን ጥቅም ሊያገለግሉ ይገባቸዋል።

ማሳያ 2

አንድ የእጅ ስፍንጅ ወንጀል ምርመራ በቀጠለበት ወቅት አንድ ሳምንት ያህል ቆይቶ ከፖሊስ ተታኩሰዉ ካመለጡ በወንጀሉ ተፈላጊ ከሆኑ ሰዎች ዉስጥ አንዱ የሚገኝበት ቦታ የት እንደሆነ እና ከሃገር ለመዉጣት ስግማሽ ቀን ያነሰ ጊዜ ብቻ የቀረዉ መሆኑ በተበዳይ ጥቆማ ታወቀ። ፖሊስ የመያዣ ትዕዛዝ ስላልነበረዉ ተበዳይዋ ተፈላጊዉ በፍጥነት እንዲያዝ ያደረገችዉን ዉትወታ አልተቀበለም። ስለዚህ አቤቱታ ይዛ ወደዐቃቤህግ ዘንድ ቀረበች።

ዐቃቤህግ በሁለቱ ጉዳዮች ላይ ምን ትዕዛዝ ወይም ምክር ለፖሊስ ሊሰጥ ይገባዋል?

አንድን ተጠረጣሪ ከመያዝ በፊት ወንጀል ፈጽሟል ብሎ ለማመን የሚያስችል ሁኔታ መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 25)። ይህም ምርመራ ሊደረግ እንደሚገባ ያሳያል። በዚህ ምርመራ ወንጀል ተፈጽሞ ሊሆን እንደሚችል መገመት ከተቻለ ተጠርጣሪዉ እንዲቀርብ በመርማሪዉ ሊጠራ ይገባል። ሊሸሽ እንደሚችል ጥርጣሬ ከሌለ በቀር ይህን ሰዉ ለማቅረብ የሰዉ እና የቁስ ሃብት ሊባክን አይገባም - የታጠቀ የፖሊስ ኃይል (በሌላ ቦታ ሊሰማራ የሚገባዉ) ያስፈልጋል፣ የሰዉ ክብር ሊጎዳ ይችላል - በክብር ራሱ ሊቀርብ የሚችል ሰዉ እንዳደገኛ ሰዉ በሚያዉቁት ሰዎች ፊት በታጠቀ ኃይል ታጅቦ መሄድ ክብርን ያዋርዳል።

የከፋው ሁኔታ ደግሞ ታጅቦ መሄድን በኃይል የመቃወም ነገር ሊከሰት መቻሉ ነው:: በዚህ ጊዜ የሰዉ ህይወትና ንብረት ለአደጋ ይጋለጣል::

ማሳያ 3

ወንጀል ተፈጽሞብኛል ያሉ አንድ ተበዳይ ለእርስዎ ጽ/ቤት ተጠርጣሪ ተይዞ ምርመራ እንዲደረግበት የሚጠይቅ ማመልከቻ አቀረቡ:: በህግ እንደሚጠበቀዉ ፖሊስ ምርመራዉን እንዲያደርግ ማመልከቻዉን ይልኩለታል:: ሆኖም መርማሪዉ ለምርመራዉ ጉዳይ ተጠረጣሪዉን በተመለከተ ምን ሊያደርግ እንደሚገባዉ ተገቢዉን መምሪያ ይጻፉለት:: የጻፉትን መመሪያ ከባልደረባዎ መመሪያ ጋር ያነጻጽሩ:: ያለዉን ልዩነት ያዉጡና በዚህ ላይ ተከራከሩ::

በርብሮ ስለመያዝ

በዚህም ረገድ ከተለዩ ሁኔታዎች በቀር ብርበራ እና መያዝ በፍርድቤት ትዕዛዝ ሊፈጸም ይገባል:: ብርበራና መያዝ የሰዎችን አካል፣ መኖሪያቤት፣ የሥራ ቦታና ንብረት መጠበቅ መብት የሚጎዳ ተግባር ነዉ:: ሆኖም ይህ መብት በህብረተሰቡ መሃል ሆኖ የሚሰራበት በመሆኑ ወንጀሎችን ለመደበቅ ማገልገል የለበትም:: ስለዚህ ወንጀል ስለመፈጸሙ በቂ ጥርጣሬ የሚፈጥር ሁኔታ እስካለ ድረስ የወንጀሉ ፍሬዎች ወይም የወንጀል መፈጸሚያ መሳሪያዎች ደብዛቸዉ ጠፍቶ ለሌላ ወንጀል መፈጸሚያ ከመሆናቸዉ በፊት ሊያዙ ስለሚገባ የፍርድቤት ፈቃድ እስኪገኝ መጠበቅ ሳያስፈልግ ብርበራና መያዝ ሊፈጸም ስለሚችል የምርመራ መሪ ወይም ተቆጣጣሪ የሆነዉ ዐቃቤህግ በዚህ አይነት እንዲፈጸም ማድረግ ይጠበቅበታል:: ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳ አከራካሪ ጉዳይ አለ:: ተገቢዉ የሥነሥርዓት ሁኔታ ሳይሟላ የሚፈጸም ብርበራና መያዝን ይመለከታል:: በዚህ ረገድ ያለዉ አቋም የተለያየ ነዉ:: ይህን አሰራር የሚቃወሙ የሚያቀርቡት ክርክር በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረዉም የሚለዉን የህገመንግሥት ድንጋጌ (ቁ 19(5)) ነዉ::

መወያያ - ማሳያ

- የህገመንግሥት ቁ.19(5) ድንጋጌ እንዴት ሊተነተን ይገባል?

- ሁሉንም ከህግ ዉጪ የተገኘ ማስረጃን (በተለይም ያለፍርድቤት ትዕዛዝ በተደረገ ብርበራ ተገኝቶ የተያዘን ማስረጃ) ተቀባይነት እንዲይኖረዉ ያደርጋል?

- ተገዶ ማመን ተቀባይነት እንዲይኖረዉ የተደረገበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል?

- ይህ ምክንያት በርብሮ በመያዝ ጊዜ ተፈጻሚ እንዲሆን ለማድረግ ይቻላል?

- ከተጠርጣሪ ወጪ የሆነ ነገር (ተበርብሮ የተያዘ ነገር) እንደዕምነት ቃል ከዕውነታዉ ጋር ያለመጣጣም አደጋ ሊያጋጥመዉ ይችላል?
- ስለዚህስ ስለአስረጂነት ብቃቱ አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል?

ማሳያ

አንድ የፖሊስ ባልደረባ በመደበኛ ሥራዉ ላይ ሆኖ ያጋጠመዉን የእጅ ስፍንጅ ወንጀል ፈጻሚ በመከታተል ላይ እንዳለ ተጠርጣሪዉ በአንድ ግቢ ዉስጥ ስለገባ ተከትሎት ሲገባ በግቢዉ ዉስጥ ሌሎች ሰዎች በርካታ ጠብመንጃዎችና ቦምቦች በሳጥን እንደታሸጉ ትልቅ መኪና ላይ ሲጭኑ ደረሰ። ሁኔታዉን እንደተረዳ ያለፍርድቤት ትዕዛዝ ተጠቃሹን ዕቃ መያዝ የሚች ስለመሆኑ በመጠራጠሩ በተንቀሳቃሽ ስልክ ወደጽ/ቤትዎ ደዉሎ ምን ሊያደርግ እንደሚገባዉ ጠየቀ። በስልክ የሚሰጡትን መመሪያ በጽሁፍ ያስፍሩትና ከባልደረባዎ ጋር ስለተገቢነቱ ወይም ስህጋዊነቱ ተወያዩበት።

በሌላ በኩል መርማሪዉ የፍርድቤት ትዕዛዝ ይዞ ብርበራ ሊያደርግ በተጠርጣሪዉ መኖሪያ ቦታ እንደተገኘ ብርበራ ከሚከናወንበት ወንጀል ጋር ግንኙነት የሌለዉ ነገር ግን ሌላ ወንጀል ተፈጽሞበት ደብዛዉ ጠፍቶ የነበረ ሽጉጥ በዚህ ቦታ ተቀምጦ አየ። ይህ ሽጉጥ በብርበራ እንዲያዝ በትዕዛዙ ዉስጥ ከተዘረዘሩት ንብረቶች ዉስጥ አይገኝም። መርማሪዉ ይህን የወንጀል መሳሪያ አስመልክቶ መያዝ ይችል ወይም አይችል እንደሁ በስልክ ስለጠየቀዎ የሚሰጡትን መመሪያ በጽሁፍ ያስፍሩት። ከባልደረባዎ መመሪያ በምን ይለያል? ስለተለያያችሁበት ምክንያት ተከራከሩ።

ከዚህ በላይ የተገለጠዉ የብርበራ ትዕዛዝ የወንጀል መሳሪያዉን ለመያዝ የተሰጠ እንደሆነ ያስቡ። ሆኖም ይህ መሳሪያ በተጠርጣሪ መኖሪያ ቤት ሲፈለግ በዚሁ መሳሪያ በማስገደድ የተወሰደዉ ንብረት ተገኘ። ይህ ንብረት የት እንደገባ ፍንጭ ስለጠፋ መርማሪዉ በርብሮ ለመያዝ ከጠየቃቸዉ ንብረቶች ዉስጥ ያላካተዉ በመሆኑ በብርበራ ትዕዛዙ ዉስጥ አልሰፈረም። በርባሪዉ ፖሊስ ይህን ንብረት ለመያዝ ይችል እንደሁ አሁንም በስልክ ጠየቀዎ። ምን መመሪያ ይሰጡታል? ይጻፉት። የርስዎ መመሪያ ከባልደረባዎ የተሻለ ወይም ተገቢ የሚሆንበትን ምክንያት በማንሳት ተከራከሩ።

አካላዊ ወይም የህሊም ምርመራ(ወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 34)

ያለ ተመርማሪዉ ፈቃድ እንዲህ አይነት ምርመራዎች ማድረግ ይቻላል?

ማስገደድና ዉጤቱ - ይህን ምርመራ ያለተመርማሪዉ ወይም ያለተጠርጣሪዉ ፈቃድ መፈጸም ፍጹም የሆነዉን የአካል ደህንነት መብት የመጣስ ዉጤት ይኖረዋል (የህ/መንግሥት ቁ. 16)። በዚህ ጊዜ ዐቃቤህግ እንደምርመራ መሪ መርማሪዎችን ምን ሊመክራቸዉ ወይም መመሪያ ሊሰጣቸዉ ይችላል? የሰዎችን መብት የሚመለከተዉ የፍትሃብሄር ህግ ክፍል ሰዎች የህክምና ምርመራን እምቢ የማለት መብት እንዳላቸዉ ይደነግጋል (የፍትሃብሄር ህግ ቁ. 20)። ይህ ድንጋጌ ቢኖርም መርማሪዉ የአካል ወይም የህክምና (ደምን ጨምሮ) ምርመራ በተጠርጣሪዉ ላይ እንዲደረግ አንድን የተፈቀደለት ሃኪም ሊያዝዝ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 34)።

ማሳያ

አሰገድዶ በመድፈር የእጅ አፍንጅ ወንጀል ተጠቂ የሆነችዉ ሴት በአንድ ሆስፒታል በተደረገላት ምርመራ የተለያዩ የአባለዘር በሽታዎች ኤች አይ ቪን ጨምሮ ተገኙባት። ይህን የሚገልጽ የህክምና ምርመራ ዉጤት ስለቀረበ ፖሊስ በተፈላጊዎቹ ላይ የደምና የአካል ምርመራ እንዲደረግ አዘዘ። ሆኖም ተፈላጊዎቹ ይህን ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። ፖሊስ ይህን ምርመራ እንዴት ማስፈጸም እንዳለበት ስለተቸገረ ከዐቃቤህጉ መመሪያ ጠየቀ።

ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ተገቢ ነዉ የሚሉትን መመሪያ ለመርማሪዉ ይጻፉ፣ ከባልደረባዎ መመሪያ ጋር ያነጻጽሩት እና ያሉትን ልዩነቶች በማዉጣት ተከራከሩባቸዉ።

የጊዜቀጠሮና የዋስትና ጥያቄ ላይ ስለመከራከር

የጊዜ ቀጠሮና የዋስትና ጥያቄዎች የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሊባሉ ይችላሉ። አንዱ ጥያቄ ሲፈቀድ ሌላኛዉ ተከለከለ ማለት ነዉ ወይም ተገላቢጦሹ። የዋስትና ጥያቄ ከክስ በፊት ወይም በክስ መሰማት ጊዜ ሊቀርብ ይችላል። በነዚህ ተግባራት ዙሪያ ዐቃቤህግ ብቻ ሳይሆን ፍርድቤቶችም ተሳታፊ ስለሚሆኑ በዚህ ግንኙነት ወቅት የፍርድቤቶች አሰራር ወይም አቀራረብ

በዐቃብያነህግ ክህሎት ላይ ተጽዕኖ መፍጠሩ አይቀርም:: እነዚህን ተግባራት ከህግና ከልምድ እንዲሁም ከዚህ ግንኙነት አኳያ እናያለን::

ገዘቀጠሮ:- አንድ ሰዉ በወንጀል ተጠርጥሮ ተይዞ ፍርድቤት ሲቀርብ የሚወሰነዉ ነገር በማረፊያ ቤት ስለማቆየት ወይም በዋስ ስለመልቀቅ የሚመለከት ይሆናል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 59):: አንዱ ተቀባይነት አገኘ ማለት ሌላኛዉ ተከለከለ ማለት ነዉ:: ዐቃቤህግ በመርማሪነት ከተሳተፈ በዚህ ክርክር ላይ ሊሳተፍ ይችላል:: ሆኖም አዘዉትሮ በዚህ ደረጃ ተከራካሪ የሚሆነዉ መርማሪ ፖሊስ ነዉ:: ስለዚህ የዐቃቤህግ ሚና የህግ ምክር የመስጠት ሊሆን ይችላል:: ምን ሊመክር ይችላል?

ምርመራ ለመቀጠል የሚያስችል ጊዜ በፍርድቤት ለማስፈቀድ ጥያቄ ሲቀርብ ምርመራ ተጀምሮ ሊጠናቀቅ አለመቻሉን ማስረዳት ይጠበቃል:: ተጠርጣሪዉን ለመያዝም ቢሆን ወንጀል ፈጽሟል ብሎ ለማመን የሚያበቃ ምክንያት መኖር አለበት:: ይህ ምክንያት በምርመራ የሚገኝ ነዉ:: ስለዚህ ዐቃቤህግ አንድ ተጠርጣሪ እንደተያዘ ቀደም ብሎ የተጀመረዉ ምርመራ ሳይቋረጥ እንዲቀጥል የምርመራ ክፍሉን መምከር ይኖርበታል:: ተጠርጣሪ ፍርድቤት ከመቅረቡ በፊት ተይዞ በቆየበት ጊዜ ምርመራ ካልተካሄደ ምርመራ እንደተጠናቀቀ ሊገመት ይችላል:: ስለዚህም ፍርድቤት የጊዜቀጠሮ ሲጠየቅ የምርመራ ጊዜ ላይፈቅድ ይችላል፣ ወይም ሳይፈቅድ ቢቀር የሚወቀስበት ሁኔታ ላይኖር ይችላል:: ወይም የምርመራ ጊዜ ቢፈቅድ ጊዜዉ አጭር እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል::

ከዚህ ጋር የተያያዘዉ ጉዳይ ተጠርጣሪን በተገቢዉ ፍጥነት ወደፍርድቤት የማቅረብ ነገር ነዉ:: ዐቃቤህግ የህግ ባለአደራ ጠባቂ እንደመሆኑ የሰዎችን መብቶች ለመጠበቅ የተደነገጉ ህጎችን በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸዉን መቆጣጠር ይኖርበታል:: እንደምርመራ ተቆጣጣሪ ለምርመራ ክፍሎች ስለዚህ ጉዳይ ተገቢዉን ምክርና ትዕዛዝ በመስጠት ወይም ምርመራዉን ራሱ የሚያከናዉን ከሆነ በሥነሥርዓት ህጎችና በህግመንግሥት የተመለከቱ የጊዜ ድንጋጌዎችን በማክበር ለምርመራ የተያዘን ሰዉ በተገቢዉ ጊዜ ፍርድቤት እንዲቀርብ ማድረግ ይጠበቅበታል::

በምርመራ ሪፖርት ላይ ስለመወሰን

የወንጀል ምርምራ ክፍሎች የምርመራ ተግባራቸዉን ሲያጠናቅቁ የዚህ ምርመራ ሪፖርት ለዐቃቤህግ ይቀርባል:: ይህም የሚሆነዉ በምርመራዉ ላይ የህግ ዉሳኔ ወይም ሃሳብ እንዲሰጥበት ነዉ:: በአዲሱ አሰራር ደግሞ ዐቃቤህግ ምርመራ ከፖሊስ ጋር ስለሚያከናዉን የምርመራዉን አካሄድ እዛዉ ሆኖ ይመለከታል:: ስለዚህ ዐቃቤህግ ይህ ሪፖርት ሲደርሰዉ

ወይም የምርመራውን አካሄድ እያየ የሚፈጽማቸዉ በርካታ አማራጭ ተገባራት አሉ። በጠቅላላዉ ምርመራን መዝጋት፣ ክስ አለማቅረብ፣ ክስ መመስረት፣ ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ማዘዝ ሊሆኑ ይችላሉ። በነዚህ ተግባራት ዐቃቤህግ ተገቢዉ ክህሎት ሊኖረዉ ይገባል። እነዚህ ተግባራት በህግ የሚመሩ እንደመሆናቸዉ የነዚህን ህግጋት አተገባበር በዉል ማወቅ ይገባል። ይህ ካልሆነ የዐቃቤህግ የህግ ጠባቂነት ሚና መና ይሆናል።

ተጨማሪ ምርመራ

ስለተጨማሪ ምርመራ ቀደም ብሎ እንደተመለከተዉ ዐቃቤህግ ከመነሻዉ ተገቢዎቹን የምርመራ ትዕዛዞች እየሰጠ ምርመራዉ የሚከናወንበት አጋጣሚ የበዛ ነዉ፣ በተለይ በምርመራ ተግባር በቀጥታ ተሳታፊ ሲሆን። ሆኖም ከዐቃቤህግ ቁጥጥር ዉጪ የሚደረጉ ምርመራዎች ስለማይጠፉ የምርመራ ክፍሎች በመሰላቸዉ መንገድ ያከናወኗቸዉ ምርመራዎች በህግ የሚፈለጉ ግብዓቶችን ሳያሟሉ ሊገኙ ይችላሉ።

በዚህ ጊዜ ዐቃቤህግ ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ሊያዝዝ ይችላል።

ማሳያ

በቀረበልዎ የምርመራ ሪፖርት ዉስጥ ከተሰበሰቡ ምስክርነቶች ማየት እንደሚቻለዉ ሁለት ሰዎች ለጉዳዩ ምስክር መሆናቸዉና ቃላቸዉ መመዝገቡ እጅግ አስፈላጊ ነዉ። ነገር ግን መርማሪዉ ይህን ባለማድረጉ የምርመራ ክፍሉን በዚህ አይነት እንዲሰራ ለማዘዝ ፈለጉ። ከዚህ በፊት በነበረዎ የሥራ ልምድ በተመሳሳይ ሁኔታ የተጠርጣሪን ቃል መመዝገብ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት ለዚሁ ብለዉ የሰጡት የተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዝ ተጠርጣሪዉ ቃል ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለሁም ስላለ ቃሉ ሳይመዘገብ የምርመራ ሪፖርቱ ሊቀርብ መቻሉን በመግለጽ የምርመራ ክፍሉ መልስ እንደሰጠዎ ያስታዉሳሉ። ስለዚህ ያሁኑን የተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዝ በቀጥታ ይሰጣሉ ወይስ ከዚህ በፊት ለማከናወን የሚያስፈልግ ተግባር ይኖራል? ከባልደረባዎ ጋር ይወያዩበት።

በሌላ በኩል ዐቃቤህግ ተገቢዉን ጥንቃቄ ሁሉ አድርጎ ተጨማሪ ምርመራ የግድ ከሆነ በትዕዛዝ አሰጣጥ ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮችን የሚያስቀር አሠራር ሊከተል ይገባል። ይህም አንዱ የዐቃቤህግ ክህሎት ነዉ። በተለይም ተደጋጋሚ የምርመራ ትዕዛዞችን ከመስጠት መዳን አለበት። ለዚህ ደግሞ በመጀመሪያዉ አጋጣሚ ተገቢዉን የተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዝ ሁሉ ልቅም አድርጎ የመስጠት ክህሎት ሊኖረዉ ይገባል። እንዲህ ካልሆነ ተደጋጋሚ የምርመራ ትዕዛዞችን በመስጠት ነገሩ በተገቢዉ ፍጥነት ለፍርድ እንዲቀርብ የሚጠይቀዉን የመብት ድንጋጌ የመጠበቅና የማስፈጸም ግዴታዉን ዐቃቤህግ እንዳይወጣ ይሆናል።

በዚህ አይነት ለታዘዘዉ ተጨማሪ ምርመራ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ ፍርድቤቶች በዚህ ነገር ዙሪያ የሚኖራቸዉ አቀራረብ ዐቃቤህግ በዚህ ረገድ የሚኖረዉን ክህሎት ሊወስን ይችላል። ፍርድቤት የተጠየቀዉን ጊዜ ሁሉ ያለበቂ ምክንያት የሚፈቅድ ከሆነ ዐቃቤህግ ሥራዉን

በተገቢዉ ፍጥነትና ጥራት ከማከናወን እንዲዘናጋ የማድረግ ዉጤት ይኖረዋል:: ስለዚህ ፍርድቤቶች ለተጨማሪ ምርመራ የጊዜቀጠሮ በሚጠየቅ ጊዜ የሚከናወን ምርመራ ስላለ ብቻ ጊዜ ሊፈቅዱ ይገባል ወይስ ነገሩን በጥብቅ በመመርመር ቁጥጥር ሊያደርጉ ይችላሉ?

የፌዴራል ፍርድቤት የሙስና ወንጀሎች ችሎት ልምድ ስናይ የጸረሙስና ኮሚሽን በሌሎች የምርመራ አካላት ያስፈጸመዉን ምርመራ መሰረት አድርጎ የሚጠይቀዉ የተጨማሪ ምርመራ ማድረጊያ ጊዜ ሊፈቀድ እንደማይገባ፣ ምክንያቱም ምርመራዉ የራሱ በመሆኑ ከመጀመሪያዉም ተገቢዉን መመሪያ እየሰጠ ማስመርመር አለበት፣ ይህ ሳይደረግ በተከናወነ ምርመራ ላይ ተጨማሪ ጊዜ ሊጠየቅ አይገባም፣ ስለዚህ ጥያቄዉ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በሚል መንፈስ የሚወስኑባቸዉ አጋጣሚዎች ነበሩ (ከጸሃፊዉ ተሞክሮ - በዚህ ችሎት በዳኝነት ሠርታለች):: ይህን አካሄድ መከተል ተገቢነት የለዉም?

መወያያ *ይህ አቀራረብ ተገቢ ነዉ ቢባል ዐቃቤህግ በዚህ ምክንያት በጉዳዩ ላይ ሊደርስ የሚችለዉን ጉዳት ለማስቀረት ምን ሊያደርግ ይገባል?*

ምርመራ መዝጋት (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 42 እና 38 39)

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 39 በተመለከቱት ምክንያቶች ዐቃቤህግ የወንጀል ምርመራ መዝገብ ይዘጋል::

ማሳያ *ይህ የሚሆነዉ ምርመራ ከተጠናቀቀ በኋላ ነዉ ወይስ በማንኛዉም ጊዜ ነዉ? ምርመራዉ በመካሄድ ላይ እያለ ዐቃቤህግ በነዚህ ምክንያቶች ላይ ተንተርሶ ምርመራዉ እንዲዘጋ ማድረግ ይችላል? ምርመራዉ ከመጀመሩ በፊትስ?*

በፌዴራል አዋጅ ቁ/ 4/1987 በቁ/ 23(4) እንደተመለከተዉ ምርመራ እንዲቆም የማድረግ ሥልጣን ለዐቃቤህግ ተሰጥቶታል:: ይህ ድንጋጌ እንደሚያመለክተዉ:-

> 23. የፍትህ ሚኒስቴር
> የፍትህ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣
> ...
> 4. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል፣ ...

በዚህ ጊዜ የተጠርጣሪው መሞት፣ የዕድሜው ከዘጠኝ ዓመት ማነስ፣ ወይም ያለመከሰስ መብት ያለው መሆኑ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 39(1)) ምርመራውን ለማስቆም በቂ ምክንያት ሊሆኑ አይችሉም?

ያም ሆነ ይህ እነዚህ ሁኔታዎች መኖራቸው ሲታወቅ ዐቃቤህግ የምርመራ መዝገቡን የመዝጋት ሥልጣን አለው:: የነዚህ ህግጋት ሃሳብ ምርመራው ተጠናቀቀም አልተጠናቀቀም እነዚህ ምክንያቶች ሲኖሩ ምርመራው (መዝገቡ) ሊዘጋ ይገባዋል፣ ስለዚህም ዐቃቤህግ ምርመራ በማቋረጥ ሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ ይህን የመዝጋት ተግባር ሊያከናውን ይገባል የሚል ይመስላል:: የሞተ ሰው ላይ ክስ ማቅረብ አይቻልም (የወ/ህ/ቁ/ 214) :: ዕድሜው ዘጠኝ ዓመት ያልሞላው ሰው በወንጀል ኃላፊነት የለበትም (የወ/ህ/ቁ/ 52):: ያለመከሰስ መብት ባላቸው ሰዎች ላይ ክስ የማቅረብ ፈቃድ ካልተገኘ በቀር ክሱ በመቃወሚያ ቀሪ ሊደረግ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 130(2)(ሠ)):: እነዚህ ሁኔታዎች ባሉበት ክሱን ወይም ምርመራውን ለመዝጋት ምርመራ እስኪጠናቀቅ መጠበቅ ፋይዳ ይኖረዋል?

የተጠርጣሪው መሞትና የዕድሜው ሁኔታ ለምርመራ መዘጋት ምክንያት በሚሆኑበት ጊዜ በቀላሉ የሚረጋገጡና ጥያቄ የሚያስነሱ አይሆኑም:: ያለመከሰስ መብት የመኖሩ ነገር እንደክስ መዝጊያ ምክንያትነት ሲታይ አንዳንድ ጥያቄዎች ማስነሳቱ አይቀርም:: በተለይ ዋናው ጥያቄ ደግሞ እንዲህ አይነቶቹ ሰዎች እነማን ናቸው የሚለው ይሆናል:: ከነዚህ ሰዎች ውስጥ የዲፕሎማቲክ ያለመከሰስ መብት የተሰጣቸውን ሰዎች መለየት ብዙም አያስቸግር ይሆናል:: ሆኖም በተለየ ህግ መብቱ የተሰጠው ሰው ማን ነው የሚለው ጥያቄ ግን በዉል ሊተነተን ይገባል::

የፌዴራልም ሆነ የክልል የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት አባላት፣ የአንዳንድ ክልሎች ዳኞች ያለመከሰስ መብት በህግ ተዉቆላቸዋል፡፡

መወያያ

ከፌዴራልና ክልል ምክርቤቶች አባላትና ከክልል ዳኞች በቀር ያለመከሰስ መብት ያላቸው ሰዎች የትኞች ናቸው? ይዘርዝሯቸው፡፡

የነዚህ ሰዎች ያለመከሰስ መብት እስከምን ድረስ ነው? ከባልደረባዎ ጋር ይወያዩበት፡፡

ያመከሰስ መብት ባለበት ሁኔታ ምርመራ የሚዘጋው ምርመራው ከመጀመሩ በፊት ሊሆን ይችላል?

አልከሰስም ስለማለት

ዐቃቤህግ ከሚሰጣቸዉ ዉሳኔዎች ዉስጥ ቀደም ሲል ከተገለጸዉ ምርመራ ከመዝጋት ጋር ተቀራራቢ የሆነዉ ክስ ያለማቅረብ ዉሳኔ ነዉ:: በህጋችን በቂ ምክንያት እሰካለ ድረስ ክስ ማቅረብ የዐቃቤህግ ግዴታ ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 40):: ስለዚህ አልከሰስም የማለት ሥልጣን እንደተለየ ሁኔታ የሚታይ ስለሆነ በህግ በግልጽ የተወሰነ እና የማይሰፋ ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 42(1)ና(2)) :: ይህን ሥልጣን የሚደነግገዉን ህግ ብንመለከት

> ቁ. 42 ክስ የማይቀርብባቸዉ ሁኔታዎች
> 1. ክስ ማቅረብ የማይቻለዉ፣
>   ሀ) ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ የሆነ መረጃ የሌለ መሆኑን ዐቃቤህጉ የተረዳዉ እንደሆነ ወይም
>   ለ) የተከሰሰዉን ሰዉ ለማግኘት የማይቻል ወይም በሌለበት ክሱ ሊታይ የማይቻል የሆነ እንደሆነ ወይም
>   ሐ) ክሱን ለማቅርብ በይርጋ የታገደ ወይም ለተፈጸመዉ ወንጀል ምሕረት ወይም የዐዋጅ ምሕረት (ይቅርታ) ተደርጎ እንደሆነ ነዉ
> 2. ከዚህ በላይ ከተመለከቱት በቀር ዐቃቤህጉ በማንኛዉም ሌላ ሁኔታ ክስ አላቀርብም ለማለት አይችልም::
> ...

ይላል:: ከነዚህ ሁኔታዎች ዉስጥ በመጀመሪያ ተራ በተነገረዉ ሁኔታ ዐቃቤህግ ክስ አላቀርብም ብሎ የሚወስንበት አጋጣሚ የበዛ ነዉ:: ይህን በመጣስ ክስ ቢቀርብ በፍርድቤት ምርመራ ክሱ ዋጋ እንዲያጣ የሚደረግበት ዕድል አለ:: ስለይርጋና ስለምህረት ወይም ይቅርታ በተመለከተዉ ሁኔታ ዐቃቤህግ ክስ አላቀርብም የሚል ዉሳኔ ሳይስጥ ቢቀርና ክስ ቢያቀርብ ክሱ በመቃወሚያ ቀሪ ሊደረግ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 130(2)(ሐ))::

በሌላ በኩል ሊገኝ በማይችል ወይም ክሱ በሌለበት ሊታይ በማይችል ሰዉ ላይ ክስ ቢቀርብ ነገርን ተከሳሽ በሌለበት የማየት ነገር በህግ በዝርዝር የተደነገገ ስለሆነ ፍርድ ቤት በዚህ መሰረት ክሱን ቀሪ ሊያደርግዉ ይችላል ተብሎ ይገመታል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 160 እና ተከታዮቹ):: ነገር ግን አሁን ካለዉ የአሰራር ልምድ እንደምናየዉ ይህ አይነቱ ዝርዝር መጠባበቂያ ሥራ ላይ ሲዉል አይታይም:: ስለዚህ ዐቃቤህግ በንደዚህ አይነት ሰዎች ላይ ክስ ላለማቅረብ ባለዉ ሥልጣን መሰረት ካልሰራበት በማይገኙ ሰዎች ላይ በሚቀርቡ ክሶች ምክንያት የሰዎች መብት ከመጎዳቱም በላይ የህግ ማስፍጸምን አቅም የሚጎዳ ተግባር እንዲፈጸም ይሆናል:: ያልተገኘ ሰዉ መጠራቱን ሊያዉቅ አይችልም:: መጠራቱን ሳያዉቅ በሌለበት ክሱ ተሰምቶ ከተወሰነ ይህ ፍርድ በመጨረሻ ቀሪ ሆኖ ተከሳሹ ባለበት ክሱ እንዲሰማ ሊደረግ ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 199(ሀ))። ስለዚህ የተሰራዉ ስራ ሁሉ ከንቱ ይሆንና ይህ ስራ የተሰራበት ጊዜ ሌላ ፍሬያማ ስራ ሊሰራበት ሲችል ባክኖ ይቀራል::

ማሳያ

በወንጀል ምርመራ ጊዜ ቃሉን ያልሰጠ ተጠርጣሪን ጉዳይ የያዘ ሪፖርት ቀረበልዎ። ነገሩን ሲመረምሩት ተከሳሹ በምርመራ ጊዜ ተፈልጎ ስላልተገኘ አልተያዘም፣ ስለተከሰሰበት ወንጀልም አልተጠየቀም። ሆኖም የተሰበሰበዉ ማስረጃ የተመረመረዉን ወንጀል ለማስረዳት በቂ ነዉ። በዚህ ነገር ላይ የሚሰጡትን ዉሳኔ ይጻፉትና ከባልደረባዎ ዉሳኔ ጋር እያነጻጸሩ ይከራከሩበት።

ተከሳሽ ሊገኝ አለመቻሉን እንዴት ማወቅ ይቻላል? በመርመራ ጊዜ ያልተገኘ ሰዉ (ከምርመራዉ በኋላ ካልተገኘ በቀር) ሊገኝ የማይችል ሊባል ይችላል። በምርመራ ጊዜ የተገኘ ሰዉ በዋስ ስለሚለቀቅ ክስ ሊቀርብበት ይችላል። ሆኖም ይህ ሰዉ በፍጹም ይገኛል ማለት ላይሆን ይችላል። ከምርመራ በኋላ በተለያየ ምክንያት ሊገኝ በማይችልበት ሁኔታ ዉስጥ ሊገባ ይችላል። በዚህ ጊዜ ሊደረግ ስለሚገባዉ ነገር ዐቃቤህግ ህግጋትን ልቅም አድርጎ ማወቅ ይገባዋል። በዚህ ህግ መሰረት መሥራት አለበት። ይህን ጭብጥ በክስ ማሰማት ጊዜ ዐቃቤህግ ሊኖረዉ የሚገባዉን ክህሎት አስመልክቶ በሚደረገዉ ዉይይት ላይ እናነሳዋለን። ለአሁኑ ግን ዐቃቤህግ ተከሳሽ በማይገኝበት ሁኔታ ክስ አላቀርብም የማለት ሥልጣን ስላለዉ ይህን በመተግበር የህግ ማስፈጸም ብቃትን መንከባከብ እና ህግን የመጠበቅ ኃላፊነቱን መወጣት እንዳለበት አጽንዖት በመስጠት ወደሌሎች ጭብጦች እናልፋለን።

ቀዳሚ ምርመራ

ክክስ መሰማት በፊት ዐቃቤህግ ከሚፈጽማቸዉ ከምርመራ ወይም ማስረጃ ከመሰብሰብና መጠበቅ ጋር የተያያዙ ተግባራት ዉስጥ ቀዳሚ ምርመራ በሚያደርግ ፍርድቤት ማስረጃን ማስመዝገብ አንዱ ነዉ። ሆኖም ይህ ሥነሥርዓት በማስረጃ አጠባበቅ ረገድ ካለዉ ከፍተኛ ጥቅም አኳያ በእጅጉ የተዘነጋ ዘዴ ሊባል የሚችል ነዉ።

ዘወትር እንደሚስተዋለዉ ምስክሮች ሲጠፉ ዐቃቤህግ የሚወስደዉ ርምጃ ምስክሮች በፖሊስ ጣቢያ የሰጡት ምስክርነት ጽሁፍ በማስረጃነት እንዲቀርብ መጠየቅ ነዉ። ነገር ግን ይህ ጽሁፍ ፍርድቤት የሚቀርበዉ ምስክር ሲጠፋ ሳይሆን ምስክር ፍርድቤት ቀርቦ እየመሰከረ ባለበት ሁኔታ በመሆኑ እንዲህ አይነቱ ጥያቄ ነገሮችን በጥብቅ በሚመረምር ችሎት ፊት ዋጋ አይኖረዉም። በቀላሉ በሚቀበሉ ችሎቶችም ዘንድ አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር እንደማስረጃ ሊወስዱት አይታይም። በማስረጃነት የሚወስዱትም ቢሆኑ ከፍ ያሉ የህገመንግሥት መርሆችን በመጣስ ስለሚሆን ከፍ ያለ አደጋ አለዉ - የሰዉን መብት ይጥሳል።

መወያያ

ምስክሮች ሳይገኙ ሲቀሩ ዐቃቤህግ ለፍርድቤት የሚያቀርበዉን ሌላዉን ጥያቄና ፍርድቤት በዚህ መሰረት የሚሰጠዉ የተለመደ ትዕዛዝ ምን እንደሆነና የዚህን ጥያቄና ትዕዛዝ ህጋዊነት ከባልደረባዎ ጋር ይመርምሩ ይወያዩበት።

ምስክር መቅረብ ሳይችል ሲቀር በሌላ ቦታ የተሰጠ የምስክረነት ጽሁፍ በማስረጃነት (ምስክርን ተክቶ) ሊቀርብ የሚችለዉ በቀዳሚ ምረመራ ጊዜ የተመዘገበ ሲሆን ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 144)። በአሁኑ ጊዜ አዘዉትሮ ከሚታየዉ የምስክሮች አለመገኘት ችግር አኳያ የምስክርነት ቃላቸዉ ራሱን የቻለ ማስረጃ ሆኖ በሚቀርብበት ሁኔታ ተመዝግቦ መገኘቱ የማይታለፍ አማራጭ ነዉ። ፍርድቤቶች ይህን አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበት ወይም የሚገደዱበት ከአሁን የተሻለ ጊዜ አይኖርም ለማለት ያስደፍራል።

ቀዳሚ ምርምራ በከባድ ነፍስ ግድያ ወይም ከባድ ዉንብድና ወንጀሎች ካልሆነ በቀር ዐቃቤህግ ሳያገዝ ሊከናወን አይችልም (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 80)። በነዚህ ከባድ ወንጀሎች ጊዜም ቢሆን ዐቃቤህግ ቀዳሚ ምርመራ ሳይደረግ ነገሩ በቀጥታ መሰማቱ እንዲጀምር ሊጠይቅና ሊፈቀድለት ይችላል። ስለዚህ ይህ አሰራር ከሞላጎደል በሙሉ በዐቃቤህግ ዉሳኔ የሚከናወን ነዉ። ለዐቃቤህግ ደግሞ በምስክሮች መጥፋት የሚደርስበትን የማስረጃ መባከን መከላከል እጅግ አስፈላጊ ከሚባሉት ተግባሮቹ ዉስጥ የሚመደብ ነዉ። ስለዚህ የወንጀል ምርመራ በምርመራ ክፍሎች ተከናዉኖ ሲያበቃ ዐቃቤህግ ይህን የቀዳሚ ምርመራ የህግ ተቋም አዘዉትሮ ሊሰራበት ይገባል።

ክስ ስለመመስረትና ተያያዥ ጉዳዮች

ከላይ የተመለከቱት ተግባራት ካልተፈጸሙ ዐቃቤህግ ክስ የማቅርብ ግዴታ አለበት። ይህም ከክስ መሰማት በፊት ከሚፈጸሙ ተግባራት ዉስጥ ይመደባል። ይህም የሚፈጸምበት ጊዜና ቦታ አለዉ። እነዚህ ሁኔታዎች በህግ ተደንግገዋል። ዓላማቸዉም ለተከሰሰዉ ሰዉ ሚዛናዊ መሆንን እና በፍጥነት ለፍርድ መቅረብና በጉዳዩ ላይ ፍርድ የማግኘት መብቱን እንዲጠበቅ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ነዉ።

ክስ የሚቀርብበት ጊዜና ቦታ (ፍርድቤት)፦ በተገቢ ፍጥነት ፍርድ ከማግኘት መብት አኳያ ክስ የሚቀርብበት ጊዜ ሊወሰን ይገባል። ከዚህ የተነሳ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 109 የክስ ማቅረቢያ ጊዜ አስራ አምስት ቀን ነዉ። እንደህግ ጠባቂ ዐቃቤህግ ይህን ጊዜ ማክበር ይኖርበታል። ሆኖም ይህ ጊዜ አዘዉትሮ ሲጣስ ይስተዋላል። ይህ ጥሰት ሊዘወተር የቻለዉ በቅድሚያ ተቋሙ ካለበት የሥራ ጫና የተነሳ እንደሆነ ይታሰባል። ሆኖም በቂ ጊዜ ባለበት አጋጣሚም ቢሆን የጊዜ ገደቡን ማሳለፍ ይስተዋላል። በተለይ ተጠርጣሪዉ በእስር ላይ የሚገኝ ከሆነ ይህ ሁኔታ የከፋ ዉጤት ይኖረዋል። ፍርድቤት የወንጀል ምርመራ ካበቃ በኋላ ተጠርጣሪን ወደማረፊያ ቤት ሲልክ ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ ቁጥጥር ስለማያደርግ የአስራአምስት ቀናት የክስ ማቅረቢያ ጊዜ በቀላሉ ሊጣስ ይችላል። ነገር ግን ይህ መጣስ መኖር አለመኖሩን ለማወቅ አይቻልም፤ ምክንያቱም

ዐቃቤህግ የአስራ አምስቱ ቀናት ጊዜ ካልበቃዉ ለምን እንደሆነ ለማስረዳት ፍርድቤት አይቀርብም::

ፍርድቤት የወንጀል ምርመራ ሲያበቃ የጊዜ ቀጠሮ መዝገብን መዝጋት አለበት? ክስ በጊዜ መቅረብ አለመቅረቡን ለማረጋገጥ ክስ ማቅረቢያ ለሆነዉ የአስራአምስት ቀናት ጊዜ መዝገቡን ሊቀጥረዉ አይገባም? በዚህ ጊዜስ ዐቃቤህግ በቀጠሮዉ ቀን ቀርቦ ክስ ያልቀረበበትን አሳማኝና በቂ ምክንያት ሊያስረዳ አይገባዉም? ዐቃቤህግ በተባለዉ ጊዜ ክስ ካላቀረበ ወይም ምክንያቱን ካላስረዳ ዐቃቤህግን ለማትጋት ተጠርጣሪዉ በእስር ላይ ከሆነ በዋስ እንዲለቀቅ ፍርድቤት ሊያዝዝ አይገባዉም? የእኩልነት መብት ይህ እንዲደረግ አይጠይቅም? በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤት የሙስና ወንጀሎች ችሎት የአሰራር ልምድ መሰረት በተገቢዉ ጊዜ ክስ ሳይቀርብ ከቀረና ተጠርጣሪዉ በእስር ላይ ከሆነ በዋስ ሊፈታ እንደሚገባዉ ይታመናል::

ክስ የት ይቀርባል? ይህን በተመለከተ የሥነሥርዓት ህግጋት የሚደነግጓቸዉ ነገሮች አሉ:: በወንጀል ህግ የተመለከቱትን ወንጀሎች የመዳኘት ሥልጣን ለተለያዩ የፍርድቤት ደረጃዎች መሰጠቱን የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ አንደኛ ሰንጠረዥ ያሳያል:: ስለዚህ ዐቃቤህግ የወንጀል ክስ ሲያቀርብ በአሰራር ለዉጥ መከራ መሰረት ከሚሰሩ የዐቃቤህግ መ/ቤቶች በቀር ያሉት ይህን ሰንጠረዥ ሊከተሉ ይገባል:: ሆኖም ይህ ሰንጠረዥ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተሻሽሏል:: ደንብ ቁ. 14/1967 የመጀመሪያዉ ነዉ:: የፌዴራል ፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 25/1988 በቀ. 4፣ 7፣ 8፣ 12፣ 15 እንዲሁም ይህን አዋጅ ያሻሻሉት አዋጅ ቁ. 138/1991፣ 321/1995፣ ወዘተ ሌሎቹ ናቸዉ:: ከነዚህ ሌላ የጸረ ሙስናን ልዩ የማስረጃና የሥነሥርዓት አዋጅ ማየት ይገባል:: በዚህ ረገድ ከክስ በፊትም ሆነ በክስ መሰማት ጊዜ የሙስና ወንጀሎችን ጉዳይ የማየት ሥልጣን በፌዴራል ጉዳይ የፌዴል ከፍተኛ ፍርድቤት፣ በክልል ጉዳይ የክልል ከፍተኛ ፍርድቤት እንደሆነ አዋጅ ቁ. 434/1997 ይደነግጋል::

እነዚህ ህግጋት የሥልጣን ክፍፍሉን የደለደሉት እንዲሁ ለይስሙላ አይደለም:: ከብቃት ጀምሮ ለሥራ መቀላጠፍ እስከሚያበረክተዉ አስተዋጽዖ ድረስ ያለዉን በማገናዘብ ነዉ:: ይህ ሥልጣን ከተደለደለ በኋላ ይህን ተከትሎ አለመስራት ሥልጣንን ከልክ አሳልፎ መሥራት ወይም ሥልጣንን ያለአግባብ መያዝ ሊሆን ይችላል:: እንዲህ አይነቱ ተግባር ወንጀል ነዉ:: ስለዚህ ፍርድቤቶች በሥልጣናቸዉ ስር የማይገቡ ወንጀሎች ክስ ሲቀርብላቸዉ ማሰናበት አለባቸዉ:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ ነገሮች ሥልጣን በሌላቸዉ ፍርድቤቶች በኩል አልፈዉ ተገቢዉ ፍርድቤት እስኪደርሱ ጊዜ፣ ጉልበት፣ ሃብት ይባክናል:: ይህም የሁሉንም ወገን የሥራ ብቃት ይጎዳል::

አንድን ጉዳይ በይግባኝ የማየት ሥልጣን ያለዉ ፍርድ ቤት ነገሩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ቢያየዉ ተገቢ ነዉ አይደለም የሚለዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የበላይ ፍርድቤት እንዲያየዉ የተደለደለን ጉዳይ የበታች ፍርድቤት እንዲዳኘዉ ቢደረግ ፍርድቤቱ ካለዉ ሥልጣን በላይ አልፎ

እንንዲሰራ መደረጉ የሚያጠያይቅ አይደለም:: ስለዚህ ዐቃቤህግ ክስ ሲያቀርብ እነዚህን ቁምነገሮች የሚገዙትን ህጎች በጥብቅ መከተል አለበት:: (*በተግባር በርካታ ክሶች ሥልጣን ለሌለዉ ፍርድቤት ሲቀርብ ይስተዋላል - በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአደንዛዥ ዕጽ ጉዳዮች በፌዴል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤቶች እንዲታዩ ሲቀርቡ ይስተዋላል*)

የሙስና ወንጀልን ጉዳይ መደበኛዉ ዐቃቤህግ ክስ አዘጋጅቶ ቢያቀርብበት ፍርድቤት ሥልጣን የለኝም ሊል ይችላል?

የት አካባቢ ያለ ፍርድቤት ክስ ሊቀርብለት ይገባል? ይህ ክልላዊ ሥልጣንን ይመለከታል:: የሥነሥርዓት ህጉ የወንጀል ክስ የሚቀርብለት ፍርድቤት ከላይ የተመለከትነዉ ሥልጣን ያለዉ ሆኖ ወንጀሉ የተፈጸመበት አካባቢ ፍርድቤት ሊሆን ይገባዋል ይላል (ቁ. 99) :: ይህም ወንጀሉ የተፈጸመበት ቦታ የት ነዉ የሚል ጥያቄ ይቀሰቅሳል:: ይህ ጥያቄ በአሁኑ የመንግሥት የሥልጣን አወቃቀር ሁኔታ የትኛዉ መንግሥት (ፌዴራል ወይስ ክልል፣ ከክልሎች የትኛዉ ክልል) በነገሩ ላይ ሥልጣን እንዳለዉ ለመወሰን ሰለሚረዳ መሰረታዊ ጥያቄ ነዉ::

በአንድ ቦታ ተጀምሮ የሚያልቅ ወንጀልን በተመለከተ ችግር ላይኖር ይችላል:: ሆኖም በአንድ ቦታ ተጀምረዉ በሌላ ቦታ የሚጠናቀቁ ወንጀሎች፣ ከአንድ ቦታ በላይ ተደጋግመዉ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ በጉዞ ላይ ወይም በተለዩ የመጓጓዣ መሳሪያዎች ላይ (ዉስጥ) የሚፈጸሙ ወንጀሎች ወዘተ ሲያጋጥሙ ከነዚህ ቦታዎች በየትኛዉ በሚገኝ ፍርድቤት ነገሩ ሊታይ እንደሚገባዉ መወሰን የግድ ይሆናል:: እነዚህን ሁኔታዎች የሚገዙ ድንጋጌዎች በወ/ህ/ቁ. 25 እና በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 99ና ተከታዮቹ ተመልክተዉ ይገኛሉ:: ከዚህም በቀር በተሻሻለዉ የጸረሙስና ልዩ የሥነሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ. 434/1997 በቁ. 7 የክልልና የፌዴራል ፍርድቤቶች ሥልጣን ተለይቶ ይገኛል:: በድሬዳዋና በአዲስ አበባ ዉስጥ የሚነሱ የወንጀል ጉዳዮች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ከተሰጡት በቀር በፌዴራል ከፍተኛ ወይም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤቶች ሥልጣን እንደሚታዩ አዋጅ ቁ 28/1988 በቁ. 12(2) እና 15(2) ደንግጎ ይገኛል::

ይህ ሁሉ ነገሩን በህግ ለመግዛት የተደረገ ጥረት ምን ያህል የፍርድቤቶች ሥልጣን ጉዳይ በቸልታ ሊታይ የማይገባዉ መሆኑን ያሳያል:: ስለዚህ በተለይ ከተፈቀዱ መተላለፎች (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 110) በቀር ዐቃቤህግ ክሱን በህግ ሥልጣኑ ለተሰጠዉ ፍርድቤት ማቅርብ አለበት፣ ይህ ካልሆነ ደግሞ ፍርድቤቶች ክሱ ሥልጣን ላለዉ ፍርድቤት እንዲቀርብ በማዘዝ መመለስ ይኖርባቸዋል:: ነገሩን በምንቸገረኝ ወይም በቸልታ ተቀብለዉ ማስተናገድ ከጀመሩ በኋላ ሥልጣን የለኝም ብሎ ማሰናበት ሊከሰት ይችላል:: የዚህ አሰራር አባካኝነት ደግሞ አያጠራጥርም፣ በሰዉ መብት ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት እንደተጠበቀ ሆኖ::

የክስ ቅርጽና ይዘት፡- የወንጀል ክስ ማቅረቢያ ፎርም አለዉ:: በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ ሁለተኛ ስንጠረዥር የተመለከቱት የተለያዩ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ናሙናዎችን በመከተል ክስ ሊቀርብ ይገባል (ቁ. 111(2)):: በዚህ መሰረት ክሱ ቀንና ፊርማ፣ የተከሰሰዉን ሰዉ ስም፣ የተፈጸመዉን ወንጀል ዝርዝር፣ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ቦታ፣ የተጎጂዉን ሰዉ ስም ወይም የንብረቱን ምንነት፣ ክስ በቀረበበት ተግባር የተጣሰዉን ህግ ከነቁጥሩ ሊይዝ ይገባል::

በተለይ የተፈጸመዉ ወንጀል ዝርዝር ሲገለጽ ተግባሩን ወንጀል ነዉ ብሎ ከደነገገዉ ህግ አነጋገር ጋር ተቀራራቢ ሊሆን የግድ ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 112):: ተከሳሹ የተከሰሰበትን ነገር እንዲያዉቀዉና ተገቢዉን መልስ መስጠት እንዲያስችለዉ ጣስክ የተባለዉ ህግ የሚናገረዉና ህጉን ጣስክ የተባለበት ክስ የሚናገረዉ በጣም ተቀራራቢ ሊሆን ይገባዋል:: ሁለቱ የተጣጣሙ ካልሆኑ ተከሳሹ ለየትኛዉ መልስ እንደሚሰጥ ሊቸገር፣ የትኛዉን በተመለከተ (ህጉን ወይስ የክሱን ዝርዝር) መከላከያ እንደሚያቀርብ ሊቸገር ይችላል::

እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲከሰት ክስ የማስተካከል ነገር አስፈላጊ ሊሆን ስለሚችል የሥራ መስተጓጎል ስለዚህም የሰዉ መብት መጎዳት ሊከሰት ይችላል::

አዘዉትሮ የሚከሰተዉ የክስ አቀራረብ ችግር ይህን የተመለከተ ነዉ:: ይህንንም መሰረት በማድረግ የክስ መቃወሚያ እየተነሳ ክስ እንዲሻሻል ሲታዘዝ ይታያል::

ሌላዉ የዘወትር ችግር ጊዜና ቦታን በበቂ ሁኔታ ያለመግለጽ ነዉ:: የዚህ ዝርዝር አለመገለጽ ተከሳሹን የመከላከል ችሎታዉን ያላግባብ ያጣብባል:: አንዳንድ መከላከያዎች በባህሪያቸዉ ከጊዜና ከቦታ ጋር የተያያዙ ናቸዉ:: ለምሳሌ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በወንጀሉ ቦታ አለመኖር አዘዉትሮ የሚቀርብ መከላከያ ነዉ::

የክስ ይዘትን በተመለከተ ሊነሱ የሚችሉ ሌሎች በርካታ ክህሎትን የሚመለከቱ ነጥቦች አሉ:: ከነዚህ ዉስጥ ክስን በአማራጭ የማቅረብ ነገር አንዱ ነዉ:: ይህም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 113 መሰረት የሚፈጸም ነዉ:: በርግጥ ዐቃቤህግ አማራጭ ክስ ባያቀርብም ፍርድቤት ራሱ በማስረጃ በተረጋገጠዉ ወንጀል ጥፋተኛ የማለት ሥልጣን አለዉ:: ነገር ግን ይህ አሰራር በህግ የተመለከቱ መመዘኛዎችን መሰረት አድርጎ የሚፈጸም በመሆኑ አንዳንድ ፍርድቤቶች እነዚህ መመዘኛዎች ካልተሟሉ በቀር ክስ የቀረረበበትን ወንጀል መረጋገጥ አለመረጋገጥ ብቻ መርምረዉ የጥፋተኝነት ወይም በነጻ የማሰናበት ሥራ ይሰራሉ:: ስለዚህ አማራጭ ክስ ቀርቦ ካልሆነ በቀር ማስረጃዉ በሚያረጋግጠዉ ወንጀል ጥፋተኛ የማለት ነገር ላይፈጸም ይችላል::

አማራጭ ክስ ባይቀርብም ማስረጃ ባረጋገጠዉ ወንጀል ጥፋተኛ ማለት የሚቻልባቸዉ መመዘኛዎች የሚከተሉት ናቸዉ:: አንዱ ይህ ወንጀል ክስ ከቀረበበት ወንጀል ወገን መሆን ይኖርበታል (ለምሳሌ - ቀላል ነፍስግድያ የተራ ነፍስ ግድያ ወገን ነዉ)፣ እንዲሁም ክስ ከቀረበበት ወንጀል ያነሰ ወንጀል መሆን አለበት:: ሌላዉ መመዘኛ ደግሞ ይህን በማስረጃ የተረጋገጠዉን ወንጀል ራሱን ችሎ ቢቀርብ ፍርድ ቤቱ ሊያየዉ ሥልጣን ያለዉ መሆን

ይኖርበታል:: እነዚህ መመዘኛዎች ተሟልተዉ ካልተገኙ በቀር አማራጭ ክስ ባልቀረበበት ወንጀል ጥፋተኛ የማለት ሥራ ሊፈጸም መቻሉ አጠራጣሪ ነዉ:: በዚህ ሁኔታ በማስረጃ የተረጋገጠዉን ተግባር ሁሉ መሰረት አድርገዉ የጥፋተኛነት ዉሳኔ የሚሰጡ ፍርድቤቶች የዐቃቤህግን ትጋት ከማዳከምና ያለሥልጣን መስራትን ከማበረታታት ብሎም የሰዉን መብት ከመጉዳት በቀር ሥራቸዉ ቁምነገር ያለዉ ሊሆን አይችልም::

ስለዚህ ዐቃቤህግ እንደዚህ አይነቱን መዘናጋት በማስወገድ ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ ፍጹም ርግጠኛ ከሆነባቸዉ ጉዳዮች በቀር በሌሎች ጉዳዮች በክሱ ዉስጥ አማራጭ ክስ ማካተትን ማዘዉተር ይኖርበታል::

ሌሎች መረጃዎች:- ተከሳሽ ከክሱ በፊት ታስሮ ስለቆየበት ጊዜ መረጃ ማግኘት ለፍርድቤት በእጅጉ ያስፈልገዋል:: በወንጀል ህግ ቁ. 116 እንደተመለከተዉ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በተከሰሰበት ነገር ከፍርድ በፊት ታስሮ የቆየዉን ጊዜ አስልቶ ከተወሰነበት ቅጣት ላይ እንዲቀነስ ታዝዟል:: ለዚህ ደግሞ የታሰረዉን የጊዜ መጠን ማወቅ አለበት:: ይህ መረጃ ከፖሊስ ምርመራ ሪፖርት ሊገኝ ይችላል::

መወያያ *ዐቃቤህግ ክስ ሲያቀርብ ስለምርመራ ክፍሉና ስለምርመራ መዝግብ ወይም ሪፖርት በክስ ማመልከቻዉ ላይ እንደሚገልጸ የታወቀ ነዉ:: አንዳንድ ጊዜም ተከሳሹ በእስር ላይ እንደሚገኝ በማመልከቻዉ ግርጌ ይገልጻል:: ሆኖም ይህ በህግ የተጣለ ግዴታ አይደለም:: ለፍርድቤቱ መረጃ ለመስጠት ታስቦ የሚደረግ ነዉ:: ይህ ከሆነ ተከሳሹ ክስ ለመስማት እስኪቀርብ ድረስ የታሰረዉ ካለዉ ይህን የሚገልጸ ወይም ቢያንስ ይህን ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎች የሚገኙበትን ምንጭ የሚገልጸ መረጃ በክስ ማመልከቻዉ ላይ ቢገልጸ ተገቢ አይሆንም?*

ማስረጃን ስለማያያዝ:- በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ የሚቀርብበትን ማስረጃ የማግኘትና የማየት መብት አለዉ (ህገመ. ቁ. 20(4)):: ስለዚህ ዐቃቤህግ የክስ ማመልከቻ ሲያዘጋጅ ሊያደርግ ከሚገባዉ ነገር ዉስጥ አንዱ የሚያቀርባቸዉን ማስረጃዎች ለተከሳሹ እንዲደርሱት ከክስ ማመልከቻዉ ጋር ማያያዝ ነዉ:: በአሁኑ ጊዜ ዐቃቤህግ ከቀድሞዉ በተለየ ሁኔታ የሰነድ ማስረጃዎችን ቅጂ እና የምስክሮችን ዝርዝር ከክስ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ያቀርባል::

መወያያ *በሙስና ጉዳዮች የሚቀርቡ ክሶችን የሚያስተናግደዉ ፍርድቤት ዐቃቤህግ የማስረጃዉንና የክሱን መግለጫ ሲያቀርብ ከምስክሮች ዝርዝር በተጨማሪ የሚመሰክሩትን ጭብጥ እንዲዘረዝር ይጠይቀዋል:: ዐቃቤህግም በዚህ አይነት ዝርዝር ሲያቀርብ ይስተዋላል:: መደበኛዉ ዐቃቤህግ*

በዚህ አይነት ከክሱ ጋር የምስክሮችን ዝርዝር ብቻ ሳይሆን የሚያስረዱትን ጭብጥ ዘርዝሮ ቢያቀርብ ተገቢ አይሆንም? ከባልደረባዎ ጋር ይወያዩበት።

3. የክስ መሰማትና የዐቃቤህግ ክህሎት

ከላይ በተጠቀሱት ከክስ በፊት በሚከናወኑ የምርመራና የክስ ዝግጅት ሥራዎች አማካኝነት ክስ ከቀረበ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ክስ መስማት ነዉ። ለዚህም ተከሳሹ እንዲቀርብ ተደርጎ ክሱ በችሎት ይነበባል፣ ተከሳሽ ስለቀረበበት ክስ ምን እንደሚል ይጠየቃል። ተከሳሽ መቃወሚያ በክስ አቀራረቡ ላይ ሊያነሳ ይችላል። በዚህ መሰረት ክሱ እንዲስተካከል የሚያደርግ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል። ሆኖም የክሱን አቀራረብ በተመለከተ ክርክር ካልቀረበ ወይም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130(2) ስር የተመለከቱት መቃወሚያዎች ካልተነሱ ዕምነት ክህደት ይቀርባል። ወንጀሉ ከታመነ ጥፋተኛነት ይወሰናል ወይም ማስረጃ መስማት ይከናወናል። ከተካደ ግን ማስረጃ መስማት የግድ ነዉ።

ሆኖም ነገሩ ሁልጊዜ በዚህ አይነት ይፈጸማል ማለት አይደለም። ነገሩን ባጭሩ ዳር ለማድረስ የሚያስችል ሁኔታ ቢኖርም አንዳንድ ጊዜ የዐቃቤህግ ጥያቄዎች ነገሩን ወደአዲስ አቅጣጫ የሚያዞሩበት አጋጣሚ ይስተዋላል። ይህም በተለይ ከክስ ማሻሻል ጋር የተያያዘ ነዉ።

ስለክስ መሻሻል

የክስ መሻሻል ጥያቄ የሚነሳዉ መቼ ወይም ምን ሲኖር ነዉ? የክስ መሻሻል ነገር አስፈላጊ የሚሆነዉ ስለወንጀሉ ዝርዝር ሁኔታ የተሳሳተ ወይም የጎደለ ነገር ሲኖር ነዉ። በተለይ ይህ ጉድለት ወይም ስህተት ተከሳሹን ያሳሳተ እንደሆነ ወይም ትክክለኛ ፍርድ ከመስጠት የሚያስተጓጉል ከሆነ ክሱን ዋጋ ሊያሳጣዉ ስለሚችል ይህ ስህተት ወይም ጉድለት ካልታረመ እንደክስ ሊሰማ አይችልም።

ይህ ክስ የመለወጥ ሥራ እንዲከናወን ፍርድቤት የማንንም ጥያቄ አይጠብቅም። ራሱ ችግሩ መኖሩን ከተገነዘበ ክሱ እንዲሻሻል ሊያዝዝ ይችላል። ወይም ጥያቄ ሲቀርብለት ይህን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

መወያያ

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 119 መሰረት ክስ ለመለወጥ (ለማሻሻል) ዐቃቤህግ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል? ከባልደረቦችዎ ጋር ሆነዉ ይከራከሩበት።

በክስ ዉስጥ ያለን ስህተት ወይም ጉድለት በመንቀስ ክስን የማስተካከል ነገር ዐቃቤህግ ስለክስ አቀራረብ ያለዉን ክህሎት የሚያዳብር አሰራር ነዉ:: ሆኖም ህግ በሚፈቅደዉ መሰረት ካልተሰራ በቀር የዐቃቤህግንና የፍርድቤትን የሥራ ብቃት ከመቀነስ ባሻገር የሰዎችን መብት ይጎዳል::
ዐቃቤህግ ከፍ ብሎ ባየናቸዉ መንገዶች ክሱን በበቂ እና በህግ በሚፈለገዉ አይነት አዘጋጅቶ ማቅረብ ይጠበቅበታል:: በዚህ አይነት የቀረበ ክስ በአቅራቢዉ በኩል የማስተካከል ጥያቄዎችን የሚጋብዝ መሆኑ ያጠራጥራል:: በተለይ የተከሰሰዉም ሆነ የከሰሰዉ ወገን እንዲሁም ፍርድቤት ስለብቃቱና ምሉዕነቱ የተስማሙበት ክስ ነገሩ መሰማቱን ቀጥሎ ባለበት ጊዜ እንዲስተካከል ጥያቄ ማንሳት ተመራጭ አካሄድ አይሆንም::
የቼክ ጉዳይ ምሳሌ... *በአንድ ሰዉ ላይ በብዙ ቼኮች የተፈጸመን ማታለል ዐቃቤህግ በአንድ ክስ ካቀረበዉ እና ክሱ ተነቦ ተከሳሽ ወንጀሉን ክዶ ዐቃቤህግ ማስረጃ በሚያቀርብበትና ምስክር በቀረበበት ጉዳይ ብዙ ክሶች አድርጎ ክሱን ለማሻሻል በዐቃቤህግ ጥያቄ ስለቀረበ በዚሁ ክርክር ተደረገ፣ የክሱ መሰማት ፈፉን ለቆ እንዳዲስ ስለክስ መሻሻል ወይም አለመሻሻል ጉዳይ ሆነ:: በዚህ ጥያቄ ላይ ለመወሰን ቀጠሮ ተያዘ:: መስክሩ በዚህ ቀጠሮ እንዲቀርብ ተነግሮት ተመለሰ::*
ሆኖም ክሱ መጀመሪያዉኑ በከሳሹ ወገን ፣ በፍርድቤት ፣ በተከሳሽ - በሁሉም በሚያገባቸዉ ወገኖች ሁሉ የተሟላ ስለመሆኑ ይሁንታ አግኝቷል:: ከዚህ በኋላ ወደክስ መሻሻል መግባት የዐቃቤህግን ፣ የፍርድቤትን ፣ የተከሳሽን እና የምስክሮችን ጥቅም የመጉዳት ዉጤት ይኖረዋል::

ማሳያ *ርስዎ ጽፈዉ ባቀረቡት የወንጀል ክስ ሊከራከሩ ችሎት ቀርበዋል:: ተከሳሹ ቀርቦ ክሱን ከሰማ በኋላ የክሱን ፎርምና ይዘት አስመልክቶ መቃወሚያ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 130(1) መሰረት አቀረበ:: ችሎቱም እንደተለመደዉ በዚህ ነገር ላይ ያለዎትን ክርክር ጠየቀ:: ለፍርድቤቱ የሚሰጡት መልስ ምንድን ነዉ? ስለቀረበዉ መቃወሚያ መልስ ይሰጣሉ፣ መልስ ለመስጠት ቀጠሮ ይጠይቃሉ ወይስ ይህ የፍርድቤቱ ስራ ስለሆነ ተገቢ ነዉ የሚለዉን ትዕዛዝ ይስጥ ብለዉ ያመለክታሉ? ዐቃቤህግ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 131(1) ስር ከተሰጠዉ ሚና አኳያ ይመርምሩት፣ ከባልደረባዎ ጋር ይከራከሩበት::*

በክስ ተቃዉሞ ጊዜ የዐቃቤህግን ሚና በተመለከተ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130 ስር የተደነገገዉን ካየን ከክስ መሻሻል ጥያቄ ጋር ብዙም ቁርኝት እንደሌለዉ እንገነዘባለን:: ዐቃቤህግ በመቃወሚያ ጉዳይ ሊከራከር የሚችለዉ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130(2) ስር ያሉት መቃወሚያዎች ሲነሱ ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 131(1))። በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130(1) የተደነገገዉ አይነት የክሱን ፎርምና ይዘት በተመለከተ የሚቀርብ መቃወሚያ ካለ ፍርድ ቤት ስለክስ ስህተትና ጉድለት እና

ስለሚታረምበት ወይም ስለሚስትካከልበት ሁኔታ በሚደነግጉት የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 119 ና ተከታዮቹ መሰረት ይወስናል:: ዐቃቤህግ በዚህ አይነት መቃወሚያ ጊዜ ክርክር ማቅረብ መቻሉ አጠራጣሪ ነዉ:: ለፍርድቤቱ በቀረበ የክስ ማመልክቻ ላይ የቀረበ መቃወሚያ በመሆኑ ፍርድቤቱ ይህን ከህግ ጋር አገናዝቦ ለመወሰን ከዐቃቤህግ ሊሰማ የሚሻዉ ተቃራኒ ክርክር አይኖርም:: በተለምዶ ግን በክሱ ፎርምና ይዘት ላይ ለሚቀርብ መቃወሚያ ዐቃቤህግ ክርክር እንዳለዉ በፍርድቤቶች ሲጠየቅና ዐቃቤህግም ይህን በመቀበል መልሰ ለመስጠት ቀጠሮ በመጠየቅ በዚህ ነገር ላይ ለመወሰን ተገቢ ያልሆነ ጊዜ ሲወሰድ ይስተዋላል:: ጊዜ ባለፈ ቁጥር ክሱ እየተጎዳ ተከሳሽ እየተጎዳ ይሄዳል:: ነገሩ በተገቢ ፍጥነት አይቋጭም፣ በጊዜ ርዝማኔ ምስክሮች መኖሪያ የመቀየር የመሞት የመጥፋት ወዘተ አጋጣሚ ሊከሰትና ማስረጃ የማጣት አደጋ ይፈጠራል::

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 130(2) መሰረት የሚቀርብ መቃወሚያ ካለ ዐቃቤህግ እንዲከራከር ይጠየቃል:: እነዚህ መቃወሚያዎች የሚመለከቷቸዉ ነገሮች ከፍርድቤቱ ዉጪ የሚገኙ ዕዉነታዎችን የሚመረኮዙ ስለሆነ ዐቃቤህግ የሚያቀርበዉ ክርክር ዕዉነቱ ምን እንደሆነ ለመለየት ይረዳል:: ስለዚህ ህግ አዉጪዉ ዐቃቤህግ በዚህ ጉዳይ እንዲከራከር ፈቅዶለታል።

የዕምነት ክህደት ክርክር

ተከሳሽ ዕምነት ክህደት ተጠይቆ ከመለሰ በኋላ ወንጀሉን ፈጽሜያለሁ የሚል ከሆነ ዐቃቤህግ አዘዉትሮ ተከሳሹ ባመነዉ መሰረት ጥፋተኛ ይባልልኝ በማለት ይጠይቃል:: ሆኖም የተከሳሹ መልስ መብትን በመጠበቅ የሚሰጥ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ክስ ከቀረበበት ወንጀል ያነሰን ወንጀል የሚያምን ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ የዐቃቤህግ ጥያቄ ጥፋተኛነቱ በዚህ መልስ ልክ እንዲሆን የሚጠይቅ በመሆኑ ፍርድቤት በዚሁ መሰረት ሊወስን ይገባል፣ በንዝህላልነት ወይም በቸልታ ክስ በቀረበበት ወንጀል ጥፋተኛነት የሚወስን ፍርድቤት ካልሆነ በቀር:: ከዚህ የተነሳ ዐቃቤህግ በዕምነት ክህደት ላይ የሚያቀርበዉ ማመልከቻ የተሰጠዉን ዕምነት ክህደት ይዘት በሚገባ ያጤነ እና ለዚሁ ተስማሚ የሆነ እንዲሆን ይጠበቃል::

ቀጠሮ

ክሱ እንከን የሌለበት ከሆነ እንደተከሳሹ ክርክር ወይ የጥፋተኛነት ዉሳኔ ይሰጣል፣ አለያም ከፍርድ በፊት ማስረጃ ይሰማል:: ማስረጃ መሰማት ካለበት ዐቃቤህግ ሊያከናዉናቸዉ ከሚገቡ ነገሮች አንዱ ምስክሮቹን እና ሌሎች ማስረጃዎችን ነገሩ በሚሰማበት ጊዜና ቦታ እንዲገኙ ማድረግ ነዉ:: ራሱም መገኘት ይኖርበታል::

የዐቃቤህግ አለመቅረብና ቀጠሮ

ምስክር ወይም ሌላ ማስረጃ ባይቀርብ፣ ዐቃቤህግም ባይቀርብ ፍርድቤቶች ሲያደርጉ የሚታየዉ ወይ መዝገቡን ዘግተናል ብሎ ለመዝገብ ቤት መመለስ ነዉ ወይም ቀጠሮ መለወጥ ነዉ:: ቀጠሮ ማድረግ የተከለከለ አይደለም:: ሆኖም በህግ በተመለከቱ ምክንያቶች ካልሆነ በቀር ቀጠሮ ሊሰጥ አይችልም (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 94):: ዐቃቤህግ ወይም ምስክሮች ሳይቀርቡ ከቀሩ ቀጠሮ ሊለወጥ ይችላል:: ሆኖም ዐቃቤህግ በቂ በሆነ ምክንያት መቅረቱ ካልታወቀ በቀር ቀጠሮ አይለወጥም:: ተተኪ ዐቃቤህግ ባለበት ነገሩ የተቀጠረበት ሥራ ሊከናወን ይገባል::

መወያያ

ዐቃቤህግ በበቂ ምክንያት መቅረቱ ካልተረጋገጠ ቀጠሮ አይለወጥም ሲባል መዝገቡ ይዘጋል ማለት ነዉ?

ዐቃቤህግ በበቂ ምክንያት መቅረቱን ማረጋገጥ የሚችለዉ መቼ ነዉ በዕለቱ ወይስ በሚቀጥለዉ ቀጠሮ?

ከዚህ የቀጠሮ ድንጋጌ የምንገነዘበዉ ዐቃቤህግ በቀጠሮ መቅረት እንደሌለበት፣ የሚያስቀረዉ በቂ ምክንያት ካለዉ ይህንኑ ቢያንስ ለራሱ መሥሪያ ቤት በዕለቱ ማሳወቅ እንዳለበት (ምክንያቱም ከዚህ በኋላ መ/ቤቱ ይህንኑ መረጃ ለፍርድቤት በማቅረብ በቂ መሆን አለመሆኑን ያስወስናል ወይም ተተኪ ዐቃቤህግ እንዲቀርብ ያዝዛል)፣ ከተቻለ ደግሞ ይህንኑ ለፍርድቤቱ ማሳወቅ እንዳለበት ነዉ፡፡ ይህ ካልተደረገ ፍርድቤት በዕለቱ እንዲከናወን የተቀጠረዉን ጉዳይ ለሌላ ቀጠሮ እንዳያስተላልፍ የቀጠሮ ድንጋጌዎቹ ያስገድዱታል፡፡

ስለዚህ ዐቃቤህግ ቀጠሮ ማክበር ካልቻለና በቀጠሮዉ ዕለት ተገቢዉ ሥራ ካልተሠራ የዚህን በቂ ምክንያት ማስረዳት ይገባዋል:: የቀጠሮ ድንጋጌዎች ጥብቅ ናቸዉ:: ለዚህ ምክንያቱ ነገሮች በተገቢዉ ፍጥነት ዕልባት እንዲያገኙ የሚጠይቀዉን መርህ ያለመንዛዛት ለመተግበር ነዉ::

የተከሳሽ አለመቅረብና ቀጠሮ

ተከሳሽ ሳይቀርብ በሚቀርበት ጊዜ ስለሚፈጸመዉ ሥነሥርዓት በህግ ተደንግጎ ይገኛል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 94(2)(ሀ)፣ 125፣ 160 እና ተከታዮቹ):: በበቂ ምክንያት መቅረቱ ከታወቀ ቀጠሮ ሊለወጥ ይችላል:: ይህም መጠራቱን ማወቁን ይጠቁማል:: መጠራቱን አዉቆ ባልታወቀ ምክንያት ከቀረ ተይዞ እንዲቀርብ ይደረጋል:: ይህ የማይሳካ ከሆነ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት ለመታየት የሚያስችሉ መመዘኛዎችን የሚያሟላ መሆን አለመሆኑ ተመርምሮ ይወሰናል::

መወያያ

ተከሳሽ ተፈልጎ ሊገኝ አልቻለም። የተከሰሰበት ወንጀል የቅጣቱ መነሻ 15 ዓመት ነዉ። ፍርድቤት ዐቃቤህግን በዚህ ላይ እንዲያመለክት ጠየቀዉ። ዐቃቤህጉ እርስዎ እንደሆኑ በማሰብ የሚያመለክቱትን ነገር በጽሁፍ ያስፍሩት። ስለተገቢነቱ ከባልደረባዎ ማመልከቻ ጋር እያነጻጸሩ ይከራከሩ።

ከላይ በተመለከተዉ ጉዳይ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ በመቅረቱ ተይዞ እንዲቀርብ የተሰጠዉን ትዕዛዝ ተከሳሹ ሊገኝ ባለመቻሉ ምክንያት ለመፈጸም አልተቻለም። ፍርድቤቱ የርስዎን ሃሳብ ጠየቀ። የሚያመለክቱት ነገር ከላይ ካመለከቱት ይለያል? ከባለደረባዎ ጋር ተከራከሩበት።

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ከ5-20 ዓመት በሚያስቀጣ ወንጀል ዙሪያ እንደተከሰቱ በማሰብ ተገቢዉን ማመልከቻ ለፍርድቤት ያቅርቡ። ስለተገቢነቱ ከባልደረቦችዎ ማመልከቻዎች ጋር በማነጻጸር ተወያዩ።

በአሰራር ልምድ እንደሚታየዉ ዐቃቤህግ መጥሪያ ያልደረሰዉ ተከሳሽም ጭምር ነገሩ በሌለበት ይታይልኝ እያለ መጠየቁና ፍርድቤትም መፍቀዱ የተለመደ ነዉ። ዐቃቤህግ የህግ ጠባቂ ከመሆኑ አኳያ ከላይ የተመለከቱት ህግጋት በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸዉን መከበራቸዉን መቆጣጠር ይገባዋል። ስለዚህ ራሱ ሊጥሳቸዉ ወይም እንዲጣሱ በር መክፈት የለበትም። እነዚህ ህግጋት የተከሳሹን የመከላከል መብት ለመጠበቅ የተደነገጉ ናቸዉ። ተከሳሽ ክሱን ለመከላከል በግንባር የመገኘት መብት አለዉ (በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 127)። ለዚሁ ተጠርቶ መቅረብ አለበት ፤ ከዚህ በኋላ መቅረብ ካልፈለገ ነዉ መብቱን ሊሰራበት እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ነገሩ በሌለበት የሚታይ ከሆነ በሌለበት እንዲታይ መደረግ ያለበት። ህግጋቱ በጥብቅ ስራ ላይ ሊዉሉ የሚገባቸዉ ናቸዉ። ምክንያቱም በጥንቃቄ ካልተተገበሩ ፤ ተከሳሽ ሳይገኝ በቀረ ጊዜ ሁሉ ነገሩ በሌለበት እንዲታይ እየተደረገ በመጨረሻ ነገሩ እንዳዲስ ተከሳሽ ባለበት መታየቱን ስለሚያስከትል አባካኝ አሰራር ይሆናል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 199)። ስለዚህ ህግጋቱ ይህን አባካኝነት ለማስቀረት በሚያስችል መንገድ ሊሰራባቸዉ ይገባል ፤ ከዐቃቤህግ የበለጠ ለዚህ ተቆርቋሪ ሊኖር አይገባም።

መወያያ

ከተከሳሽ አቀራረብ ጋር በተያያዘ የጋዜጣ ማስታወቂያ አግባብነት የሚኖረዉ መቼ ነዉ? ተከሳሽ ተፈልጎ ሳይገኝ ሲቀር ወይስ በሌላ ሁኔታ? ከባልደረቦችዎ ጋር ሆነዉ ይወያዩበት።

በሌላ አጋጣሚ ተከሳሽ ተፈልጎ ባለመገኘቱ እንዲቀርብ በተቀጠረበት ቀን ሳይቀርብ ይቀራል። ዐቃቤህግም ፍርድቤትም ዘወትር የሚወስዱት ርምጃ በድጋሚ ትዕዛዝ መስጠት ነው። ሆኖም ተከሳሹ ሊገኝ ያልቻለ ሰው ነው። ስለዚህ ይህ ተከሳሽ በተገኘ ጊዜ እንዲቀርብ ማዘዝ ሲገባ ቀጠሮ በመያዝ ተከሳሹ ይቅረብ ብሎ በድጋሚ ማዘዝ በፖሊስ ላይ ሊፈጸም መቻሉ የሚያጠራጥር ሥራ ማብዛት ፣ ተከሳሽ በተገኘ ጊዜ ሊስተናገድ የሚገባው ሥራ በፍርድቤትና በዐቃቤህግ የሥራ ሸክም ውስጥ እንዲቆይ ማድረግ ይሆናል።

ከዚህ ይልቅ ከተደጋጋሚ ፍሬአልባ ትዕዛዞችና ቀጠሮዎች በኋላ እንደሚደረገው አስቀድሞ በመጀመሪያው ቀጠሮ ተከሳሹን ፖሊስ አግኝቶ ሲያቀርበው ክሱ መሰማቱ እንደሚቀጥል በመግለጽ ነገሩን አቋርጦ መቆየት ተመራጭ አይሆንም? ነገሩ ከተቋረጠ ፖሊስ ተከሳሹን ለማቅረብ አይተጋም የሚለውን ስጋት ለማስቀረት (ስጋቱ መሰረት የሌለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) ጉዳዩ ሲቋረጥ በተለምዶ እንደሚደረገው ነገሩን አቋርጦ መዝገቡን መዝጋት ሳይሆን ይህ ተዕዛዝ ለፖሊስ እንዲደርሰው ይደረግልኝ ብሎ ዐቃቤህግ ሊጠይቅ አይገባም?

የምስክር አለመቅረብና ቀጠሮ

መወያያ

ምስክር እንዲቀርብ በትቀጠረበት ዕለት ፖሊስ ለዐቃቤህግ የሰጠው መልስ አላገኝቷቸውም የሚል ነው። የተለመደው የዐቃቤህግ ርምጃ ተለዋጭ ቀጠሮ መጠየቅ ነው። ከዚህ የተለየ ርምጃ ሊኖር አይችልም? ከባልደረቦችዎ ጋር ሆነው ከዚህ የተለየ ዐቃቤህግ ሊያመለክት የሚችለው ነገር ስለመኖሩ ይመርምሩ።

ምስክር ካልቀረበ እንዲሁ ቀጠሮ ሊለወጥ ይችላል። ነገር ግን እስከመቼ የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ምስክር ሊገኝ ባልቻለ ጊዜ ሁሉ ቀጠሮ ሊሰጥ ይገባል? ቀጠሮ ሲለወጥ የሚሰጡ ትዕዛዞች በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 33 ፣ 53 ፣ 125 መሰረት እንዲሆኑ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 96(1) መደንገጉ ምንን ያመለክታል?

በተግባር እንደሚታወቀው ከምስክር አለመቅረብ ጋር ተያይዞ የሚፈጸም አሰራር አለ። ይኸውም የዐቃቤህግ ምስክሮች እስኪገኙ ክስን ማቋረጥ ነው። ክስ ማቋረጥ ዉጤቱ ላልታወቀ ጊዜ የነገሩን መሰማት ማስተላለፍ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ቀጠሮ መስጠት ማለት ነው። እንዲህ አይነት ቀጠሮ በቀጠሮ ድንጋጌዎች የታወቀ አይደለም። ነገሮች በተገቢው ፍጥነት እንዲያልቁ የሚጠይቀውን የህገመንግሥት መርህ የተከተለም አይደለም። ስለዚህ ተከሳሹ ቀርቦ ፍርድ በሚጠብቅበት ሁኔታ ፍርድቤት በዚህ አይነት ቀጠሮ ሊያስተላልፍ አይገባም። ክሱ እስከቀጠለ ድረስ በነገሩ ላይ ዉሳኔ ሊሰጥ ይገባል። ምናልባትም ክሱ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ (ከምስክር

ሌላ ማስረጃ ከሌለ) በነጻ የማሰናበት ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል:: እዚህ ላይ በሁለት ነገሮች ላይ ዐቃቤህግ ክህሎት ሊኖረዉ ይገባል::

የመጀመሪያዉ ቀደም ሲል የተመለከትነዉ በምስክር አለመገኘት ምክንያት የሚከሰተዉን የማስረጃ መባከን የምናስቀርበት አሰራር ነዉ - የቀዳሚ ምርመራ አሰራር:: ይህን አሰራር በሚገባ መከተል ምስክር ሲጠፋ ክስ በህግ ከተፈቀደዉ ዉጪ እንዲቋረጥ ከመጠየቅና ነገርን ያለቅጥ ከማንዛዛት ያድናል፣ ዐቃቤህግ የህግ ጠባቂነቱን ሚና በአግባቡ እንዲወጣ ያግዛል:: ምስክርነቱ በፍርድቤት ተመዝግቦ ስለሚገኝ በቀጥታ በማስረጃነት ይቀርባል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 144(1))፡፡

ሌላዉ የክስ ማንሳት ሥልጣንን የሚመለከት ነዉ:: ዐቃቤህግ ክስ የማንሳት ሥልጣን አለዉ:: እንዲያዉም በአሁኑ ጊዜ ይህ ሥልጣን ቀደም ሲል ከነበሩበት ገደቦች ነጻ የሆነ ሥልጣን ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 122 አብዛኛዉ ክፍል በአዋጅ ቁ. 11/1980 ተሽሯል):: ምስክር ባለመገኘቱ ክሱን የማስረዳት አቅም አጠራጣሪ ሲሆንና የቀዳሚ ምርመራ ምስክርነት ሊቀርብ ካልቻለ ክሱን ማስረዳት አለተቻለም ተብሎ በነጻ የማሰናበት ዉሳኔ መሰጠቱን ማስቀረት የሚቻለዉ ክሱን በማንሳት ነዉ:: ክሱ ከተነሳ ተከሳሹ በአፋጣኝ ፍርድ የማግኘት መብቱ ተጎድቷል የሚል ጥያቄ ሊያነሳ አይችልም:: ፍርድቤትም ዉሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ አይኖርም:: ማስረጃ በተገኘ ጊዜ ክሱን መቀጠል ስለሚቻል ክሱን የማዳን ተግባር መፈጸም ተቻለ ማለት ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 122 አብዛኛዉ ክፍል በአዋጅ ቁ. 11/1980 ሲሻር ክስን እንደገና ማቅረብ እንደተፈቀደ ነዉ)::

ይህን አሰራር የመከተል ሁኔታ አዘዉትሮ አይታይም:: ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነዉ:: ዐቃቤህግ በዚህ ላይ እንዲተጋ የሚያደርግ የፍርድቤት አሰራር የለም:: ክሱ ላልተወሰነ ጊዜ የሚቀጠርለት ከሆነ ዐቃቤህግ በህግ ተገቢ የሆኑትን አሰራሮች ለመከተል ፍላጎት ወይም መገፋፋት አይኖረዉም:: ስለዚህ በዚህ ረገድ ለዐቃቤህግ ክህሎት አለመዳበር ትልቁን አስተዋጽዖ የሚያበረክተዉ ፍርድቤት ነዉ ማለት ይቻላል::

ከዚህም በቀር የዐቃቤህግ የሙያ ነጻነት ሁኔታ ለዚህ አይነቱ አሰራር እንዲገፋፋ ያደርገዋል፡፡ የበላይ ዐቃብያነ ህግ በችሎት የሚቆመዉ ዐቃቤህግ በዚህ ጉዳይ አንጻራዊ ነጻነት እንዲኖረዉ ካልፈቀዱ በተለይ የክስ ማንሳት ነገር የሚታሰብ አይሆንም፡፡ ይህም ባይሆን ከበላይ ዐቃብያነህግ ጋር ዉይይት ተደርጎ ክስ ማንሳት ጠቃሚነቱ ቢረጋገጥም የበላይ ዐቃብያነህግ አንዳንድ ጊዜ ነጻነታቸዉን ባግባቡ ሊሠሩበት ስለማይፈቅዱ ከችሎት ዐቃብያነህግ ጋር በዚህ ጉዳይ ያለመስማማት ነገር ይዘወተራል፡፡

የክስ መሰማት

ዝግጅት

ምስክሮች ቀርበዉ የሚሰሙ ከሆነ በምስክር ማሰማት ጊዜ የሚገጥሙ ችግሮችን ለመቋቋም አንዱና ትልቁ መርህ ዝግጅት ነዉ። ከዝግጅቱ አንዱ አካል ደግሞ በምርመራ በቂ ማስረጃ ማግኘት ሲሆን ቀደም ሲል በተመለከትናቸዉ መንገዶች የሚከናወን ነዉ። ሆኖም መርማሪና በችሎት ተከራካሪ የተለያዩ ባለሙያዎች ሲሆኑ በምርመራ ጊዜ የተሰበሰበዉ ማስረጃ በርግጥ ፍርድቤት ቀርቦ እንደሚሰማዉ መሆን አለመሆኑን ተከራካሪዉ ባለሙያ (ዐቃቤህግ) ሊያረጋግጥ ይገባል። ክሱ የሚመሰረተዉ በምርመራ ጊዜ በተመዘገቡ ማስረጃዎች ስለሆነ በተለይ ምስክሮች ፍርድቤት ሲቀርቡ በርግጥ በምርመራ ጊዜ እንደተመዘገበዉ (እንደክሱ) ይናገሩ እንደሆነ ዐቃቤህግ አስቀድሞ ሊያዉቅ ያስፈልጋል። ይህም ብዙ ጥቅም አለዉ።

በቅድሚያ ዐቃቤህግ ማስረጃዉን ለማቅረብ የመክፈቻ ንግግር ያደርጋል። ይህም የቀረበዉን ክስና የሚቀርበዉን ማስረጃ ባህሪ ባጭሩ፣ በትክክል (objectively) እና ያለአድልዎ (impartially) የሚገልጽ ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 136(1))። ስለዚህ የክሱን መሰማት ከመክፈት በፊት ፍርድቤት ቀርቦ የሚሰማዉ ማስረጃ ምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነዉ ማለት ነዉ።

ክስ (በምርምራ ክፍል የተመዘገበ ምስክርነት)ና በፍርድቤት ፊት የሚሰማ ምስክርነት አለመጣጣምን ተከትሎ ሲፈጸም አዘዉትሮ የሚስተዋል ተግባር አለ - ምስክሩን በሃሰተኛ ምስክርነት መክሰስ። ይህ አለመጣጣም ምስክር ፍርድቤት ሲቀርብ የሚመሰክረዉን ነገር ዐቃቤህግ አስቀድሞ ካለማወቁ የሚመጣ ነዉ። አለመጣጣሙ ክሱን ይጎዳዋል። ከዚህ በኋላ በምስክሩ ላይ የሚወሰደዉ ርምጃ ለክሱ የሚፈይደዉ ነገር አይኖርም። ከዚህም በቀር እንዲህ አይነቱ ርምጃ በህግ ያለዉ ተቀባይነትም ቢሆን አጠያያቂ ነዉ።

ማሳያ

በፍርድቤት ፊት ቀርቦ የሰጠዉ ምስክርነት በፖሊስ ጣቢያ ከተመዘገበዉ የሚለይ ምስክር በሃሰት የተናገረዉ የት እንደሆነ መለየት የሚቻለዉ እንዴት ነዉ? በሁለቱ ቦታዎች የተነገረዉን በማወዳደር የትኛዉ ሃሰት እንደሆነ መለየት ይቻላል?

ምስክሩ ሃሰት የተናገረዉ በየትኛዉም ተቋም ፊት ቢሆን ዉጤቱ ተመሳሳይ ነዉ?

በሃሰት የመወንጀል እና በሃሰት የመመስከር ወንጀሎች የሚባሉት ልዩነታቸዉ ምንድን ነዉ?

በሃሰት መስክሯል ያልነዉን ሰዉ ለምርመራ የምንፈልገዉ ቢሆን በቁጥጥር ስር ለማድረግ የፍርድቤትን ፈቃድ መጠየቅ ይገባል? ፍርድቤት ይህን የመያዝ ትዕዛዝ ጥያቄ አላስተናግድም ቢል ዐቃቤህግ ምን ማድረግ አለበት?

የተለመደዉ አሰራር ክስን ከመክፈት በፊት ምስክሮችን የማነጋገር ልማድ የማይዘወተርበት ነዉ። ምናልባትም ዐቃቤህጉ የሚዘጋጀዉ በምርመራ መዝገብ ላይ የተመዘገበዉን ምስክርነት

ብቻ በማጥናት ይሆናል። ይህ ካልሆነም ክሱንና በማስረጃ ዝርዝር የተመለከተዉ ምስክር የዐይን መሆን አለመሆኑን በማየት ብቻ ይሆናል። የክርክር መክፈቻ ንግግር የሚያቀርበዉ (ጭብጥ የሚሰጠዉ) በዚህ ላይ ብቻ በመመርኮዝ ነዉ።

ሆኖም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 136 እንደተመለከተዉ የክስ መክፈቻ ሲቀርብ በትክክል ወይም በተጨባጭ ሊሆን ይገባል። የሚቀርበዉ ሃሳብ ተጨባጭ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚገለጸዉ ነገር በርግጥ ለመኖሩ ርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል። ይህንም ለማድረግ ምስክሮች በርግጥ የሚናገሩትን ነገር አስቀድሞ ማወቅ ተገቢ ነዉ።

ዝግጅት የምስክሩን ብቃት ከመገምገምና ከመወሰን በተጨማሪ ይህን ብቃት ለማጎልበትም ይረዳል። በሃገራችን የሙግት አካሄድ በከፊል አድቨርሳሪያል እንደመሆኑ ተቃራኒ ወገን በምስክር መስማት ጊዜ መስቀለኛ ጥያቄ የማካሄድ መብት አለዉ። ምስክር በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ እንዳይምታታበት ወይም የመስቀለኛ ጥያቄን ዓላማ የማምከን ችሎታ እንዲኖረዉ አስቀድሞ ሊዘጋጅ ይገባል። ለዚህም ስለሚመሰክርበት ነገር ያለዉ ዕዉቀት በዝርዝር ሊመረመር ይግባል።

መወያያ

ትጉህ ዐቃቤህግ ስለሆኑ ምስክሮችን ችሎት አቅርበዉ ከማሰማትዎ በፊት አግኝተዉ ሊመረምሯቸዉ ፈቅደዋል። እነርሱም በክሱ እንደተነገረዉ ይመሰክራሉ ብለዉ ይጠብቃሉ። ሆኖም ምስክርነታቸዉ በፍጹም የተለየ ሆኖ አገኙት። እነዚህን ምስክሮች ምን እንዲያደርጉ ይመክሯቸዋል ወይም ያዝዟቸዋል?

ከላይ ባደረጉት ምርመራ ምስክሮቹ መርማሪዉ ፖሊስ በቃል ካነጋገራቸዉ በኋላ በወረቀት ላይ ጽፎ ያቀረበላቸዉን ነገር ሳያነብላቸዉ በአስቸኳይ ፈርመዉ እንዲሄዱ ስላደረጋቸዉ የማንበብ እድልም ሳያገኙ የምስክርነት ቃላቸዉ እንደሆነ በማመን ፈርመዉ መመለሳቸዉን እንጂ በፖሊስ ተመዘገበ የተባለዉን ምስክርነት አለመስጠታቸዉን አረጋገጡልዎ። እነዚህን ምስክሮች በተመለከተ የሚያደርጉት ምንድን ይሆናል?

መወያያ

ምስክርን ችሎት ከመቅረቡ በፊት መርምረዉ እንደክሱ ሊመሰክር እንደሚችል አረጋገጡ። በዚሁ ችሎት እንዲቀርብ ነግረዉ ያሰናብቱታል ወይስ ከዚህ ያለፈ ከርስዎ በኩል የሚፈጸም ነገር አለ? ከባልደረባዎ ጋር በመሆን በዚህ ረገድ አሉ የሚሏቸዉን አማራጮች ወይም አቀራረቦች መርምረዉ ያግኙ፣ ይዘርዝሯቸዉ።

ዐቃቤህግ ምስክር ስለጉዳዩ የሚያዉቀዉን እንዲነግረዉ በማድረግ ነገሩን በሚገባ ያስረዳ አያስረዳ እንደሆን ገምግሞ ይወስናል። ሆኖም ለምስክር የሚያሳዉቀዉ ምንም ነገር የለም፣ ግንኙነቱ

ከምስክር ወደዐቃቤህግ ብቻ መረጃ የሚፈስስበት ነዉ ማለት አይደለም። ዐቃቤህግ ከምስክር መረጃ የሚያገኘዉ በክስ መሰማት ጊዜ በዕዉን እንደሚደረገዉ አይነት የጥያቄና መልስ ሂደትን በመከተል ነዉ። በዚህ መንገድ የተገመገመዉ ምስክር ብቁ መሆኑ ከታመነበት ምስክሩ ሊያዉቃቸዉ ስለሚገቡ ስለብዙ ነገሮች ዐቃቤህግ ሊነግረዉ እና ሊመረምር ይጠበቃል። ከነዚህ አንዳንዶቹን ቀጥለን እንይ፦

- ምስለጢሮችን በተመለከተ፦ ምስክሩ የሚያዉቃቸዉ እና ከሚመሰክርባቸዉ ነገሮች ጋር የተያያዙ ምስጢሮች ካሉ እነዚህን መግለጽ ወንጀል መሆኑን እንዲያዉቅ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ እነዚህን ምስጢሮች እንዲገልጽ የሚያደርግ መስቀለኛ ጥያቄ ሊነሳ እንደሚችል፣ በዚህ ጊዜ ምስክሩ ምስጢሩን እንዳይገልጽ በህግ የተከለከለ መሆኑን በማሳወቅ መብቱ እንዲጠበቅለት ፍርድቤቱን እንዲጠይቅ ማሳወቅ።
- የሚያዉቀዉን ወይም ዕዉነቱን መናገር የሚገባዉ ስለመሆኑ፦ እንዲናገር የሚፈለገዉን ሳይሆን የሚያዉቀዉን እንዲናገር የሚጠበቅ ምስክር ምን እንደሚያዉቅና እንደማያዉቅ ለመለየት አያስቸግርም። በዝግጅት ጊዜ ለጉዳዩ የሚጎዳዉንም የሚጠቅመዉንም ይገልጻል። በተለይ ተቃራኒዉ ወገን በህግ ባለሙያ የሚረዳ ከሆነ ባለሙያዉ ምስክሩን በተመለከተም ሆነ ስለሚመሰክረዉ ነገር ተዘጋጅቶ ሊቀርብና ምስክርነቱን ሊያፍረከርከዉ ስለሚችል አስቀድሞ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን ለማወቅ ምስክሩ ስለጉዳዩ የሚያዉቀዉን ሁሉ መዳሰስ ጠቃሚ ነዉ። የምስክሩ ደካማ ጎኖች የሚያስከትሉትን ጉዳት መቀነስ ወይም ለማስቀረት የሚያስችል ዘዴ ለመፈለግ ይረዳል። ምስክሩም በሚመሰክርበት ጊዜ የሚያዉቀዉን ስለሚናገር በመስቀለኛም ሆነ በሌላ ጥያቄ ጊዜ ነገሩን የማዘባረቅ ሁኔታ አይፈጠርም። ለዚህ ሁሉ ምስክር የሚያዉቀዉን ነገር እንዲመሰክር መገፋፋት ወይም ማሳመን አንዱ የዝግጅት ስራ እንዲሆን ማድረግ ያስልጋል።
- ምስክሩ ስለሚያዉቀዉ ነገር አስቀድሞ እንዲገልጽም ሆነ በምስክርነት ጊዜ የሚያጋጥሙት ነገሮች ግር እንዳይሉት የምስክርነት መሰማት የሚመስል ጥያቄና መልስ ማካሄድ፣ ስለነዚህ ማብራሪያ መስጠት (በተለይ በዋና ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ እንደማይጠየቅ ስለዚህ ነገሮችን ሁሉ በዝርዝር የሚናገረዉ ራሱ መሆኑን፣ የዘለለዉ ነገር ሲኖር ዐቃቤህጉ ምን አይነት አጠያየቅ እንደሚከተልና ይህም የተዘለሉ ነገሮችን አስቦ ማስታወስና መመለስ እንዳለበት መጠቆሚያ መሆኑን ለምስክር ማሳወቅ፣ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ሊያጋጥም ስለሚችለዉ ነገር፣ ወዘተ ማስረዳት) ያስፈልጋል።
- በዚህ መንገድ ታይቶ ለነገሩ ተገቢ የሆነ ምስክር በችሎት ቀርቦ ሲሰማ አዲስና የሚያደናግር ሁኔታ እንዳይገጥመዉ ሊብራሩለት የሚገቡ ሌሎች ነገሮች አሉ። የችሎቱን አቀማመጥ በተመለከተ የጉዳዩ ተዋንያን እንዴት እና የት እንደሚቀመጡ ወይም እንደሚቆሙ፣ እነዚህ እነማን እንደሆኑ፣ ምስክሩ ፍርድቤት ሲቀርብ

ለምስክርነት ከመቀመጡ በፊት ስለሚፈጸሙ አሰራሮች (ለምሳሌ ስለመማል) ወዘተ ዐቃቤህግ ሊያስረዳዉ የሚገባዉ በዝግጅት ጊዜ ነዉ:: በተጨማሪም ምስክር ፍርድቤት ከመጣ በኋላ እስኪጠራ ድረስ የት ሊቆይ እንደሚገባዉ ዐቃቤህግ ሊገልጽለት ይገባል:: አንዳንድ ጊዜ በተግባር እንደሚታየዉ ምስክሮች በችሎት ተቀምጠዉ እያዳመጡ ተከሳሹ ተጠርቶ ወደመቆሚያ ሳጥኑ የሚገባበት፣ ክሱ የሚነበብበት፣ ወዘተ አጋጣሚ አለ:: ከዚህ በኋላ እነዚህ ምስክሮች ይሰማሉ:: ይህም የክሱን መስማት ሂደት ሚዛናዊነት ጥርጣሬ ዉስጥ እንዲገባ ያደርጋል:: ስለዚህ አንዳንድ ፍርድቤቶች ምስክሩ ክሱን እና የሚመሰክርበትን ነጥብ ምናልባትም የተከሳሹን ክርክር የሰማ ስለሆነ፣ በዚህ ዕዉቀት ላይ ተመስርቶ ይሁን ወይም ስለሚያዉቀዉ ነገር፣ በየትኛዉ መንገድ እንደሚመሰክር አጠራጣሪ ስለሆነ ምስክሩ አይሰማም ብለዉ ይወስናሉ (ጸሃፊዉ በዳኝነት በሠራ ጊዜ ከነበረዉ ተሞክሮ):: ሌሎች ለነገሩ ክብደት ባለመስጠት ምስክርነቱን ይሰማሉ:: ዞሮዞሮ ምስክርነቱ ሳይሰማ የሚቀር ከሆነ ክሱ ይጎዳል:: የህዝብ ጥቅም ይጎዳል:: ስለዚህ ምስክር ሲቀርብ የት ሊቆይ እንደሚገባዉ ሊያዉቅ ያስፈልጋል፣ ይህም በዝግጅት ጊዜ የሚሆን ነዉ::

- ከምስክሩ ሌላ ዐቃቤህግ ከምስክሩ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን በተመለከተ ዝግጅት ማድረግ አለበት:: ምስክሩ በኃላፊነቱ የተጻጻፋቸዉ ወይም የፈረመባቸዉ ሰነዶች፣ ስለምስክሩ የተዘጋጁ የጉዞ ወይም የህክምና ሰነዶች (ደረሰኞችን ጨምሮ)፣ በወንጀል ምርመራ ጊዜ የሰጣቸዉ ቃሎች ወዘተ ፍርድቤት ፊት ከሚሰጠዉ ምስክርነት ጋር የማይጣጣም ይዘት ሊኖራቸዉ እና ተቃራኒዉ ወገን ምስክሩን ለማስተባበል (ለኢምፒችመንት) ሊያዘጋጃቸዉ ይችላል:: ስለዚህ እነዚህን አስቀድሞ ተመልክቶ በጉዳዩ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት በሚያመጣ መልኩ ከምስክርነቱ ጋር መቃረን አለመቃረናቸዉን መመዘንና ምስክሩን ለመጥራት ወይም ላለመጥራት መወሰን አለበት::
- ምስክሩ ለጉዳዩ ገንቢ የሆኑ ነገሮችን የሚያስታዉስና አፍራሽ የሆኑ ነጥቦች ላይ አላስታዉስም የሚል ከሆነ ፍርድቤት ምስክሩን እየዋሸ ነዉ ብሎ ሊገምተዉ ስለሚችል ስለጉዳዩ በስፋት (አፍራሽ የሆነዉንም ጨምሮ) የሚያስታዉሱ ምስክሮችን መምረጥ ያስፈልጋል:: የበለጠ የሚታመኑ ስለሆነ::
- ምስክር ችሎት ስለሚቀርብበት ሁኔታ እንዲሁም በመሰማት ጊዜ ሊኖረዉ ስለሚገባ አቀራረብ ዐቃቤህግ ሊያስታዉሰዉ ወይም ሊያሳዉቀዉ ይገባል:: ቀጥሎ የተመለከቱት ከፊሎቹ ምስክር ችሎት ከቀረበ በኋላ የሚከናወኑ፣ ዋናዉን ሥራ የሚያስተጓጉሉ ሁኔታዎች ናቸዉ:: ስለዚህ ምስክር ችሎት ከመቅረቡ በፊት ሊታሰብባቸዉ ይገባል::

1. ስለአለባበስ - በተቻለ መጠን ፍርድቤቱ እንዳለበት አካባቢ ልማድ ሥርዓት ያለዉ አለባበስ እንዲኖረዉ መምከር
2. ከድካም ነጻ ሆኖ እንዲቀርብ እንዲሁም ቀርቦ ሳይጨናነቅ ነገር ግን ጠያፍ ባልሆነ መንገድ እንዲመሰክር ማስታወስ
3. ጥያቄ ከመመለስ በፊት ጥያቄዉን በሚገባ ማዳመጥ (ከመስማት በላይ ነዉ)፣ ከዚያም ግልጽ ካልሆነ እንዲደገምለት በትህትና መጠየቅ፣ መልሱን ወዲያዉ ከመመለስ በፊት ማሰብ እንዳለበት ማስታወስ
4. ዳኛ ጣልቃ ገብቶ ሲናገር ወይም ተቃዉሞ ሲቀርብ ምስክሩ መናገሩን አቋርጦ ማዳመጥ እንዳለበት፣ ምስክርነቱን ያቋረጠዉ ንግግር ሲያልቅ ቀደም ሲል ሲሰጠዉ የነበረዉ መልስ አለማለቁን አስታዉሶ መልሱን ለመጨረስ (ጥያቄዉና መልሱ አያስፈልግም ተብሎ በፍርድቤቱ ካልተወሰነ) መጠየቅ እንደሚገባ መንገር (ይህ በተለይ ምስክርነት በቴፕ በሚቀረጽበት ችሎት በእጅጉ አስፈላጊ ነዉ)
5. የማያቀዉ ነገር ሲጠየቅ አላዉቅም ማለት ለሚያዉቀዉ ነገር ሲመልስ በትህትና እና ተረጋግቶ እንጂ መሸቆጥቆጥ እንደሌለበት፣ መልስ ሲሰጥ በድምጽ እንጂ በምልክት መሆን እንደሌለበት መግለጽ (ምስክርነት በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ሲቀዳ ሊታለፍ የማይገባዉ ነዉ)
6. ምስክር በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ከሌላዉ ወገን ጋር ንትርክ ዉስጥ እንዳይገባ ለተጠየቀዉ ጥያቄ ብቻ መልስ እንዲሰጥ፣ ካልተጠየቀ ለሌላዉ ወገን ንግግሮች መልስ ከመስጠት እንዲቆጠብ መምከር
7. የተደራረቡ ጥያቄዎች ወይም ጥቅል ጥያቄዎች ሲቀርቡ ምስክሩ ተጠንቅቆ እንዲመልስ መምከር:- የተደራረቡ ከሆነ ጥያቄዎቹን ነጣጥሎ መመለስ፣ ጥቅል ከሆነ ደግሞ ጠያቂዉ በተለይ የሚፈለገዉ ነገር ካለ ለይቶ ቢጠይቅ ለመመለስ ፈቃደኛ መሆኑን እንዲገልጽ ማስታወስ ያስፈልጋል::

የምስክር መሰማት

መወያያ

ምስክር ለማሰማት ዐቃቤህግ ከላይ በተመለከቱት መንገዶች በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ የክርክር መክፈቻ መበለጫ ይሰጣል። በዚህ ጊዜ ተዘዉትሮ የሚታወቀዉ የጭብጥ አሰጣጥ ‘ምስክሮች እንደክሱ ያስረዳሉ’ የሚለዉ ነዉ። ይህ ምን ያህል ተገቢና በቂ ነዉ?

ምናልባት የዐይን ምስክር የተባሉትን በተመለከተ ይህ መግለጫ በቂ ነዉ ሊባል ይችል ይሆናል:: ከዚህ ዉጪ የተጠራዉን ምስክርና ሰነድ ሁሉ በደፈናዉ እንደክሱ ያስረዳል ብሎ መግለጫ መስጠት በተራ አስተሳሰብ እንኳ ለመቀበል የሚያስቸግር ነዉ:: ቢያንስ አንድን ነገር በተመለከተ ሁሉም ሰዎች በእኩል ጊዜና ቦታ እኩል አስተዉለዉ እኩል መረጃ ሊኖራቸዉ አይችልም:: ስለዚህ በተቻለ መጠን የክስ መክፈቻ መግለጫ ሲቀርብ በደፈናዉ ከሚሆን ዘርዘር ያለ ቢሆን ለሁሉም ወገን ጠቃሚ ነዉ:: ፍርድቤትም ዐቃቤህግ ድፍንፍን ያለ ሳይሆን ግልጽና ተጨባጭነት ያለዉ መግለጫ እንዲሰጥ መገፋፋት አለበት::

ምስክሮች ከቀረቡ በኋላ በሚሰሙበት ጊዜ የዐቃቤህግ ዋናዉ ተግባር ምስክሮችን በመጠየቅ ማስመስከር ነዉ:: ይህ ምስክርነት ክሱን እንዲያስረዳ ስለሚፈለግ የጥያቄዉ አመራርና አካሄድ ክህሎትን የሚፈልግ መሆኑ ግልጽ ነዉ:: ዐቃቤህግ ክሱን ለማስረዳት የራሱን ምስክሮች አቅርቦ ማሰማት ብቻ ሳይሆን የተከሳሽን ምስክሮች በመጠየቅም የማስመስከር ተግባር አለዉ - መስቀለኛ ጥያቄ:: ለዚህም ክህሎት ያስፈልጋል:: በዚህ ረገድ ብዙ ሊባል የሚችል ቢሆንም ከሃገራችን ህግና የአሰራር ልማድ አኳያ አግባብነት ያላቸዉን ህጎችና የምስክር አጠያየቅ ቴክኒኮችና አወቃቀር እንመለከታለን::

ስለዋና ጥያቄ

የዐቃቤህግን ምስክር ሊሰማ በቀረበበት ጊዜ ´ስለመጡበት ጉዳይ ለፍርድ ቤቱ ያስረዱ´ የሚል (ጥያቄ ሳይሆን ትዕዛዝ የመሰለ) ሃሳብ ከዐቃቤህግ መቅረቡ የተዘወተረ ነዉ:: አንድ ምስክር ፍርድቤት የሚቀርብበትን ጉዳይ አስመልክቶ እጅግ በርካታ ነገር ሊያዉቅ ይችላል:: ከዚህ ሁሉ የቱ መቼ ለፍርድቤቱ ሊነገር እንደሚገባ ምስክሩ ሊያዉቅ አይችልም ፣ ዐቃቤህጉ ለነገሩ አግባብ ያላቸዉን ነጥቦች ተንተርሶ ጥያቄ እያነሳ ካልመራዉ በቀር:: ሌላዉ ቀርቶ ከየት እንደሚጀምርም ሊቸገር ይችላል (በርግጥ ይህ ሁሉ ለሙያ ምስክሮች ላያስቸግር ይችላል):: ስለዚህ በጉዳዩ ላይ ምስክሩ ያዉቃል የተባለዉን እና ለጉዳዩ የሚያስፈልጉ ነገሮችን አስመልክቶ ዐቃቤህግ ጥያቄዎች እያነሳ ምስክሩ እንዲመልስ ማድረግ ያስፈልጋል:: ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን ለነገሩ ጥቅም የሌለዉን ሃሳብ ያካተተ ረጅም ትረካ ሊቀርብና ያላግባብ ጊዜና ጉልበት ሊባክን ይችላል:: ከዚህም በቀር ፈራጁን ወገን የማሰላቸት ዉጤት ይኖረዋል::

ይህ ማለት ግን ለመላሹ ሰፊ የመናገር ዕድል የሚሰጡ ጥያቄዎች ሊነሱ ፈጽሞ ክልክል ነዉ ማለት አይደለም:: እንዲያዉም አንዳንዴ የዚህ አይነት ጥያቄዎች የምስክርነቱ መጀመሪያ ላይ አስፈላጊ መሆናቸዉ አይቀርም:: የዋና ጥያቄዎች አወቃቀር መርህ እንደሚያመለክተዉ ወደዝርዝር ጥያቄዎች ከመግባት በፊት እንዲህ አይነት አጠቃላይ ጥያቄዎች መጠየቅ ተገቢ ሊሆን ይችላል:: በዚህ መሰረት ከሚገኘዉ መረጃ ዉስጥ የበለጠ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸዉ

ነጥቦች ላይ በተለይ በመጠየቅ የጥያቄዉ አድማስ እየጠበበ እንዲሄድ ሊደረግ የሚችልበት የጥያቄ አወቃቀር ይገኛል::

ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ምስክር አጠቃላይ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚቸገርበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል:: በዚህ ጊዜ ወደተለዩ ነጥቦች ያተኮረ ጥያቄ በመጠየቅ በሚሰጣቸዉ መልሶች ለአጠቃላዩ ጥያቄ መልስ መሰረት ማበጀትና የእዉርድምብር ሳይሆን በቂ መነሻ ያለዉ መልስ ማግኘት ይቻላል::

ስለመሪ ጥያቄ - በዋና ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ የተከለከለ ነዉ:: ነገር ግን ይህ ክልከላ የሚሰራዉ ሌላኛዉ ተከራካሪ ሳይፈቅድ ከቀረ ነዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ ቁ. 137(2)):: ስለዚህ ተከሳሹ ወይም ጠበቃዉ ካልተቃወመ ዐቃቤህግ በዋና ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል፣ ፍርድቤት በራሱ አስተያየት መሪ ጥያቄ መጠየቅን ሊከለክል አይችልም ማለት ነዉ?

መሪ ጥያቄ ተነስቷል ብሎ መቃወሚያ ማቅረብ በፍርድቤቶቻችን የተለመደ የክስ መስማት ሂደት አጋጣሚ ነዉ:: ዋና ከሚባሉት የማስረጃ መቃወሚያዎች አንዱ መሪ ጥያቄን የሚመለከት ነዉ:: ነገር ግን ማስረጃን መቃወም የፍርድቤትን ዉሳኔ የሚጠይቅ በመሆኑ ዋናዉ ክርክር እየተቋረጠ የሚቆይበትን ጊዜ ያበዛል:: ስለዚህ መሪ ጥያቄ ተጠይቋል እየተባለ የሚነሳ መቃወሚያ በርግጥ መሪ ጥያቄ ሲኖር ብቻ እንዲሆን ያስፈልጋል:: ለዚህ ደግሞ መሪ ጥያቄ ምን ማለት እንደሆነ ለይቶ ማወቅ ያስፈለጋል:: አዘዉትሮ እንደሚታሰበዉ መሪ ጥያቄ አዎ ወይም አይ የሚያስብል ጥያቄ ነዉ:: ይህ ማለት ግን እነዚህን ሁለት አማራጮች በአንድ ላይ የሚያቀርብ ጥያቄ ማለት አይደለም:: መሪ ጥያቄ መልሱን የሚጠቁም ማለት ነዉ:: ስለዚህ ከሁለቱ አንዱን በመጠቆም የተጠቆመዉ መልስ ብቻ እንዲመለስ የሚጋብዝ ጥያቄ ነዉ:: ስለዚህ የመልሱን ምርጫ ለምስክሩ በመተዉ የሚቀርብ ጥያቄ መልሱ ከሁለቱ አንዱ (አይ ወይም አዎ) ቢሆንም መሪ ጥያቄ እንደማይባል መታወቅ ይኖርበታል::

መሪ ጥያቄ የትኛዉንም ያህል አማራጭ መልሶች ቢኖሩ ከነዚህ አንዱን ብቻ እንዲመርጥ ምስክሩን የሚጋብዝ ጥያቄ ነዉ:: ስለዚህ የማስረጃ ተቃዉሞ ሲነሳ ይህ ነገር ከግምት ሊገባ የግድ ነዉ:: ዐቃቤህግም በሌላዉ ወገን የሚነሳዉ ጥያቄ በርግጥ መሪ ነዉ አይደለም የሚለዉን በፍጥነት የመለየት ብቃት ሊኖረዉ የሚችለዉ ይህን ልዩነት ጠንቅቆ ሲያዉቅ ነዉ::

ይህም ሆኖ በተለያዩ አጋጣሚዎች ከላይ የተመለከተዉ ባህሪ ያለዉ ጥያቄ ቢነሳም ተቃዉሞ ሊቀርብ አይገባም:: ለምሳሌ ክርክር ባላስነሱ ፍሬነገሮች ላይ መሪ ጥያቄ ቢቀርብ መቃወም ተገቢ አይደለም:: በጣም ህጻን ወይም አረጋዊ የሆኑ ሰዎች ምስክር በሚሆኑ ጊዜና ምስክር ስለተጠራበት ጉዳይ አንዳንድ ነገሮችን ማስታወስ በሚያስፈልግ ጊዜ ምስክርነታቸዉን ለማግኘት መሪ ጥያቄ መጠየቅ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል::

ስለስሚስሚ ማስረጃ፡- በዋና ጥያቄ ጊዜ የሚነሳዉ ሌላዉ ጭብጥ የስሚስሚ ምስክርነት የሚያስከትል ጥያቄ ማንሳት ይቻላል ወይ የሚለዉ ነዉ:: በማስረጃ ህግ መርህ የስሚስሚ ማስረጃ በጠቅላላዉ የተከለከለ ነዉ:: ሆኖም በተለዩ ሁኔታዎች ይህ ማስረጃ ሊፈቀድ ይችላል::

መወያያ
በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.137(1) ...በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ምስክሩ ስለሚያዉቃቸዉ ፍሬ ነገሮች... በሚል የተመለከተዉ ዐቃቤህግ ምስክሩን የስሚስሚ ምስክርነት ሁልጊዜ እንዲጠይቅ ለመፍቀድ ነዉ ወይስ በተለየ ሁኔታ የሚፈቀዱ የስሚስሚ ምስክርነት ሁኔታዎችን በህጉ ዉስጥ ለማካተት የታሰበ ነዉ?

በተለምዶ የግምት (ኦፒኒየን) ምስክርነት የምንለዉን በተመለከተም እንዲሁ ሰዉ ግምቱን እንዲመሰክር አይፈቀድም፣ የሚያዉቃቸዉን ፍሬነገሮች እንጂ:: ምናልባት የሙያ ምስክሮችን በተመለከተ ይህ አይሰራ ይሆናል::

መወያያ
ባለሙያ ያልሆኑ ምስክሮች በቀረቡበት ጊዜ ሁሉ ግምትን የሚመለከት ማስረጃ እንዲሰጡ መጠየቅ አይቻልም ወደሚል ድምዳሜ መድረስ ይቻላል? ለምን?

ፍጥነትን፣ ርቀትን፣ መጠንን፣ ወዘተ በተመለከተ ለማወቅ ወይም ለማስመስከር ብንፈልግ በግምት እንዲነገር ከመጠየቅ ልንከለከል ይገባል?

የዋና ነጥቦችን (ጭብጦችን) ምስክርነት አለመበታተን፡- ዋና ጥያቄ ሲካሄድ ዐቃቤህግ ወደዋናዉ ጉዳይ ከመግባቱ በፊት ዙሪያጥምጥም መሄድ የለበትም:: የመግቢያ ጥያቄዎች ከተነሱ በኋላ ወደዋናዉ ጉዳይ ገብቶ ለነገሩ አንኳር የሆኑትን ጥያቄዎች መጀመር አለበት:: የዋና ጥያቄ ዓላማ የቀረበዉን ክስ ማስረዳት የሚችሉትን ነገሮች ማቅረብ በመሆኑ የጉዳዩ አንኳር ሃሳቦች ወደኋላ የሚቆዩበት ምክንያት አይኖርም::

ዋናዋና ነጥቦች በሚመሰክሩበት ጊዜ ዝርዝር ነገሮችን ወይም ማብራሪያዎችን ፍለጋ ጣልቃ በመግባት ጥያቄ ማንሳት የምስክርነቱን ፍሰት ያስተጓጉላል፣ ክብደቱንም ይቀንሳል:: ስለዚህ ማብራሪያዎችን ወደኋላ በማቆየት መጠየቅ የሚቻል ሆኖ ዋና ነጥቦች ላይ የሚቀርበዉን ምስክርነት ሳይቆራረጥ ለማቅረብ ደጋግሞ ጣልቃ እየገቡ ማብራሪያዎችን አለመጠየቅ ይመረጣል::

በተመሳሳይ ሁኔታ የአካባቢ ማስረጃ በአንድ ላይ ሳይበታተን ሲቀርብ የበለጠ ክብደት ስለሚኖረዉ እና ይዘቱንም ለመረዳት ስለሚያመች በነዚህ ማስረጃዎች መሃል ሌላ ማስረጃ ወይም ማብራሪያ ጣልቃ ሳይገባ ምስክርነቱ እንዲሰማ ማድረግ ያስፈልጋል::

አጫጭር ጥያቄዎችና ምስክርነትን ስለመደጋገም፡- በዋና ጥያቄ ጊዜ የሚነሱ ጥያቄዎች ምስክሩ ነገሩን የማስረዳት ሰፊ ዕድል የሚሰጡ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: ምክንያቱም ነገሩን የሚያስረዳዉ ምስክሩ እንጂ ባለጉዳዩ ወይም ጠያቂዉ አይደለም:: ስለዚህ ጥያቄዎቹ አጫጭር ቢሆኑ ይመረጣል::

አንዳንድ ጊዜ ለክርክሩ ጠቃሚ የሆኑ ፍሬነገሮች ላይ ትኩረት እንዲደረግ መፈለግ አይቀርም:: ስለዚህ የፍርድቤቱን አትኩሮት ወደነዚህ ነጥቦች ለመሰብሰብ እነዚህ ነጥቦች ተደጋግመዉ እንዲነገሩ ማድረግ ተገቢ ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ይህን ስናደርግ ጥያቄዎቻችን ሊደጋገሙ አይገባም:: ተቃዉሞ ሊነሳበት ወይም ችሎቱን ሊያሰለች ይችላል:: ስለዚህ ተፈላጊዉን ነጥብ የሚመለከቱ ሌሎች ጥያቄዎችን በማንሳት በተለያየ መንገድ ተደጋግሞ እንዲመለስ ማድረግ ይመከራል::

ጥያቄዎች ስለሚቀርቡበት ቋንቋና ስለተደራረቡ ጥያቄዎች፡- በዙዉን ጊዜ ምስክር የሚሆኑ ሰዎች የህግ ሙያ ወይም መሰረታዊ የህግ ዕዉቀት የላቸዉም:: ስለዚህ ጥያቄዎቻችን በተራ የዕለት-ተዕለት መግባቢያ ቋንቋ ሊቀርብ ይገባል:: የህግ ሙያ ቋንቋ በጥያቄዎች ዉስጥ ሊካተት አይገባም:: ምስክሩን ግራ ያጋባል::

በአንድ ጊዜ አንድ ጥያቄ መጠየቅ ጠቃሚ ነዉ:: ምስክሩ በርካታ ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ ከተጠየቀ መልሱ ላይ ከፊሉን ሊዘነጋ ይችላል:: ስለዚህ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ከተፈለገ በየተራ ሊጠየቁ ይገባል እንጂ ተነባብረዉ መሆን የለበትም::

ስለመስቀለኛ ጥያቄ

በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ዐቃቤህግ የሚፋጠጠዉ ከተከሳሹ መከላከያ ምስክሮች ጋር ነዉ:: በዚህ ጊዜ በቀጥታ ከመዋሸት አንስቶ ለዐቃቤህግ ክስ ገንቢ የሆኑ ወይም የተከሳሹን ክርክር የሚያፈርሱ ፍሬነገሮችን አላስታዉስም እስከማለት የሚደፍሩ ምስክሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: ስለዚህ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ዋናዉ የዐቃቤህግ ግብ ይህን ድፍረት ማዳከምና በህግና በሥነምግባር ደንቦች በታወቁ መንገዶች ሃቆችን ማፍረጥረጥ ይሆናል:: ይህም የተባለዉን ሃቅ ከምስክሩ ማግኘትን የሚመለከት ነዉ:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊታወስ የሚገባዉ ነገር እንደየተመልካቹ አንድ ሃቅ በተለያየ አቅጣጫ ሊተነተን የሚችል መሆኑ ነዉ:: ከጊዜ ማለፍ

ለነገሩ ከሚኖር የተዛባ አመለካከት ወይም ከጥቅም ጋር ከተያያዘ አቀራረብ የሰዎች አተያይ በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያየ ሊሆን ይችላል::

ስለዚህ በፍርድ ሂደት ዕዉነቱ ላይ የመድረስ ግብ ወደተረትነት እንዲጠጋ ያደርገዋል:: ያም ሆኖ በተቻለ መጠን ዕዉነቱን ለማዉጣት መሰራት ይኖርበታል:: ለዚህም ቀደም ሲል እንደተመለከትነዉ ዝግጅት አስፈላጊ ነዉ:: ችግሩ አሁን ባለዉ የአሰራር ልማድ ስለሌላዉ ወገን ምስክር ቃል መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ነዉ:: ስለዚህ የተቃራኒ ወገን ምስክር በተለይም የተከሳሽ ምስክር በፍርድቤት ሲቀርብ ምን እንደሚመሰክር አስቀድሞ ማወቅ አይቻልም:: እንዲያዉም በመደበኛዉ አሰራር የተከሳሽ ማስረጃ ምንነት የሚታወቀዉ ክርክሩ ወደፊት ገፍቶ የዐቃቤህግ ማስረጃ ታይቶና ተሰምቶ ካበቃ በኋላ ነዉ::

መወያያ

በአንድ ችሎት የቀረበዉ የወንጀል ክስ ተሰምቶ ሲያበቃ ተከሳሹ ወንጀሉን አልፈጸምኩም አለ:: ፍርድቤቱም ተከሳሹን ወንጀሉን አልፈጸምኩም ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ እንዲያብራራ ጠየቀዉ:: እንዲህ አድርጎ ለማጣራት ያስገደደዉ ወንጀል አልፈጸምኩም የሚባልበት ብዙ ምክንያት ስላለ እዉነት ከሆነ የትኛዉ ምክንያት እንደሆነ ለመለየት ነዉ:: በዚህ ማጣራት መሰረት ተከሳሹ ወንጀሉን አልፈጸምኩም ያለዉ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ በወንጀሉ ቦታ ሳይሆን በሌላ ቦታ ስለነበረ መሆኑን ገለጸ::
ይህን የፍርድቤቱን አቀራረብ እንዴት ይገመግሙታል? ተገቢ አይደለም ይላሉ? ለምን?

በሌላ በኩል ተከሳሹ ከላይ ያቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ ፍርድቤቱ ዐቃቤህግን ምን እንደሚያመለክት ሲጠይቀዉ ተከሳሽ ለዚህ ክርክሩ የሚያቀርበዉን የማስረጃ አይነትና ይዘት ለፍርድቤቱ ያስመዝግብልኝ ብሎ አመለከተ::
ይህ የዐቃቤህግ አካሄድ ምን ያህል ተገቢ ነዉ? ከባልደረባዎ ጋር ይወያዩበት::

ፍርድቤቶች የዐቃቤህግ ምስክሮችን ምስክርነትም ሆነ የተከሳሽን ምስክሮች ምስክርነት ይዘት የሚገልጽ ማመልከቻዎች ግራ ቀኙን አያለዋዉጡም:: ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የሙስና ጉዳዮችን በሚያዩ ችሎቶች ያለዉን አሰራር ስንመለከት በተለዩ የሥነሥርዓት ድንጋጌዎች መሰረት ዐቃቤህግ የምስክሮችን ቃል ይዘት በመግለጫ ለተከሳሽ እንዲያደርስ ይደረጋል:: በተመሳሳይ ተከሳሽም ስለማስረጃዉ ቢያንስ ዝርዝር እንዲያቀርብ ይደረጋል:: ይህ ሁሉ የክሱን ዋና ጉዳይ ማየት ከመጀመር በፊት የሚከናወን ነዉ:: ስለዚህ ይህ ማስረጃን የተመለከተ የመግለጫ መለዋወጥ ለህጋችን እንግዳ አይደለም::

ያም ሆኖ በመደበኛዉ አሰራር የዐቃቤህግ ማስረጃ በክፊል (የጽሁፍ) ለተከሳሽ አስቀድሞ የሚደርሰዉ ቢሆንም ስለተከሳሽ ማስረጃ ምንም የሚደረግ ነገር ባለመኖሩ ዐቃቤህግ የተከሳሽ ማስረጃ ይዘቱ ይቅርና ስለመኖር አለመኖሩ እንኳ የራሱ ክርክር ከማለቁ በፊት ሳያዉቅ ቆይቶ

የተከሳሹ ክርክር መቅረብ ሲጀምር ስለሚያገኘዉ ያለበቂ ዝግጅት ቀርቦ የመስቀለኛ ጥያቄ ሂደትን ያከናዉናል:: ከዚህ የተነሳ አንዳንዴ በችሎት የሚስተዋሉ አጋጣሚዎች ይህን ማስረጃ የመገላለጽ ነገር አስቀድሞ ማድረግ አይቻልም ወይ የሚል ጥያቄ የሚጋብዙ ናቸዉ::

የጽሁፉ አዘጋጅ በተለያዩ አጋጣሚዎች ችሎት ላይ የሚከናወኑ ሂደቶችን እንዳስተዋለዉ የመከላከያ ማስረጃ ሲቀርብ የሚከተለዉ ይከናወናል፡፡ *ተከሳሽ የመከላከያ ክርክሩን በወንጀሉ ቦታ አልነበረኩም፣ በሌላ ቦታ ነበርኩ፣ ለዚህም የሚያዉቁ ምስክሮች (በተወሰነ ቀንና ሰዓት በአንድ ተለይቶ በተመለከተ ቦታ እንደነበርኩ) ያስረዳሉ በሚል ያስመዘግባል፡፡ ከዚህ በኋላ ዐቃቤ ህግ ጭብጡን በተመለከተ ዝርዝር ነገሮችን ከተከሳሹ ለማግኘት ተከሳሹን ወይም ጠበቃዉን ለረጅም ጊዜ እንዲጠይቅ ይደረጋል*::

ይህ አይነቱ አካሄድ የፍርድ ቤቱን ጊዜ የሚያባክን ነዉ:: ፍርድቤቶች ይህን አሰራር በዚህ ደረጃ የሚፈቅዱ ከሆነ ተከሳሹ መጀመሪያዉኑ ክሱን ሰምቶ ወንጀሉን ሲክድ ራሱን ለመከላከል ስለሚያቀርበዉ ማስረጃ መግለጫ እንዲሰጥ ቢያደርጉ ልዩነት ይኖረዋል ወይ? ዐቃቤህግስ እንዲህ እንዲደረግ በዚህ ደረጃ ሊጠይቅ አይገባም?

በወንጀሉ ጊዜና ቦታ አልነበርኩም የሚለዉ መከላከያና መስቀለኛ ጥያቄ፡- በርግጥ ዘወትር የሚቀርብ የተከሳሾች መከላከያ ክርክር በወንጀሉ ጊዜ በወንጀሉ ቦታ አልነበርኩም የሚል ከመሆኑ አኳያ ይህን መከላከያ አስመልክቶ የዐቃቤህግን የመስቀለኛ ጥያቄ ክህሎት በተመለከተ አንዳንድ ነጥቦችን አንስቶ መመርመር ተገቢ ነዉ:: ከላይ እንደተመለከተዉ ዐቃቤህግ ይህን መከላከያ አስመልክቶ ያለዉ ፍላጎት የፍሬነገር ዝርዝር ላይ በማተኮር መከላከያ ምስክሮች በፍሬነገር ዝርዝሩ ላይ የሚለያዩበትን አጋጣሚ በመፍጠር እንዳይታመኑ ማድረግ ነዉ:: ነገር ግን የዚህ ክርክር የተለየ ባህሪ ዕዉነትን ተመርኩዞ ሊቀርብና በቀላሉ ሊዋሸበት የሚችል መሆኑ ነዉ:: በዚህ መከላከያ ማስረጃ የሚነገረዉ ነገር ሙሉ በሙሉ የተከሰተ ዕዉነተኛ ታሪክ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ ምስክሮች በፍሬነገር ዝርዝር ላይ ተመሳሳይ ሊመስክሩ ይችላሉ:: ችግሩ የሚኖረዉ ይህ ታሪክ በርግጥ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ጊዜ የተከሰተ ታሪክ ነዉ ወይ የሚለዉ ዉስጥ ነዉ:: ምስክሮች በሌላ ጊዜ የተከሰተን ዕዉነተኛ ታሪክ በወንጀሉ ጊዜ እንደተፈጸመ አድርገዉ ለማቅረብ ተዘጋጅተዉ ቢቀርቡ ትልቁ ደካማቸዉ ጊዜዉን መቀየር ላይ ብቻ ነዉ:: ይህም ቀላል ነዉ:: ስለዚህ ዐቃቤህግ መስቀለኛ ጥያቄዉን ምን ላይ እንዲያተኩር ሊያደርግ ይገባል? በታሪኩ ላይ ወይስ ስለጊዜ በተነገረዉ ምስክርነት ላይ? እንዲህ ከሆነስ የተከሳሹ መከላከያ ክርክር (ጭብጥ) በሚቀርብበት ጊዜ የፍሬነገር ዝርዝር ፍለጋ የፍርድቤቱን ጊዜ በሚያባክን ሁኔታ ተከሳሹንና ጠበቃዉን በጥያቄና መልስ (ኢንተሮጌሽን ሊባል እስከሚችል) ማፋጠጥ ያስፈልጋል ወይ? ፍርድቤቶችስ የመከላከያ ክርክር አስቀድሞ እንዲገለጽ ማድረግ የለባቸዉም? ዐቃቤህግስ ይህን አስቀድሞ ሊጠይቅ አይችልም?

የመስቀለኛ ጥያቄ መርሆችና ቴክኒኮች፦ ዐቃቤህግ በመደበኛ የወንጀል ክስ ለመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ሲቀርብ ስለጉዳዩ በተለይም ስለምስክርነቱ አስቀድሞ ሳይዘጋጅ ማለትም ዕውቀት ሳይኖረዉ ነዉ:: መስቀለኛ ጥያቄ ሂደት እንኳንስ ያለቅድመዝግጅት ዝግጅትም ተደርጎ አስቸጋሪ ሥራ ነዉ:: የመከላከያ ምስክሮች ከመዋሸት እስከ ሆን ብሎ አለማስታወስ ድረስ መሰናክል ሊፈጥሩ ይችላሉ:: በመስቀለኛ ጥያቄ ሂደቱ ለዐቃቤህግ ተባባሪ ላይሆኑ ይችላሉ:: ስለዚህ ዐቃቤህግ በዚህ ሂደት ለማግኘት የሚፈልገዉን ምናልባትም ሊያገኝ የሚገባዉን ያለማግኘት ችግር ሊያጋጥመዉ ይችላል:: እንዲያዉም የራሱን ክስ ሊጎዳ የሚችል አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል:: ስለዚህ መስቀለኛ ጥያቄን ለማካሄድ ወይም ላለማካሄድ በከፍተኛ ጥንቃቄ መምረጥ አና ማካሄድ የግድ ነዉ:: ለዚህ ደግሞ አንዳንድ መርሆችንና ቴክኒኮችን ማወቅ ተገቢ ነዉ:: እነዚህ መርሆችና ቴክኒኮች በአሰራር ልማድ የምንፈጥራቸዉን ችግሮች ለማረም እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ ናቸዉ:: እነዚህን ቆየት ብለን የምናያቸዉ ሆኖ ከዚያ በፊት ስለመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ወሰን እና መጠን አንዳንድ ነገሮች እንይ::

በቅድሚያ ከላይ እንደተገለጸዉ መስቀለኛ ጥያቄ አስቸጋሪ ሂደት ነዉ:: አደጋዎች አሉት:: ስለዚህ መስቀለኛ ጥያቄ ማከሄድ ተመራጭ ላይሆን ይችላል:: መስቀለኛ ጥያቄ አለማካሄድ ምን ዉጤት አለዉ? በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 140 እንደተመለከተዉ መስቀለኛ ጥያቄ አለመጠየቅ በሌላዉ ወገን የተነገረዉን እንደማመን አያስቆጥርም:: ስለዚህ መስቀለኛ ጥያቄ ብዙም ባይደፈር ይመረጣል:: በተለይም የመስቀለኛ ጥያቄ ግብ ከሆኑት (የተቃራኒን ምስክርነት የማይታመን መሆኑን ማሳየት፣ በክሱ ላይ የደረሰዉን ጉዳት ማስተካከል፣ ወዘተ) አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ለማሳካት የምንችል ወይም ተገቢ ካልሆነ በቀር፣ ወይም ምስክሩ ለጉዳያችን የምንፈልገዉ መረጃ ብቸኛ ምንጭ ካልሆነ በቀር መስቀለኛ ጥያቄ ማካሄድ የሚመከር አይደለም::

ሆኖም ዘወትር እንደሚስተዋለዉ አንዳንድ ምስክሮች ባህሪያቸዉ ምንም ሳይጠየቁ መሄድ የለባቸዉም የሚያስብል ይሆናል:: በዚህ ጊዜ መስቀለኛ ጥያቄ ማንሳት የግድ ከሆነ ከላይ ሲባል እንደነበረዉ አደጋዉ የበዛ በመሆኑ መጠኑን ማሳነስ ይመከራል::

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 137(3) ስር መስቀለኛ ጥያቄ በዋና ጥያቄ ጊዜ በተመለሱ ነገሮች ዉስጥ ያለዉን ስህተት፣ አጠራጣሪ ወይም የማይታመን ቃል ለፍርድ ቤቱ ለመግለጽ ወይም ለማስተባበል የሚደረግ መሆኑ ተደንግጓል:: ስለዚህ ከዚህ የወጣ ጥያቄ ሲነሳ ተቃዉሞ ሊገጥም ይችላል:: ሆኖም በዋና ጥያቄ ከተፈጠረዉ ድንበር ወጥቶ መጠየቅ የሚቻልባቸዉ የተለዩ አጋጣሚዎች ይኖራሉ:: ለምሳሌ የምስክሩን ተዓማኒነት የሚመለከቱ ጥያቄዎች በዋና ጥያቄ ጊዜ ባይነሱም በጠቅላላዉ ምስክሩ የተናገረዉን ነገር ተዓማኒነት የሚመለከት ስለሚሆን ተቀባይነት ያለዉ አካሄድ ነዉ:: ለምሳሌ የተለመደዉ የተከሳሽ መከላከያ ክርክር (በወንጀሉ ጊዜ በወንጀሉ ቦታ አልነበርኩም) ሲቀርብ የሚነገረዉ ታሪክ የተፈጸመበትን ጊዜ ከወንጀሉ ጊዜ ጋር እንዲገጥም

የማድረግ ነገር ስለሚኖር ምስክሩ ጊዜን በመለየት ረገድ ስላለዉ ችሎታ ለማረጋገጥ በዚህ ዙሪያ ጥያቄ ቢነሳ ሊከለከል አይገባም:: ምስክሩ ተዓማኒነቱ ምን ያህል እንደሆነ ለማሳየት የሚረዳ በመሆኑ ተገቢ ነዉ::

መወያያ

በወንጀሉ ጊዜና ቦታ አልነበርኩም በሚለዉ ክርክር ዉስጥ ዐቃቤህግ ስለምስክሩ ጊዜን የመለየት ችሎታ ረዘም ያለ የመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ለመምራት በመፈለግ በዚሁ ነጥብ ላይ ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ሲያነሳ ተከሳሽ አጭብጥ ወጪ ነዉ የሚል ተቃዉሞ ቢያነሳና ፍርድቤት ለዚህ የዐቃቤህግ አቀራረብ ማብራሪያ ቢጠይቅ ዐቃቤህግ ምን ብሎ ሊያስረዳ ይችላል?

ከተዓማኒነት ጋር በተያያዘ ምስክሩ በነገሩ ዉስጥ ያለዉ ጥቅም ወይም ፍላጎት ሊታለፍ የማይገባዉ ነጥብ ነዉ:: ምስክሩ የሚሰጠዉ ምስክርነት ከነገሩ ዉስጥ ካለዉ ጥቅም ወይም ፍላጎት የተነሳ ከዕዉነት የራቀ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ በነገሩ ዉስጥ ጥቅም እንዳለዉ ማሳየት በሰጠዉ ምስክርነት ላይ ዕምነት እንዲታጣ ሊያደርግ ስለሚችል በዋና ጥያቄ አልተነሳም ተብሎ ቀሪ ሊደረግ አይገባም::

አንዳንዴ ምስክሩ ራሱ ለመስቀለኛ ጥያቄ በሚመልስበት ጊዜ በዋና ጥያቄ ጊዜ ላልተነሱ ሀሳቦች መንገድ ሊከፍት ይችላል:: በዚህ ጊዜ ምስክሩ ራሱ ባነሳዉ ነገር ላይ ሌላ መስቀለኛ ጥያቄ የማይጠየቅበት ምክንያት አይኖርም:: ስለዚህ ዐቃቤህግ እነዚህን አጋጣሚዎች በንቃት መጠባበቅ ይገባዋል፣ ለዚህም ምስክርነቱን በሚገባ ማዳመጥ ይኖርበታል፡፡

ከጭብጥ ከመዉጣት ሌላ በመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት የማይፈቀድ ነገር ምስክርን ማስፈራራት እና ማንጓጠጥ ነዉ:: ምስክሩ ዐቃቤህግ የሚፈልገዉን እንዲል መገደድ የለበትም:: ይህን ማድረግ የሚቻለዉ ክህሎት በተሞላዉ የአጠያየቅ ዘዴ መሆን አለበት:: አዘዉትሮ በፍርድቤቶች በሚደረግ ክርክር ጊዜ የሚስተዋል በህግ ባለሙያዎች (ዐቃብያነህግ፣ ጠበቆች፣ ዳኞች) የሚባል አንድ ነገር አለ:: ምስክሩ እነዚህ ባለሙያዎች እንደፈለጉት ወይም ዕዉነት ነዉ ብለዉ እንደሚያስቡት ሳይናገር በቀረ ጊዜ በሃሰት መመስከር በወንጀል እንደሚያስቀጣ ይነግሩታል:: ይህ ነገር ማስፈራራት ከመሆኑ በተረፈ ነገሩ ተሰምቶ ሳያልቅ እና ምስክሩ የተናገረዉ ሃሰት ይሁን ዕዉነት ሳይረጋገጥ በጉዳዩም ላይ በምስክሩም ላይ ፍርድ የመስጠት ያህል ይሆናል:: ከዐቃቤህግ የህግ ጠባቂነት ሚና አኳያም የሰዉን መብት የሚደነግጉ ህጎችን የመጣስ ዉጤት ይኖረዋል::

የመስቀለኛ ጥያቄዎች ባህሪያት (መሪ ጥያቄ)፡-- ይህ የጥያቄ አይነት በመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ዉስጥ በህግ የተፈቀደ ቢሆንም ዐቃቤህግ (ሌሎች ባለሙያዎችም) ሲጠቀሙበት አይስተዋልም:: በርግጥ ይህ የጥያቄ አይነት ስለሚያስከትለዉ መልስ ማወቅን ስለሚጠይቅና ዐቃቤህግ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸዉ ያለቅድመዝግጅት ስለሚቀርብ ይህን የጥያቄ አይነት ለመጠቀም አይደፋፈርም:: ሆኖም ዋና ጥያቄ የሚመስል ሂደት በማካሄድ ነገሮችን እንዲደገሙ ከማድረግና በዚህም ችሎትን ከማሰላቸት፣ ግፋ ሲልም የዐቃቤህግን ክስ የሚያፈርስ አጋጣሚ ከመፍጠር በዚያዉ በችሎት በተደረገች ዝግጅትም ቢሆን መሪ ጥያቄ በመጠየቅ ምስክሩን እንዳሻዉ እንዳይናገር መቆጣጠር ይመከራል:: በመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ዋናዉ ግብ ምስክሩን መቆጣጠር፣ የሚመሰክረዉን ነገር መወሰን፣ በዚህም ለመዋሸት ያለዉን ዝንባሌ ወዘተ ማስቀረት ነዉ:: በዋና ጥያቄ ጊዜ ሊነሱ የሚገባቸዉ ዝግ ያልሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳት ምስክሩ የሚናገረዉን ነገር ልቅ ማድረግ ሂደቱን ዐቃቤህጉ ሳይሆን ምስክሩ እንዲቆጣጠረዉ ማድረግ ይሆናል::

አጭርና ነጠላ ጥያቄ፡- የተከሳሽን ምስክር በመስቀለኛ ጥያቄ መቆጣጠር የሚቻልበት መንገድ ጥያቄዉን መሪ ጥያቄ በማድረግ ብቻ አይደለም:: ጥያቄዉን አጭር ማድረግም እንዲሁ በምስክሩ ላይ የበላይነትን ያስገኛል:: ጥያቄዉ ከአንድ በላይ ሃሳብ ከሌለዉ እና ርዝመቱም አጭር ከሆነ ምስክሩ ለዚሁ ብቻ መልስ እንዲሰጥ ሰለሚገደድ ብዙም መፈናፈኛ አይኖረዉም:: በተለይ ከአንድ በላይ ሃሳብ አለመያዙ ምስክሩ መርጦ የመመለስ ስራ እንዳይሰራ ያደርገዋል፣ የመልሱ ወሰን የታጠረ ይሆናል::
ከዚህ በተያያዘ ከአንድ በላይ የሆኑ ጥያቄዎችን አነባብሮ በአንድ ጊዜ መጠየቅ የሚገኘዉን መልስ ግልጽ እንዳይሆን ያደርገዋል:: አንድ መልስ ቢሰጥ ለየትኛዉ ጥያቄ እንደተመለሰ ማወቅ አይቻልም:: ስለዚህ እንደዋና ጥያቄ ጊዜ በአንድ ጊዜ አንድ ጥያቄ ብቻ ማንሳት ተገቢ ይሆናል::

መልሱ የሚታወቅ (የሚረጋገጥ) ጥያቄ፡- የመስቀለኛ ጥያቄ መልሱ የሚታወቅ ወይም ማስረጃ ሊቀርብበት የሚችል መሆን ይኖርበታል:: ግን ቀደም ሲል እንደተገለጸዉ ትልቁ ችግር ስለመከላከያ ምስክርነትም ሆነ ስለምስክሩ አስቀድሞ የሚሰበሰብ ማስረጃ የለም:: ስለዚህ የዐቃቤህግ መስቀለኛ ጥያቄዎች በዕድል፣ ባወጣ ያዉጣዉ ወዘተ ላይ ተመስርተዉ የሚጠየቁ ናቸዉ:: ሆኖም ማስረጃ በተሰበሰበባቸዉ አጋጣሚዎች ለምስክሩ የሚቀርብ መስቀለኛ ጥያቄ ሊመለስ የሚገባዉን መልስ የሚጠቁም ሊሆን ይገባል:: ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠዉ መልስ ምንም ይሁን ምን በቂ ስለሚሆን የሚገኘዉ መልስ ምንነት ስጋት አይፈጥርም:: የሚፈለገዉን መልስ ምስክሩ አመነም አላመነም ዉጤቱን አይቀይረዉም:: ምክንያቱም ቢያምን ዐቃቤህግ እንደሚፈልገዉ ሆነለት ማለት ሲሆን፣ ከካደ ደግሞ ማስረጃ ስላለ ምስክርነቱን ማስተባበልና በዚህም ምስክሩ ተዓማኒነት የሌለዉ መሆኑን ማሳየት ይቻላል::

የመስቀለኛ ጥያቄዎች አደረጃጀት፡- ዉጤታማ መስቀለኛ ጥያቄ በጥያቄዎች አይነት ብቻ የሚወሰን አይደለም:: የጥያቄዎቹ ቅደም ተከተልም (ቅንብር) የራሱ አስተወጽዖ ይኖረዋል:: በተለይ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ምስክሩን በሚገባ መቆጣጠር እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑ አኳያ የጥያቄዎቻችን አወቃቀር ይህን የመቆጣጠር ችሎታ የሚያሳጣ መሆን የለበትም:: ስለዚህ የተቃራኒ ወገንን ምስክር የምንጠይቅ እንደመሆኑ በቀላሉ የምንፈልገዉን ነገር ለማግኘት አስቸጋሪ ስለሚሆን የጥያቄዎቻችን አወቃቀር የምስክሩን ወዳጅነት የሚያስገኝ እንዲሆን የግድ ነዉ::

ዐቃቤህግ መስቀለኛ ጥያቄ ሊጠይቅ ከወሰነ በዚህ ጥያቄ ሊያሳካ የፈለገዉን ነገር በሂደቱ መጀመሪያ ላይ መግለጽ የለበትም:: ይህ ግብ በምስክሩ ከታወቀ የተቃራኒ ወገን ምስክር እንደመሆኑ የመስቀለኛ ጥያቄዉ ሂደት ወደዚህ ግብ እንዲደርስ መፍቀዱ አጠራጣሪ ነዉ:: ስለዚህ ይህን ግብ የሚደብቅ የጥያቄዎች ቅደምተከተል መኖር አለበት::

ከዚህ የተነሳ በመነሻዉ ላይ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ከምስክሩ ጋር ፍጥጫን የማያስነሱ፣ ምስክሩ በቀላሉ ሊያምናቸዉ ወይም ሊስማማባቸዉ የሚችሉ ፍሬነገሮችን የሚመለከቱ መሆን ይገባቸዋል:: ይህን ማድረግ በዐቃቤህጉና በተከሳሽ ምስክር መካከል ሰላማዊ ሁኔታ ይፈጥራል:: ስለዚህ ከምስክሩ የሚፈለገዉን ለማግኘት ቀላል ይሆናል፣ ቢያንስ ምስክሩ መሰናክሎችን ከመፍጠር ይታቀባል::

ይህ ማለት ደግሞ ዐቃቤህግ ለክሱ እጅግ አስፈላጊ የሚላቸዉን ነጥቦች መጀመሪያ ላይ ማንሳት የለበትም ማለት ነዉ:: እነዚህን ጉዳዮች ከመነሻዉ ከገለጸ ምስክሩ የመስቀለኛ ጥያቄዉን ዓላማ በቀላሉ ማወቅ ስለሚችል እና ይህም ምስክሩ በዋና ጥያቄ ጊዜ ከተናገረዉ ሊቃረን ስለሚችል ምስክሩ ይህን የተፈለገ ነገር ለመስጠት አይፈቅድም:: በሚችለዉ መንገድ ራሱን ከመቃረን ለማዳን የማስተካከያ መረጃዎችን ከመግለጽ ያለፈ ነገር ለመፈጸም ፈቃደኛ እንዳይሆን ያደርገዋል:: ስለዚህ ዐቃቤህግ መነሻዉ ላይ ከዋና ጥያቄ ሂደት በተቃራኒ ዋና ነጥቦችን ሳይሆን ዝርዝር ጉዳዮችን (በተቻለ መጠን ምስክሩ የማይክዳቸዉን) እንዲያነሳ ይመከራል::

ከዚህ ሌላ ዐቃቤህግ የመስቀለኛ ጥያቄ ዓላማዉን ለመደበቅ በጥያቄና መልሱ ሂደት ጊዜ ከአንድ የጥያቄ ሃሳብ ወደሌላዉ በመዝለል ምስክሩ የነገሩን አቅጣጫ እንዳይገነዘብ ማድረግ ይችላል:: ለዚህም ጥያቄዎቹ በተለያየ ርዕስ ስር እንዲደራጁ ሊያደርግ ይገባል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ የአካባቢ ማስረጃን አስመልክቶ ከዋና ጥያቄ ጋር በማያያዝ ያነሳነዉ ሃሳብ ለመስቀለኛ ጥያቄም አግባብነት ይኖረዋል:: በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ዓላማዉ ምስክሩ የዐቃቤህግን የክርክር አቅጣጫ እንዳይገነዘብ ማደረግ በመሆኑ የአካባቢ ማስረጃን የሚመለከቱ ጥያቄዎች እነዚህን ማስረጃዎች በአንድ ላይ የማሰባሰብ ባህሪ እንዳይኖራቸዉ ማድረግ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ከተሰባሰቡ ትርጉማቸዉ ግልጽ ስለሚሆን ምስክሩ የክርክሩን አቅጣጫ በቀላሉ እንዲረዳዉ በማድረግ

መሰናክል እንዲፈጥር ይገፋፋዋል። ስለዚህ መስቀለኛ ጥያቄዎች የአካባቢ ማስረጃዎች እንዲበታተኑ የማድረግ ችሎታ ሊኖራቸዉ ይገባል። ለዚህም ከላይ እንደተመከለተዉ የጥያቄዎችን ቅድም ተከተለ በማዘባረቅ ከርዕስ ወደርዕስ መሄዛር አስፈለጊ ነዉ።

ከጥያቄዎች ቅደም ተከተል ጋር በተያያዘ አዘዉትሮ የሚታይ ስህተት አለ። በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ምስክሩ ሊክዳቸዉ የማይችሉ ፍሬነገሮችን መሰረት በማድረግ ዐቃቤህግ ለሚያቀርባቸዉ ጥያቄዎች በሚገኙ መልሶች የሚገነባ ታሪክ ሊኖር ይችላል። ከዚህ በኋላ የዚህን ሁሉ ጥያቄና መልስ እንድምታ (ድምዳሜ) ምስክሩ እንዲናገር ከተጠየቀ መልሱ የተከሳሹን ክርክር የሚጎዳ ከመሰለዉ ወይም ከሆነ ምስክሩ የጥያቄዉ አቅጣጫ ሰለሚገባዉ ቀደም ሲል የሰጣቸዉን መልሶች የሚያስተካክል መልስ ሊሰጥ ስለዚህ ለክሱ የሚረዳዉን ነገር የመደበቅ ተግባር ሊፈጽም ይችላል። ይህም እንኳ ባይሆን ተከሳሹ ወይም ጠበቃዉ በክርክሩ ላይ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ የደረሰዉን ጉዳት በድጋሚ ጥያቄ ጊዜ የማስተካከል ስራ እንዲሰራ የማባነን ዉጤት ይኖረዋል። ይህም ካልሆነ ፍርድቤቱ ራሱ በማጣሪያ ጥያቄ ጊዜ ነገሩን እንዲያነሳ ምስክሩም በዚህ አጋጣሚ ነገሩን የሚያድበሰብስ ወይም የሚያርም ተግባር እንዲፈጽም የማስታወስ ዉጤት ይኖረዋል። በተግባር ሲደረግ የሚስተዋለዉም እንዲህ ያለ ዉጤትን የሚያመጣ አጠያየቅ ነዉ።

ስለዚህ ይህን የነገሩን ማሰሪያ ጥያቄ ዐቃቤህግ መጠየቅ የለበትም። ቀላልና ተራ በሚመስሉ ጥያቄዎች የተገነባዉ ታሪክ እንድምታ ለፍርድቤቱ የሚተዉ ነዉ። ምናልባት ለፍርድቤቱ ግልጽ የማይሆን ቢሆን በመስቀለኛ ጥያቄ የተሰጡ መልሶች የሚጠቁሙት ድምዳሜ ምን እንደሆነ በክርክር ማቆሚያ ንግግር ጊዜ መግለጽ ይቻላል።

ነገር ግን አሁን ባለዉ አሰራር ይህ ከላይ የተመለከተዉ የአሰራር አቅጣጫ ምን ያህል ያስኬዳል? የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነዉ። ምክንያቱም የክርክር መዝጊያ ንግግር ወይም በተለምዶ አጠራሩ የመፋረጃ ሃሳብ እንዲቀርብ የሚያደፋፍሩ ፍርድቤቶች ጥቂት ከመሆናቸዉም በላይ እንዲቀርብ የሚያደርጉትም ቢሆኑ በአብዛኛዉ በጽሁፍ እንዲቀርብ የሚያደርጉ ሰለሆነ እንዲሁም የቀረበዉን ሃሳብ የሚጠቀሙበት ማለትም በዉሳኔ ጊዜ ከግምት የሚያስገቡት ፍርድቤቶች በእጅጉ ጥቂት በመሆናቸዉ ዐቃቤህግ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ያስመሰከራቸዉ ፍሬነገሮች ድምር ዉጤት ምን እንደሆነ በክርክሩ ጊዜ (በመስቀለኛ ጥያቄ ማጠናቀቂያ ጊዜ) ካልጠቆመ እንዲህ የሚያደርግበት መድረክ አያገኝም። ከዚህ የተነሳ ዐቃቤህግ ከተከሳሽ ምስክር ጋር በመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ዉስጥ ወይም ማሳረጊያ ላይ የምስክርነቱን እንድምታ እመን አትመን እሰጥ አገባ ዉስጥ ሲገባ ይታያል። ስለዚህ ፍርድቤቶች የክርክር ማቆሚያ ንግግርን አሰራር እንዲያከብሩ ዐቃቤህግ መወትወት ዳኞችም ይህን አሰራር ባህል እንዲያደርጉት የግድ ነዉ።

ከዚህ በላይ ያየናቸዉ የጥያቄ አደረጃጀት ስራዎች ብቸኛ አይደሉም:: በርከት ያሉ በተለያዩ በለሙያዎች የሚቀርቡ ዘዴዎች አሉ:: ሆኖም ከላይ ያነሳናቸዉ ዘዴዎች ከኛ የአሰራር ልምድ ጋር ቁርኝት ስላላቸዉ ሊጠቀሱ በቅተዋል::

ሌሎች ቴክኒኮች፦ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ፣ ቅድመዝግጅት ካለ፣ ጥያቄዎችን በጽሁፍ አዘጋጅቶ የመቅረብ ነገር ሊኖር ይችላል:: ነገር ግን እንዲህ አይነቱ አቀራረብ መልካም አይደለም:: ጥያቄዎቹ በጽሁፍ ከተዘጋጁ ወይ እያነበቡ ለመጠየቅ ነዉ አለያም ሸምድዶ ከሃሳብ እያስታወሱ ለመጠየቅ ነዉ:: ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸዉ:: ወረቀት ላይ የምናተኩር ከሆነ ወይም በአዕምሯችን ስለምናስታዉሰዉ ነገር የምናስብ ከሆነ ምስክሩን ዓይንለዓይን አንገናኝም ማለት ነዉ:: በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ከምስክሩ ጋር የዓይንላይን ግንኙነት መኖር ምስክሩን ለመቆጣጠር ይረዳል:: ከዚህም ሌላ ያልተጠበቀ፣ ለክሱ የሚጠቅሙ አጋጣሚዎችን ለመጠቀም በጥያቄና መልሱ ሂደት ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል:: ጥያቄን ከወረቀት ላይ ወይም ከአዕምሮ ዉስጥ ማንበብ ይህን አትኩሮት ስለሚነፍግ በዚህም ረገድ ዐቃቤህግ ብሎም ክሱ ተጎጂ ይሆናሉ:: በተለይ ጥያቄዉ በርከት ያለ ከሆነ አንዱ ጥያቄ ተመልሶ ሌላ ለመጠየቅ በዝርዝሩ ዉስጥ የሚቀጥለዉ ጥያቄ ቦታ እንዳይጠፋ በማሰብ አትኩሮትን ወደዚሁ ጽሁፍ ለማድረግ መገደድ ይኖራል::
ከዚህ የተሻለዉ አማራጭ ጥያቄዉን በዝርዝር አለመጻፍ ነዉ:: ዝግጅቱ የግድ በጽሁፍ መሆን ካለበት የጥያቄዎቹን ሃሳቦች የያዙ ርዕሶችን ዝርዝር (አዉትላይን) አዘጋጅቶ መቅረብ ይመረጣል:: ርዕሶቹን ብቻ ከወረቀቱ ላይ በመመልከት ጥያቄዎቹን ከራስ ማመንጨት ይገባል::

አትኩሮትን ወደጥያቄና መልሱ ሂደት ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ ከፍ ብሎ ተጠቅሷል:: ከዚህ በተያያዘ ለመሰቀለኛ ጥያቄ የሚሰጡ መልሶችን ዐቃቤህግ ማድመጥ ይኖርበታል:: ለክሱ ገንቢ የሆኑ አጋጣሚዎችን ለመጠቀም የሚረዳ ከመሆኑም በላይ ምስክሩ ጥያቄዉን እየሸሸ የሚመልስ ከሆነ ይህን አስተዉሎ ጥያቄዉ እንዲመለስ ለማስገደድ (ምስክሩን ለመቆጣጠር) የሚያስችል ነዉ:: ከዚህ ከማድመጥ የሚያሰናክለዉ አንዱ ከላይ እንደተመለከትነዉ ጥያቄን በዝርዝር ጽፎ ቀርቦ በንባብ መጠየቅ ሲሆን ሌላኛዉ ደግሞ ምስክርነቱን በዝርዝር መጻፍ ነዉ:: ሰለዚህ እነዚህን የአሰራር ዘዴዎች ወይም ባህሪዎች ዐቃቤህግ ሊያስወግድ ይገባል::
አንዳንድ ጊዜ የተቃራኒ ወገን ምስክር ሳያስበዉ ወይም ከዐቃቤህግ የአጠያየቅ ብቃት የተነሳ ለክሱ ጠቃሚ ምስክርነት ሊሰጥ ይችላል:: በሌሎች አጋጣሚዎች ደግሞ ክሱን የሚጎዳ ነገር ሊመሰክር ይችላል:: በዚህ ጊዜ ዐቃቤህግ እንደተሰጠዉ ምስክርነት ጠቃሚነት ወይም ጎጂነት ስሜቱ የሚለዋወጥ ከሆነ ምስክሩ በሰጠዉ ምስክርነት እያደረሰ ያለዉን ዉጤት በሚገባ

እንዲገነዘብ ስለሚያደርገዉ የተከሳሹን ክርክር የሚጎዳዉን ምስክርነት ያስተካክላል፣ የዐቃቤህግን ክስ የጎዳበትን ምስክርነት በማጠናከር የበላይነቱን ይዞ የክርክሩን ሂደት የመቆጣጠሩን ሚና ከዐቃቤህግ ይነጥቃል።

የተከሳሽ ምስክር ለዐቃቤህግ ክስ ገንቢ የሆነ ምስክርነት ከሚሰጥባቸዉ አጋጣሚዎች አንዱ መዋሸት ነዉ። መዋሸቱን የምናዉቅ ከሆነ ከምስክርነቱ በተቃራኒ የሆነዉን ዕዉነተኛዉን ታሪክ የሚያሳይ ማስረጃ አለን ማለት ነዉ። ስለዚህ ምስክሩ ሲዋሽ ካገኘነዉ በዚሁ ዉሸቱ እንዲቀጥልበት የሚያደርጉ ጥያቄዎችን ማንሳት እንጂ መዋሸቱን ያወቅንበት መሆኑን የሚገልጽ ምንም ነገር ማድረግ የለብንም። ምክንያቱም ይህን ከገለጽን የዋሸበትን ሁኔታ ያስተካክላል፣ ስለዚህ ዐቃቤህግ ምስክሩ የማይታመን ወይም የሚዋሽ መሆኑን የሚያስረዳበትን አጋጣሚ ያጣል ማለት ነዉ።

በብዙ አጋጣሚዎች አላዋቂ መስሎ ላለመታየት በሚደረግ ጥረት ክርክርን መጉዳት ሊከተል ይችላል። ስለዚህ በማያዉቁት ጉዳይ ጥያቄ ከመጠየቅ አለመቦዘን ተገቢ ነዉ። ለምሳሌ በባለሙያ ምስክርነት ጊዜ ለባለሙያዉ ወይም ስለጉዳዩ ዕዉቀት ላላቸዉ ሰዎች ተራ የሆነ ነገር ሁሉ ለዐቃቤህግ ግልጽ ላይሆን ይችላል። ስለዚህ አላዋቂ ላለመምሰል የባለሙያ ምስክርነት በሚነገርበት ጊዜ ነገሩ እንደገባዉ ሰዉ ዝም ብሎ ማዳመጥ ጉዳቱን ማወቅ የሚቻለዉ ነገሩ ካለቀ በኋላ ሰለሚሆን ጥንቃቄ ይፈልጋል። በዚህ ረገድ ግልጽ ያልሆነን ነገር ማብራሪያ እንዲሰጥበት መጠየቅ ሊያሳፍር አይገባም፣ ምንም ያህል ተራ ነገር ቢሆን ወይም ቢመስል።

ቀደም ሲል ለማየት እንደተሞከረዉ መስቀለኛ ጥያቄ አደጋ ያለዉ ሂደት ነዉ፣ እንደተገኘ የሚገባበት አይደለም። ጥንቃቄ ያሻዋል። ተመራጭ ሆኖ ወይም አማራጭ የሌለዉ ሆኖ ጥያቄዉ መካሄድ ያለበት ከሆነ የተመጠነ ሊሆን ይገባዋል። በዚህ ጊዜ ምስክሩን ለመቆጣጠር መቻል ያስፈልጋል። ለዚህም የማያጨቃጭቁ ጥያቄዎችን ማንሳት አንዱ ከምስክሩ ጋር ያለመፋጠጥ ሁኔታ መፍጠሪያ መንገድ ሲሆን ሌላዉ የጥያቄዉን ሂደት ዓላማ መደበቅ መቻል ነዉ። ይህ ማለት ግን ምስክሩን ማፋጠጥ ወይም ማስጨነቅ በማንኛዉም አጋጣሚ ተገቢ አይደለም ማለት አይደለም። ተቃራኒ ምስክር እንደመሆኑ የምንፈልገዉን ነገር በቀላሉ ሊሰጠን አይችልም ወይም አይፈቅድም። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ፍጥጫ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ትልቁ ጥያቄ ግን መቼ የሚለዉ ነዉ። ይህን ነገር መቼ ማድረግና አለማድረግ እንዳለብን የምናዉቅባቸዉን አንዳንድ ሁኔታዎች መለየት ያስፍልጋል።

ምስክርን ማስጨነቅ ወይም ማፋጠጥ ተገቢ የሚሆንበት ጊዜ ምልክቶች - የምስክሩ መረጋጋት አለመቻል፣ ከጠበቃዉ ርዳታን መጠበቅ፣ መናደድ ወይም ማድበስበስ መጀመር፣ የጠበቃዉ ማደናገሪያ ወይም አቅጣጫ ማስቀየሪያ ተቃዉሞዎች መበራከት - እነዚህና መሰል ሁኔታዎች ምስክሩ ለማፋጠጥ የተጋለጠ መሆኑን ጠቋሚ ናቸዉ። በዚህ ጊዜ ምስክሩ የደበቀዉን

ለማዉጣት ወይም ነገሮችን ማሳሳት ወይም ማዘባረቅ ጀምሮ ከሆነ የበለጠ ነገር የሚያበላሽበት ሁኔታ ዉስጥ መሆኑን መረዳትና ማፋጠጡን ማጠንከር ያስፈልጋል::

በዚህ ሁኔታ የተጀመረ ማፋጠጥ ቢኖርም ምስክሩ እየጠነከረ ከመጣና በቀላሉ የሚፈታ ሰዉ ካልሆነ ማፈግፈግ - መተዉ ተመራጭ ነዉ::

ምስክሩን ማፋጠጥ ተገቢ የማይሆንባቸዉ አጋጣሚዎች ሲኖሩ በቀጥታ ማጥቃትን ማስቀረት ተገቢ ነዉ:: ይህ ተገቢ የሚሆንባቸዉ ሁኔታዎች ባብዛኛዉ ሃዘኔታን ወይም አክብሮትን የሚያገኙ ሰዎች ምስክር የሆኑባቸዉ አጋጣሚዎች ናቸዉ:: እነዚህም - ህጻናት፣ አዛዉንት፣ የሃይማኖት ሰዎች ወይም አባቶች ወዘተ ናቸዉ:: በነዚህ አጋጣሚዎች በቂና አስተማማኝ ማስረጃ ካልኖረ በቀር እንደዚህ አይነት ሰዎችን ማፋጠጥና ማስጨነቅ በዳኞችና ሂደቱን በሚከታለዉ ህጎብረተሰብ ፊት የሚያስጸይፍ ሊሆን ስለሚችል ዉጤቱ አፍራሽ ይሆናልና ይህ አይነቱን አቀራረብ መተዉ ተገቢ ነዉ::

ምስክርን ስለማስተባበል፦ ከመስቀለኛ ጥያቄ ሂደት ጋር የማይነጣጠለዉ ይህ ምስክርን የማስተባበል ነገር በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 145 የተፈቀደ ነዉ:: ይህ ህግ ተከሳሽ የዐቃቤህግን ምስክር የሚያስተባብልበትን ሥነሥርዓት ብቻ የሚደነግግ ይመስላል:: ሆኖም በፖ/ሊስ ጣቢያ የተሰጠ ምስክርነት ጽሁፍ ለምስክርነት ማስተባበያ ይሆን ዘንድ ከመፈቀዱ በፊት ለፍርድቤት የሚቀርበዉ በተከሳሽ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በዐቃቤህግም ጭምር ነዉ:: ከዚህ በኋላ ፍርድቤት ጽሁፉን ለማስተባበያነት እንዲሰጠዉ የሚያደርገዉ ለተከሳሹ ነዉ::

መወያያ
በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 145 በተቋቋመዉ ድንጋጌ መሰረት ዐቃቤህግ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ በፖ/ሊስ ጣቢያ በተሰጠ የምስክርነት ጽሁፍ አማካኝነት የተከሳሽን ምስክር ማስተባበል አልተፈቀደለትም ማለት ይቻላል?

ምናልባት በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጽሁፉ ለተከሳሹ ይደርሰዋል ሲል ዐቃቤህግን ያለመጥቀሱ ይህ ጽሁፍ ለማንም ከመድረሱ በፊት ከምርመራ መዝገቡ ጋር የሚደርሰዉ ለዐቃቤህግ ስለሆነ እንዲደርሰዉ ማድረግ ትርጉም አልባ ስለሚሆን ይሆን?

ያም ሆነ ይህ በተለመደዉ አሰራር መሰረት ዐቃቤህግ የራሱን ምስክር በተመለከተ ቃሉን እየለወጠ መሆኑን ለማስረዳት በፖ/ሊስ ጣቢያ የሰጠዉን ቃል ጽሁፍ ለምስክሩ አሳይቶ ፊርማዉን እንዲያረጋግጥ ካደረገ በኋላ ለፍርድቤት በማቅረብ ሲያስወስን ይታያል:: በተመሳሳይ ሁኔታ የተከሳሹ ምስክር በፖ/ሊስ ምርመራ ጊዜ የሰጠዉን ቃል ጽሁፍ ለማስተባበያነት እንዲታይለት ቢጠይቅ ምን ስህተት አለዉ? የተከሳሽ ምስክር በፖ/ሊስ ጣቢያ የምስክርነት ቃል

ሊያስመዘግብ ይችላል? የተከሳሽ ምስክር በወንጀል ምርመራ ጊዜ በጉዳዩ ላይ ቃሉን በምስክርነት ከሰጠ በኋላ ዐቃቤህግ ማስረጃ አድርጎ ሳይቆጥረዉ ቢቀርና ተከሳሽ ምስክሩ ቢያደርገዉ ለፖ/ሊስ ምስክርነቱን የሰጠ ምስክር ሊባል አይችልም?
በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የሚደረገዉ ማስተባበል ቀድሞ በተሰጠ ቃል ላይ የተመረኮዘ ነዉ:: ሆኖም የማስትባበል ስራ ቀደም ሲል በምስክሩ በተደረገ ሌላ ተግባርም ሊከናወን ይችላል:: እንዲሁም የምስክሩን ባህሪ (ምናልባትም የመዋሸት) እና በጉዳዩ ዉጤት ምስክሩ የሚኖረዉን ጥቅም በማሳየት ምስክሩን ማስተባበል ይቻላል::

ከወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 145 ዉጪ ያሉ ምስክር ማስተባበያ ዘዴዎች፡- የቀድሞ የምስክር ቃልንም በተመለከተ ህጉ በፖ/ሊስ ጣቢያ የተመዘገበን ቃል ብቻ ይገልጻል:: ቀደም ሲል በፍርድቤት በማንኛዉም ጉዳይ የተመዘገበ ቃልስ ምስክሩን ለማስተባበል አይዉልም? የቀዳሚ ምርመራ ፍርድቤት የመዘገበዉ ምስክርነት ለዚህ አገልግሎት ማዋል አይቻልም? በክስ መስማት ጊዜ በፍርድቤት ከሚደረግ የቃል ምዝገባ ሌላ ቃልን ለመመዝገብ ብቻ በሚሰራ ፍርድቤት ቃል ሊመዘገብ አይችልም (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 35)? ምስክሩ ባለዉ የሥራ ኃላፊነት መሰረት የጻፋቸዉ ጽሁፎች ወይም ደብዳቤዎች ምስክሩን ለማስተባበል አያገለግሉም?
በነዚህ በሁሉም ሆነ በፖ/ሊስ ጣቢያ ቃል ምስክርን ለማስተባበል አስቀድሞ ይህን ቃል ወይም መጻጻፍ እና ይዘቱን ማወቅ እንደሚያስፈልግ አያጠያይቅም:: ለዚህ ደግሞ ከዚህ በፊት እንደተገለጸዉ ዝግጅት ማድረግ የማይታለፍ ይሆናል:: ለዚህም አስቀድሞ ስለተከሳሹ ምስክር እንዲሁም ስለመከላከያ ክርክሩ ማወቅ ያስፈልጋል:: ሆኖም ይህ ክርክር እንዲገለጽለት ዐቃቤህግ ፍርድቤትን መጠየቅ ይችላል ወይ የሚለዉ የዘወትር ጥያቄ ነዉ?

4. የክርክር መክፈቻና መዝጊያ ንግግር

ከዚህ በላይ ያየነዉን የክርክር አካሄድና ሌሎችም ለማከናወን ዐቃቤህግ አስቀድሞ የክርክሩን መክፈቻ ያቀርባል:: የክርክር መክፈቻ ንግግር በአንግሎአሜሪካ ሥርዓቶች የሚሰጠዉን ያህል አገልግሎት በኢትዮጵያ ባይሰጥም የክርክሩን ድንበር ለመወሰን ይረዳል:: በዚህ መሰረት የተሻለ የክርክር መክፈቻ ተደረገ ሲባል ስለያንዳንዱ ማስረጃ ጭብጥ ተያዘ ማለት ነዉ::
በርግጥ ይህ መክፈቻ ባግባቡ ቢደረግ ለፍርድቤት የማስረጃን ተቀባይነት ለመወሰንም ዕድል ይሰጣል:: አቀራረቡን በተመለከተ ዐቃቤህግ ካለዉ የህግ ጠባቂነት ልዩ ስፍራ አኳያ በትክክል (ኦብጀክቲቭሊ) እና ያለአድልዎ ሊያቀርበዉ ይገባል:: ፍሬነገሮችን እንዳሉ ያለግምገማ እና

ያለድምጻሜ ማቅረብ ይጠበቅበታል:: ፍሬነገሮቹ ዕዉነትና በማስረጃ ሊረጋገጡ የሚችሉ መሆን አለባቸዉ:: እንዲህ ካልሆነ የክርክሩ መክፈቻ በትክክል የቀረበ ሊባል አይችልም::

መክፈቻዉ ሲቀርብ በቃል ነዉ ወይስ በጽሁፍ? የሙስና ጉዳዮችን የሚያዩ ፍርድቤቶች ብዙ ጊዜ ክሱን መስማት ከመጀመራቸዉ በፊት ግራ ቀኙን ስለክርክሮቻቸዉና ማስረጃዎቻቸዉ በጽሁፍ መግለጫ እንዲለዋወጡ ያደርጋሉ:: ይህ መግለጫ ማስረጃዎችን የሚዘረዝርና ስለይዘታቸዉ የሚገልጽ ነዉ:: የቅድመክስ ሂደት ካስፈለገ ፍርድቤቱ ነገሩን መርምሮ ዉሳኔ የሚፈልጉ ጭብጦችን ከያዘ በኋላ እነዚህኑ ለግራ ቀኙ በብይን መልክ ይገልጽላቸዋል:: ከዚህ በኋላ ምስክር ወደመስማት ይገባል:: ስለዚህ መክፈቻዉ በጽሁፍ በመሆኑ ፎርሙ ትክክል አይደለም ሊባል ይችላል? እነዚሁ ፍርድቤቶች ቅድመክስ ክርክር የማያካሂዱ ከሆነ ዐቃቤህግ በቃል ጭብጥ እንዲያስይዝ ይጠይቃሉ:: በሌላ አጋጣሚ በመደበኛ ክርክሮች ሁልጊዜም መክፈቻ ሊባል የሚችለዉ የክርክሩ አካል የሚቀርበዉ ጭብጥ በመስጠት መልክ ሆኖ በቃል ነዉ:: በርግጥ ጉዳዮቹ ሰፋ እና ወሰብሰብ ሲሉ ዐቃቤህግ ጭብጡን በጽሁፍ ይዞ ቢቀርብም በንባብ እንዲያስሰማ ሲደረግ ይስተዋላል:: ጥሩ ምሳሌ የሚሆነዉ የቀይ ሽብር ክሶችን ይሰሙ የነበሩ አንዳንድ ችሎቶች ይከተሉት የነበረዉ አሰራር ነዉ:: እንዲያዉም እነዚህ ችሎቶች በግልጽ ዐቃቤህግን የመክፈቻ ንግግር አድርግ ብለዉ ይጠይቁ ነበር:: በጽሁፍ የቀረበ የክስ መክፈቻ በንባብ ተሰምቶ ክርክሩ ይቀጥላል:: ስለዚህ ይሽኛዉ በቃል ስለቀረበ ትክክለኛዉን ፎርም ተከትሏል ሊባል ይችላል?

በየትኛዉም ፎርም ይቅረብ የክርክር መክፈቻ ለተከሳሹ ሊገባዉ ስለሚያስፈለግ ቋንቋዉ ቀላል መሆን አለበት:: የህግ የሙያ ቋንቋ መሆን የለበትም::

ክርክሩ ሲጀመር መክፍቻ እንደተደረገለት ፣ ሲያበቃ ደግሞ የመዝጊያ ሥነሥርዓት ይኖረዋል:: እንዲያዉም ይህን የሚመለከተዉ ድንጋጌ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 148 በግልጽ እንደሚያሳየዉ ይህ መዝጊያ የክርክር ማቆሚያ ንግግር ነዉ:: ስለዚህ በቃል ሊሆን ይገባል:: ከዚህ አኳያ አሁን ያለዉ አሰራር ምን ያህል ትክክል ነዉ? ምክንያቱም የመፋረጃ ሃሳብ እንዲቀርብ የሚጠይቁ ጥቂት ችሎቶችም ቢሆኑ በቃል ለመቀበል ፈቃደኛ አይደሉም:: ግራቀኙ ከፍርዱ በፊት መፋረጃ ሃሳባቸዉን ከመዝገቡ ጋር እንዲያያይዙ ነግረዉ ጉዳዩን ለመወሰን ይቀጥራሉ::

በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 148 እንደተመለከተዉ የንግግር ማድረጊያ ቅደምተከተል አለ:: የመከላከያ ማስረጃ እንዳበቃ ዐቃቤህግ አስቀድሞ ክርክሩን ይዘጋል:: ከዚያ ተካሰሽ ይናገራል:: ሁልጊዜም ቢሆን ተከሳሹ የመጨረሻ ተናጋሪ ነዉ:: ይህ ማለት በግራ ቀኙ ከአንድ ጊዜ በላይ ምልልስ ይኖራል ማለት ይሆን? እንዲያ ከሆነ የግራ ቀኙ የክርክር መዝጊያ ንግግር ክርክር ነዉ ማለት

ነው:: ስለዚህ ይህ ክርክር ግራቀኙ ባሉበት ሊቀርብ ይገባል ማለት ነው:: ስለዚህ ይህ ንግግር በቃል መሆን የለበትም?

በክርክር መክፈቻ ጊዜ እንዳስተዋልነው አይነት ክልከላዎች በክርክር መዝጊያ ጊዜ አይታዩም:: በፍሬነገርም ሆነ በህግ ነጥቦች ላይ ግምገማ፣ ክርክር እንዲሁም ድምዳሜ መግለጽ ይቻላል::

ይህ ንግግር የጠቅላላው ክርክር መቋጫ ስለሆነ በክርክሩ ለማሳየት የተፈለገው ነገርና የቀረቡት ማስረጃዎች ግንኙነት ምን እንደሆነ፣ በህግ የሚጠበቀውን ማሟላቱን፣ ከተቃራኒው ወገን ክርክር የበለጠ ሊታመን የሚገባው የሚሆንበትን ምክንያት፣ (ዝርዝር ፍሬነገሮችን፣ በተቃራኒ ወገን መስቀለኛ ጥያቄ ተበታትነው ሊሆኑ የሚችሉ የአካባቢ ማስረጃዎችን ማሰባሰብና ስለሚሰጡት ትርጉም የመቋጫ ክርክር ማድረግ፣ ስለምስክሮች ተዓማኒነት እና ምስክርነቱን ለመስጠት የተገፋፉበትን ምክንያት፣ የተቀራኒን ወገን ማስረጃ አለመጣጣምና ስህተት ወዘተ ከቀረበው ማስረጃ በመነሳት መተንተንና መከራከር)

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከተከሳሽ ምስክርና ጠበቃ የመስቀለኛ ጥያቄውን አቅጣጫ ወይም ዓላማ ለመደበቅ ሲባል ዐቃቤህግ ያስመሰከራቸውን አንዳንድ ፍሬነገሮች ሳይቋጭ ሊተዋቸው ይችላል (አስፈላጊ ስለሆነ):: እነዚህ ያለተቋጨ ክርክሮች ሙሉ መልካቸው ለፍርድቤት የሚገለጸው በዚህ የመዝጊያ ንግግር ወቅት ነው::

ከነዚህ በተጨማሪ በመዝጊያ ንግግር ጊዜ ሊቀርቡ የሚገባውቸው ሌሎች ነገሮች አሉ:: ሌላው ወገን አስረዳለሁ ብሎ ሳያስረዳ ስለቀረው ነገር መግለጽ አንዱ ነው:: ሌላው ደግሞ ምንም ያህል ከባድ ቢሆን የራስን ደካማ ነጥቦች መጠቆም ነው:: ዐቃቤህግ ካለው የተለየ የተከራካሪነት ሚና የመነጨ ይሆን? የህግ ጠባቂ እንደመሆኑ እና ነገሮችን ያላድልየ፣ በትክክል ማቅረብ ስለሚጠበቅበት ይሆን? ወይስ ይህ ነገር በሌላኛው ወገን ቢገለጽ ሊፈጠር የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ - ፍርድቤቱ የማያውቀው ወይም ያልሰማው አዲስ ነገር ስለማይሆን ክብደቱ ቀለል ያለ ይሆናል - ከሚል ዕምነት የተነሳ ነው?

ይህ የክርክር መዝጊያ ንግግር እንዴት ሊዋቀር ይገባዋል? በርከት ያሉ ዘዴዎች አሉ:: ለምሳሌ በጭብጥ ላይ የተመሰረተ ወይም በምስክር (ማስረጃ) ላይ የተመሰረተ የንግግር አቀራረብ ሊኖር ይችላል:: ሆኖም ከነዚህ ውስጥ በጭብጥ ላይ የተመሰረተው አቀራረብ የተሻለ እንደሆነ ይታመናል:: በጠቅላላው የክስ ሂደት ዓላማው ጭብጦችን ማስረዳት ነው:: ስለዚህ አንድ ጭብጥ ከአንድ በላይ በሆነ የማስረጃ አይነት (ምስክር፣ ሰነድ፣ ኤግዚቢት)፣ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ምስክር ወይም ሰነድ ወዘተ ማስረዳት ሊያስፈልግ ይችላል:: ስለዚህ በማስረጃ ላይ ተመስርቶ ጠቅላላ ክርክሩን ለማጠቃለል ነገሩን የበለጠ ከማወሳሰብ በቀር የሚፈይደው አይኖርም:: ብዙ ማስረጃዎች፣ ጥቂት ጭብጦች በአንድ የክስ ጉዳይ ውስጥ ማግኘት የተዘወተረ ነው:: ስለዚህ

ነገሩን በቀላሉ መገንዘብ እንዲቻል ማስረጃዎቹን በጭብጦቹ ዙሪያ መተንተንና መከራከር ይቀላል::

መወያያ
በክርክር መዝጊያ ንግግር ጊዜ ንግግሩ በሁለቱም ወገኖች ክርክሮች ላይ የተመሰረተ ነዉ:: በዚህ ጊዜ የቱ ቀድሞ የቱ ቢከተል የተሻለ ነዉ?

ዐቃቤህግ በክርክር መዝጊያ ንግግር ጊዜ የራሱን ደካማ ነጥቦች የሚገልጽ ቢሆን በየትኛዉ የንግግሩ ክፍል ሊያካትተዉ ይገባል? በመነሻዉ፣ በመሃል ወይስ በመጨረሻ? ለምን?

5. ስለቅጣትና ይግባኝ

ስለቅጣት ክርክር

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸዉ ሁሉ ከተከናወኑ በኋላ ፍርድቤት በነገሩ ላይ ይወስናል:: ዐቃቤህግ ክሱን ካላስረዳ ተከሳሹን የማሰናበት ፍርድ ይሰጣል:: ክሱ በማስረጃ የተረጋገጠ ከሆነ ወይም ማስረጃዉ ክስ ያልቀረበበትን ወንጀል (ክስ ከቀረበበት ያነሰ እና በፍርድቤቱ ሊዳኝ የሚችል) ካስረዳ የጥፋተኛነት ዉሳኔ ይሰጣል:: ጥፋተኛነት ከተወሰነ ሌላ ዉሳኔ ይከተላል - የቅጣት ዉሳኔ:: ይህ ዉሳኔ የራሱ የሆነ የክርክር ሂደት ያለዉ ነዉ:: በዚህ ክርክር ዐቃቤህግ እንደ ህግ ጠባቂነቱ በግልጽ የተለየ ሚና አለዉ:: ያለማዳላት ስለተከሳሹም ስለራሱም ክርክር ሃሳብ የማቅረብ ኃላፊነት አለዉ (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 149(3))::

ዐቃቤህግ ስለቅጣት የሚያቀርበዉ ክርክር ቅጣትን ስለማክበድና ማቅለል ነዉ:: ምንም እንኳ አዘዉትሮ ዐቃቤህግ በዚህ ደረጃ የሚያቀርበዉ ክርክር ቅጣትን ስለማክበድ ቢሆንም አልፎአልፎ በህግ የተሰጠዉን ኃላፊነት የሚወጣበት አጋጣሚ እንዳለ ለማየት ይቻላል:: ለምሳሌ የግንቦት ሰባት ተከሳሾች ጉዳይ ላይ ዐቃቤህግ የቅጣት አወሳሰን ክርክር ሲያቀርብ ስለቅጣት ማክበድ ብቻ ሳይሆን ቅጣት ሊያቀልሉ ስለሚችሉ ነገሮችም ተከራክሯል - የቅጣት ማቅለያ ሃሳቦችን አቅርቧል:: ይህ ሃሳብ የቀረበዉ በጠቅላላዉ በክርክሩ ዉስጥ የተገኙ ወይም የቀረቡ ፍሬነገሮችን ወይም ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ ነዉ:: ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ዐቃቤህግ ይህን ኃላፊነቱን ለመወጣት አዘዉትሮ እንደሚስተዋለዉ የፖሊስን የቀድሞ የቅጣት ሰሌዳ መቅረብ አለመቅረብ መጠበቅ እንደሌለበት ነዉ::

የተለመደዉ የዐቃቤህግ የቅጣት ክርክር በተከሳሹ ላይ የሚቀርብ የቀድሞ ጥፋተኛነት ማስረጃ ስለሌለ ፍርድቤት ለጥፋቱ ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲወስን የሚጠይቅ ነዉ:: ሆኖም ከላይ እንደተገለጸዉ ስለቅጣት ክርክር ለማቅረብ ሬከርድ መኖር አለመኖሩ ወሳኝ አይደለም:: ጠቅላላ

ክርክሩ ራሱ የቅጣት ክርክር ለማቅረብ የሚሆኑ በርካታ ዕዉነታዎች ምንጭ ነዉ። ስለዚህ ሪከርድ ባለመኖሩ ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲወሰን የሚቀርብ ሃሳብ የቅጣት ክርክር ሊባል የሚችል አይደለም። ተመጣጣኝ ቅጣት መወሰን የፍርድቤት ተግባር ነዉ። ለፍርድቤት የሚያስፈልገዉ ቅጣትን ለማክበድና ለማቅለል የሚችሉ ፍሬነገሮችን እና ህጎችን መሰረት ያደረገ ክርክር እንዲቀርብ ነዉ። ስለዚህ ዐቃቤህግ በቅጣት ክርክር ጊዜ ቅጣትን የሚያከብዱና የሚያቀልሉ ሃሳቦችን እንዲያቀርብ ብቻ ሳይሆን እነዚህን ሃሳቦች መገንት የሚችሉበትን ምንጮች ማወቅና ከነዚህ ምንጮች ፈልፍሎ በማዉጣት ለፍርድቤት ማቅረብ ይጠበቅበታል።

ማሳያ

ተከሳሽ በስለት አስፈራርቶ በፈጸመዉ ተግባር በተራ ዉንብድና ተከሶ ጥፋተኛ ተብሏል እንበል። ዐቃቤህግ የቅጣት ሃሳብ እንዲያቀርብ ተጠየቀ። ጥፋተኛ የተባለዉ ክሱን ሰምቶ በሰጠዉ ዕምነት መሰረት ነዉ። ዐቃቤህግ ምን አይነት ሃሳብ ሊያቀርብ ይቸላል?

ስለይግባኝ ክርክር

በመጀመሪያ ደረጃ ነገሩን ያየዉ ፍርድቤት የቀረቡለትን ማስረጃዎች ሁሉ በቀጥታ ሰምቶና አይቶ ዉሳኔ ስለሚሰጥ ከዚህ ዉሳኔ ዉስጥ ስህተቶችን መንቀስ ከባድ ነዉ። ስለዚህ የይግባኝ ክርክር ማድረግ ከፍ ያለ ክህሎትን የሚጠይቅ ነዉ።

የይግባኝ ክርክር በሁለት አይነት ዉሳኔዎች ላይ ሊቀርብ ይችላል። ክርክሩ ከማለቁ በፊት በሚሰጡ ዉሳኔዎችና ክርክር ካለቀ በኋላ በሚሰጥ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ሊባል ይችላል። ከፍርድ በፊት በሚሰጥ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበዉ በሁሉም አጋጣሚዎች አይደለም። ከፍርድ በኋላም ይግባኝ ማለት የሚቻለዉ በሁሉም ዉሳኔዎች ላይ አይደለም።

ከፍርድ በፊት የሚሰጡ የተለያዩ ዉሳኔዎች ይኖራሉ። እነዚህም ቀጠሮን ፣ የክስ መቃወሚያን እና የማስረጃን ተቀባይነት በተመለከተ የሚሰጡ ትዕዛዞች ናቸዉ። ከነዚህ ሌላ ትዕዛዞች ቢኖሩም ተጠቃሾቹ ትዕዛዞች ላይ ይግባኝ ማለት የሚቻለዉ ትዕዛዞቹ እንደተሰጡ ሳይሆን ነገሩ ላይ የጥፋተኝነት ወይም ለጊዜዉ የመልቀቅ ዉሳኔ ተሰጥቶ ይግባኝ በሚባልበት ጊዜ ነዉ። በነዚህ ትዕዛዞች ላይ ይግባኝ ማለት ቢፈቀድ ሊደርስ የሚችለዉን የጉዳዮች መንዛዛትና በየጊዜዉ መቋረጥ ፣ በይግባኝ ከተወሰነ በኋላ ነገሩን ሌላ ችሎት እንዲያየዉ በማድረግ ነገሩ በየጊዜዉ ጥሬ እንዲሆን የማድረግ ዉጤት በቀላሉ ለማየት ይቻላል። ስለዚህ ዐቃቤህግ እንዲህ አይነት ይግባኝ ከማቅረብ መቆጠብ አለበት።

ፍርድቤት እንዲህ አይነቱ ይግባኝ ሲቀርብለት ያልተፈቀደ ወይም በህግ የተከለከለ ይግባኝ ነዉ ብሎ ሊያሰናብት ይገባል:: ይህ መሰናክል ካልተደረገ ዐቃቤህግ ይህን የህግ ክልከላ በመዘንጋትም ሆነ በመጣስ ይግባኝ ሊያቀርብ እና ሊስተናገድ ስለዚህም ከላይ የጠቀስናቸዉ ችግሮች እንዲከሰቱ ያደርጋል::

ማሳያ

የሙስና ጉዳዮችን የሚያይ ፍርድቤት ዐቃቤህግ ለክሱ በሰጠዉ መግለጫ ምስክሮችን ባልቆጠረበት፣ የሚያስረዱበትን ጭብጥ ባልሰጠበት የቅድመክስ ክርክር ከተካሄደ በኋላ የያዛቸዉን ጭብጦች በተቆጠሩ የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ ለመወሰን ቀጠሮ ሰጠ እንበል:: በዚህ ጊዜ ዐቃቤህግ ምስክሮች ላቅርብ ብሎ ሲጠይቅ ፍርድቤቱ ምስክሮቹን አልሰማም በተቆጠረዉ ማስረጃ ብቻ እወስናለሁ ብሎ የዐቃቤህግን የማስረጃ ማቅረብ ጥያቄ ዉድቅ አደረገ:: ዐቃቤህግ ይግባኝ አቀረበ ፍርድቤቱም ይግባኙን ተቀብሎ ማስረጃ መሰማት አለበት ብሎ ዉሳኔ ሰጠ፣ መዝገቡን መለሰ:: ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድቤት ትክክል ነዉ? ለምን?

ዐቃቤህግ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በሁሉም ነገሮች ላይ ይግባኝ ለማለት ይችላል? ክሱን የሚጎዳ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ካለዉ ይግባኝ ማለቱ ላይ ብዙም አጠያያቂ ነገር አይኖርም:: ነገር ግን ከህግ ጠባቂነት ሚናዉ አኳያ ህግን ያልተከተለ ተከሳሹን የሚጎዳ ዉሳኔ ቢወሰንና ተከሳሹ ካለማወቅ የተነሳ ዉሳኔዉን የማስለወጥ ርምጃ ሳይወስድ ቢቀር ዐቃቤህግ ዉሳኔዉን ለማስቀየር ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል?

የዐቃቤህግን ክስ የሚጎዳ ዉሳኔ ምናልባት ዐቃቤህግ እስካላመነበት ድረስ ተከሳሽን በነጻ የማሰናበት ዉሳኔ ነዉ:: ጥፋተኛነት በተወሰነበት ጉዳይ ደግሞ የቅጣት መጠን ማነስ ለይግባኝ ምክንያት ሊሆን ይችላል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 185(2))::

መወያያ

ቅጣቱ ከህግ በተቃራኒ ቢበዛ ዐቃቤህግ በይግባኝ ሊያስለዉጠዉ ይችላል? ስለቅጣቱ አወሳሰን ዐቃቤህግ የሚያቀርባቸዉ ክርክሮች ቅጣት ስለማቅለልም ጭምር በመሆኑ ይህን ክርክሬን ፍርድቤቱ ያለፈብኝ ያላግባብ ነዉ የሚል ክርክር በይግባኝ ከማቅረብ ይከለክላል?

ዐቃቤህግን ቅር ያሰኘዉ ፍርድ በይግባኝ ሰሚ ፍርድቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የሰጠዉ ከሆነ ይግባኝ የማለት ዕድል የሚኖረዉ ይህ ፍርድ ቀደም ሲል በመጀመሪያ ደረጃ የተሰጠዉን ፍርድ ለዉጦት ከሆነ ነዉ (የፌዴራል ፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ 25/1988 ቁ. 9(2))::
ስለዚህ በፌዴራል ፍርድቤቶች በሚታዩ ጉዳዮች ዐቃቤህግ በይግባኝ በጸና ፍርድ ላይ ተጨማሪ

ይግባኝ ሊጠይቅ አይችልም ማለት ነዉ:: ይህም የህግ ስህተት ካለ በሰበር ለማስለወጥ የሚቀርበዉን አቤቱታ የሚያስቀር አይደለም::

አንዳንድ ጊዜ ተከሳሹ በሌለበት የተወሰነ ፍርድ እንዲነሳ ተከሳሹ የሚያቀርበዉ ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ ፍርዱ ቀሪ ይሆናል:: ነገሩ እንዳዲስ እንዲታይ ይሆናል:: በዚህ ጊዜ የዐቃቤህግ ማስረጃዎች በተለያየ ምክንያት የማይገኙ ሊሆኑ ይችላሉ:: በዚህ ጊዜ የዐቃቤህግ ክስ በእጅጉ ይጎዳል:: ይህ ሁኔታ ለዐቃቤህግ ይግባኝ የማለት ሥልጣን ያስገኝለታል? ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ፍርድ ቀሪ የሚደረግበትን ሁኔታ የሚመራዉ ህግ እንደሚለዉ (በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 202) ክሱ ቀሪ ተደርጎ ነገሩ እንደገና እንዲታይ ሲወሰን ዐቃቤህግ ክሱን ሥልጣን ላለዉ ፍርድቤት ያቀርባል ተብሎ ተደንግጓል:: የተከሳሹም ጥያቄ ዉድቅ ሲደረግ ይግባኝ ሊባልበት እንደማይቻል በዚሁ ህግ ተደንግጓል (ከቅጣቱ ዉሳኔ በቀር):: ስለዚህ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ዉሳኔን ቀሪ ለማድረግ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ የሚሰጥ ዉሳኔን ለማስለወጥ ይግባኝ ማለት የሚቻል መሆኑ ሲበዛ ያጠራጥራል::

ይግባኝ እንዴት ይጠየቃል? የይግባኝ መጠየቂያ ጊዜ በህግ ተመልክቶ ይገኛል:: በዚህ ጊዜ ካልቀረበ ይህ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት በማስረዳት በፍርድቤት አስፈቅዶ ካልሆነ ይግባኝ ሊሰማ አይችልም:: ስለዚህ ይግባኝን ያለበቂ ምክንያት ጊዜዉ እንዲያልፍ መፍቀድ አይገባም ፣ በተለይም የይግባኝ ጊዜን በህግ እንደተመለከተዉ ጠንቅቆ ማወቅ ይገባል::

በተወሰነለት ጊዜ የቀረበ ይግባኝ ይዘቱ ምን መሆን አለበት? በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 189 እንደተመለከተዉ የይግባኝ ቅሬታዉን የሚገልጹ ምክንያቶች በተራ ቁጥር ተለይተዉ የተዘረዘሩበት መሆን ይገባዋል:: በነዚህ ምክንያቶች ፍርዱ ምን ሊሆን እንደሚገባዉ ማለትም ምን ሊወሰንለት እንደሚገባ ዐቃቤህግ ሊገልጽ ይገባል::

ዐቃቤህግ ያቀረበዉ ይግባኝ ተቀባይነት አግኝቶ ሊሰማ የሚችል ከሆነ ዐቃቤህግ ፍርድቤቱ በሚወስነዉ ቀን ቀርቦ ክርክሩን ማሰማት አለበት:: ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መቅረቱን ካላስረዳ በቀር ይግባኙ ይሰረዛል ተሰርዞም ይቆያል:: ዐቃቤህግ ተቋም እንደመሆኑ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ፍርድቤት እንዳይቀርብ የሚያደርገዉ መሆኑ አጠራጣሪ ነዉ:: ስለዚህ ይህን አስረዳለሁ ብሎ ግለሰብ ዐቃቤህግ ክክርክሩ መቅረት አይኖርበትም::

የተከሳሽ ይግባኝ ከሆነ በተመሳሳይ የሚሰማበት ቀን ይወሰናል:: በዚህ ጊዜ ዐቃቤህግ እንደመልስ ሰጭ ካልቀረበ ነገሩ የርሱን መቅረብ ሳይጠብቅ እንደሚሰማና እንደሚወሰን ሊያዉቅ ይገባል::

ዐቃቤህግ ቀርቦ ክርክሩን የሚያሰማ ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ነገሩን ያየዉ ፍርድቤት የተጠቀመዉን ማስረጃ እንደገና እንዲመረመርለት መጠየቁ የሚጠበቅ ነዉ:: ሆኖም ምናልባት ይህ ማስረጃ በርግጥም ደካማ ሊሆን ይችላል:: በሌላ በኩል ክሱን ለማዳን የሚያስችል በመጀመሪያ ደረጃ ያልቀረበ ማስረጃ ሊኖር ይችላል:: ስለዚህ ይህን ማስረጃ በመጀመሪያ ደረጃ

ያልቀረበበትን ምክንያት አስረድቶ ማቅረብ የሚቻልበት መንገድ መፈለግ ይኖርበታል። ይግባኝ ሰሚ ፍርድቤት ተጨማሪ ማስረጃ የሚቀበልበት ሥነሥርዓት በህግ ተመልክቶ ይገኛል (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 194)። ይህን መንገድ ተከትሎ ይግባኝ ባይ ዐቃቤህግ ተጨማሪ ማስረጃ በይግባኝ ጊዜ ለማቅረብ መጠየቅ ይችላል?